


# ያልታተሙ የሰበር ውሳኔዎች በአንድ ተሰብስበው የተዘጋጁ ቅፅ 3

በዳንኤል ፍቃዱ ( ጠበቃና የህግ አማካሪ)

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-203260

ቀን፡-30/03/2014ዓ/ም

**ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነዉ**

**ተሾመ ሽፈራዉ**

**ሀብታሙ እርቅይሁን**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ነጻነት ተገኝ**

**አመልካች ፡- የጉምሩክ ኮሚሽን ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት**

**ተጠሪ ፡- አቶ ኤልያስ ዩሱፍ**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበትን ይግባኝ ማቅረብ እንዲቻል ለማስፈቀድ የቀረበ ማመልከቻ ዉድቅ በማድረግ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ተብሎ የቀረበ አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በመሆን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ግራ ቀኙ በነበራቸው ክርክር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት በመ/ቁጥር 13393 ላይ በቀን 27/02/2012 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ዉሳኔዉ ከተነበበ በኋላ ተጠሪ በዉሳኔዉ ላይ በአሃዝና በፊደል የተጻፈዉ የገንዘብ መጠን ልዩነት ስላለበት ይታረምልኝ በማለት አመልክተዉ ፍርድ ቤቱ በመዝገቡ ላይ በቀን 18/03/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በፊደል “ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንትም ተብሎ የተጻፈዉ የአጻጻፍ ስህተት ስለሆነ አራት መቶ ሃምሳ ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም ” ተብሎ እንዲነበብ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 208 መሰረት አርሟል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ጊዜዉ ያለፈበትን ይግባኝ ማቅረብ እንዲችል እንዲፈቀድለት በቀን 11/01/2013ዓ/ም የተጻፈ ማመልከቻ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በማመልከቻዉ ላይ የጠቀሰዉ ምክንያት የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ ያለፈበት በውሳኔዉ ላይ እርማት ሳይሰጥ በመቆየቱ ግልባጭ ሳይደርሰዉ ለ21 ቀናት በስር ፍርድ ቤት እንዲቆይ በመደረጉ ምክንያት ነዉ ስለሆነ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው መቆጠር ያለበት እርማት ተደርጎ ውሳኔው ከተሰጠበት ከቀን 18/03/2012 ዓ/ም ጀምሮ ሊሆን ይገባል በማለት ጊዜዉ ያለፈዉ በዚህ ምክንያት መሆኑ ታዉቆ እንዲፈቀድለት ጠይቋል።ችሎቱም ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጡ አድርጎ በሰጠዉ አስተያየት ፍርድ የተሰጠው በቀን 27/02/2012 ዓ/ም ሆኖ ስህተቱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 208 መሰረት የታረመዉ ተጠሪ ባቀረብኩት ማመልከቻ መነሻ ነዉ። አመልካች ይግባኙን በጊዜው ያላቀረበው በቸልተኝነት በመሆኑ ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ሊቆጠር የሚገባው ፍርድ ከተሰጠበት ከቀን 27/02/2012 ዓ/ም ጀምሮ በመሆኑና የአመልካች ጥያቄ በበቂ ምክንያት የተደገፈ ባለመሆኑ ማስፈቀጃዉ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም በማለት አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል።

ችሎቱም በመ/ቁጥር 195771 ላይ በቀን 20/05/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የሰጠዉ በቀን 27/02/2012ዓ/ም ሆኖ አመልካች የይግባኝ ቅሬታ ያቀረበዉ በአገራችን የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ከመከሰቱ በፊት ሆኖ ዉሳኔ ከተሰጠ ከ77 ቀናት በኋላ በቀን 06/05/2012ዓ/ም በመሆኑና እርማት እየተሰጠ ለ21 ቀናት በስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በመዘግየቱ ምክንያት ጊዜዉ አለፈብኝ በማለት ያቀረበዉ ምክንያትም እንደ በቂ ምክንያት ሊቆጠር የሚችል ስላልሆነ የአመልካችን ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም ሲል ዉድቅ በማድረግ ወስኗል።

አመልካች በቀን 12/06/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡-በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 323/2 መሰረት ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እና ይርጋ ሊቆጠር የሚገባው ስህተቱ እርማት ተደርጎ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ሊሆን ሲገባ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የወሰነዉ ከዚህ የሕግ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ነዉ።ጊዜዉ ያለፈብን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እርማት ለመስጠት ረጅም ጊዜ በመፍጀቱ ምክንያት ነዉ።የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ መቆጠር ያለበት ዉሳኔዉ ላይ ያለዉ ስህተት ታርሞ ስህተት አልባ ዉሳኔ ከተሰጠበት ከቀን 18/03/2012ዓ/ም ጀምሮ ሊሆን ስለሚገባ በሰ/መ/ቁጥር 59085 ላይ ከተሰጠዉ ትርጉም አንጻር ጉዳዩ ታይቶ ጊዜዉ ያለፈበትን ይግባኝ ማቅረብ እንዲንችል አለመፈቀዱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል።

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የይግባኝ ማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜው ሊቆጠር የሚገባው ፍርድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው ወይስ ፍርድ ከታረመበት ጊዜ ጀምሮ ነው? እንዲሁም ፍርዱ ላይ ያለዉ ስህተት ከታረመበት ጊዜ አንስቶ ሲቆጠር ጊዜው አልፏል ወይስ አላለፈም የሚለው ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 14/08/2013 ዓ/ም የተጻፈ መልስ በማቅረብ፡- ዉሳኔዉ የተሰጠዉ በቀን

27/02/2012ዓ/ም ሲሆን የአጻጻፍ ስህተት እንዲታረም የጠየቅሁት ተጠሪ ነኝ ፡፡አመልካች ዉሳኔዉ እርማት ስላለበት ግልባጭ አልተሰጠኝም ያለዉ ምክንያት ለስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ አዲስ ምክንያት ስለሆነ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም፡፡እርማቱም የፍርዱን መሰረታዊ ክፍል የሚነካ ባለመሆኑ አመልካች እርማቱን እየጠበኩ ጊዜ አለፈብኝ በማለት ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡አመልካች ይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበዉ በቀን 06/05/2012ዓ/ም ሲሆን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበት ነዉ ተብሎ ተቀባይነት ከአጣ በኋላ ማስፈቀጃ ያቀረበዉ በቀን 11/01/2013ዓ/ም ነዉ፡፡ይህም የሚያሳየዉ አመልካች ጉዳዩን በቸልተኛነት ባለመከታተል ጊዜዉን በአግባቡ ስላልተጠቀመና በሰ/መ/ቁጥር 59085 ላይ የተሰጠዉ ትርጉምም ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ስለሌለዉ የአመልካች ማመልከቻ ተቀባይነት በማጣቱ የተፈጸመ ስህተት የለም ተብሎ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ነጥብ ከግምት በማስገባት አመልካች የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበትን ይግባኝ ማቅረብ እንዲችል እንዲፈቀድለት ያቀረበዉ ማመልከቻ ተቀባይነት በማጣቱ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀዉ በልዩ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የፍትሐ ብሔር ክርክር መመራትና እና እልባት ማግኘት ያለበት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን ሥነ ሥርዓት ተከትሎ ሊሆን ይገባል፡፡ይህም ሥርዓት የተዘረጋበት ምክንያት ክርክር ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ ክርክሮች ተለይተዉ በሚታወቅ ሥነ ሥርዓት አግባብ ተመርተዉ ፍትሐዊ እልባት እንዲያገኙ ለማድረግ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ለማሳካት የታቀደዉ ዓላማ ከግብ እንዲደርስ ለማድረግ ነዉ፡፡የይግባኝ አቀራረብ እና ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ነዉ ተብሎ በሕጉ የተደነገገዉ ሥነ ሥርዓትም ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት በመሆኑ የሕጉን ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 323/2 ስር እንደተደነገገዉ የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚገባዉ ይግባኝ የሚባልበት ፍርድ፣ዉሳኔ ወይም ትእዛዝ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 60 ቀናት ዉስጥ ነዉ፡፡የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበትን ይግባኝ ማቅረብ እንዲቻል ለማስፈቀድ የሚቀርብ ማመልከቻ ጊዜዉ ሊያልፍ የቻለበትን በቂ ምክንያት የሚያሳይና ይህንኑ ምክንያት ከሚያስረዳ ማስረጃ ጋር መቅረብ እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 325 እና 326 ስር ተደንግጓል፡፡ከእነዚሁ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ የምክንያቱ መከሰት በማስረጃ ከተረጋገጠ የምክንያቱ በቂ መሆን ያለመሆን ጉዳይ በእነዚሁ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉ ከግምት እየገባ እንደየምክንያቱ አይነት እየተመዘነ የሚወሰን ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ይግባኝ የሚባልበት ፍርድ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ በቅን 27/02/2012ዓ/ም እንደሆነ አከራካሪ አይደለም፡፡በዚህ ዉሳኔ ላይ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል ተብሎ የተወሰነዉ የገንዘብ መጠን በአሃዝና በፊደል ሲጻፍ ልዩነት ስለነበር በፊደል የተጻፈዉ ስህተት ስላለበት በአሃዝ ከተጻፈዉ ጋር እንዲመሳሰል ተደርጎ እንዲታረም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 208 መሰረት አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ

መሆናቸዉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤት የተጠሪን አቤቱታ ተቀብሎ ስህተቱን የሚያርም ትእዛዝ የሰጠዉ በቀን 18/03/2012ዓ/ም ነዉ፡፡ ስህተቱ እንዲታረም ጥያቄ ያቀረበዉ አመልካች ባለመሆኑ ስህተቱን የሚያርም ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ ሳይጠብቅ ዋናዉ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ይግባኝ ማለት እንደሚፈልግ ገልጾ ፍርድ ቤቱ ግልባጭ እንዲሰጠዉ መጠየቅ ይችላል፡፡ነገር ግን በዚህ አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 323/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት በ60 ቀን ዉስጥ ይግባኝ እንደሚጠይቅ ገልጾ የዉሳኔ ግልባጭ እንዲሰጠዉ የጠየቀ ስለመሆኑና የሥር ፍርድ ቤት ግልባጩን ያዘገየበት ስለመሆኑ በመግለጽና በማስረጃ በማስደገፍ ለይግባኝ ሰሚዉ ችሎት አላስረዳም፡፡ እንዲሁም በፍርዱ ላይ ስህተቱ መኖሩን ካወቀም ራሱ ስህተቱ እንዲታረምለት የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሳያልፍ መጠየቅ እየቻለ ይህንን ስለማድረጉ አላስረዳም፡፡

በተጨማሪም ተጠሪ አመልካችነት የአጻጻፍ ስህተት በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ትእዛዝ የታረመ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች ይግባኝ የሚልበት ጉዳይ በስህተቱ ላይ ሳይሆን በፍርዱ ላይ ባለዉ ዋናዉ ጉዳይ ላይ እንደመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የአጻጻፍ ስህተቱን እስከሚያርም መጠበቅ ሳይጠበቅበት የፍርድ ዉሳኔዉ በራሱ ይግባኝ ሊባልበት የሚችል በመሆኑ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈልግ ገልጾ የፍርድ ዉሳኔ ግልባጭ በመዉሰድ እስከ ቀን 27/04/2012 ዓ/ም ድረስ ባለዉ 60 ቀናት ዉስጥ ይግባኙን ማቅረብ ሲገባዉ የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበዉ በቀን 06/05/2012 ዓ/ም ፍርዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ሲቆጠር 60 ቀን ካለፈ በኋላ ነዉ፡፡ በዚህ ቀን ያቀረበዉ የይግባኝ ማመልከቻ ጊዜ ያለፈበት ነዉ ተብሎ ተቀባይነት ሲያጣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 325/1 መሰረት ተቀባይነት የለዉም ተብሎ ከተመለሰበት ጊዜ ጀምሮ በ10 ቀን ዉስጥ የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻዉን ማቅረብ ሲገባዉ የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻዉን ያቀረበዉ ግን ከወራት በኋላ በቀን 11/01/2013ዓ/ም ጀምሮ መሆኑ የሚያሳየዉ አመልካች በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተቀመጠዉን የጊዜ ገደብ ንቁ ሆኖ አለመጠቀሙንና በግደለሽነት ማባከኑን የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለዉ ፍርዱን የሰጠዉ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 208 መሰረት ይግባኝ በሚባልበት ፍርድ ላይ የሚገኘዉን ስህተት ካረመ በኋላ ሲሆንና በዚህ አግባብ እርማት እንዲደረግ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሳያልፍ ተጠይቆ የቀረበ አቤቱታ መርምሮ ፍርድ ቤቱ ተገቢዉን ትእዛዝ ሳይሰጥ ቢያዘገይ እና በዚህ ምክንያት ጊዜ በመባከኑ ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ቢያልፍ ለይግባኝ ባይ እንደ በቂ ምክንያት ተቆጥሮለት የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻዉ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ግን ፍርዱ በራሱ ይግባኝ ሊባልበት የሚችል ሆኖ እያለ ፍርዱ ከተሰጠበት ከቀን 27/02/2012 ዓ/ም ጀምሮ አመልካች በ60 ቀን ዉስጥ ይግባኝ ለማለት እንደፈለገ ገልጾ ግልባጭ እንዲሰጠዉ ጠይቆ በስር ፍርድ ጉድለት ምክንያት ጊዜዉ እንዳለፈበት ወይም የስር ፍርድ ቤት በፍርዱ ላይ ያለዉን ስህተት የሚያርም ትእዛዝ ሳይሰጥ በማዘግየቱ ምክንያት ጊዜዉ እንዳለፈበት ካለማስረዳቱም በተጨማሪ ራሱ ያላቀረበዉን የእርማት አቤቱታ መሰረት በማድረግ ያቀረበዉ የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ በበቂ ምክንያትና ማስረጃ የተደገፈ አይደለም በሚል በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ተቀባይነት በማጣቱ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ ስህተት አላገኘንም፡፡ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

# ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 195771 ላይ በቀን 20/05/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

??/? /?? ? 203214
?? 29/3/2014 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - የጉምሩክ ኮምሽን - የቀረበ የለም

ተጠሪ - አቶ ተስፋ ዮሀንስ - ጠበቃ ካላአዩ አያለው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች የካቲት 19 ቀን 2013 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 195827 ጥር 18 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 243070 ሐምሌ 3 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 15 ተገቢ ያልሆነ ትርጉም በመስጠት የተሰረዘ ዲክላራሲዮን ጸንቶ ያለ ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 15 የእቃ ዲክላራሲዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ 5 የሥራ ቀን ድረስ የጉምሩክ ሥነ ሥረዓት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ካልጀመረ ዲክላራሲዮኑ ሊሰረዝ ይችላል እያለና በተጨማሪም የደንብ ቁጥር 118/08 አንቀጽ 20(1) ሊሰረዝ እንደሚችል ደንግጎ እያለ ላይሰረዝ ይችላል የሚል ትርጉም መስጠቱ ካለአግባብ ሲሆን ግመሎቹ ከህጋዊ መስመር ውጪ ወደ ሱዳን ለመግባት ሲሉ መያዛቸው እየታወቀ ጊዜ ባለፈበት ዲክላራሲዮን ህጋዊ አንደሆኑ ተወስዶ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከኢፌዴሪ ታክስ ይግባኝ ኮምሽን ሲሆን ይግባኝ ባይ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ የአሁን ተጠሪ የቁም እንሰሳት ወደ ውጪ የመላክ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ነው፡፡ 43 ግመሎች ወደ ውጪ ለመላክ በ7/12/2008 ዓ/ም እና በ13/12/2007 ዓ/ም ህጋዊ ዲክላራሲዮን የተመታለት እና በቀን 22/11/1007 ዓ/ም እቃ ወደ ውጪ መላኪያ የባንክ ፈቃድ ተሰጥቶኛል፡፡ በወቅቱ በሱዳን መንግስት የቁም እንሰሳት ወደ ሀገር እንዳይገባ በመከልከሉ የዘገዩና በፌደራል ፖሊስ ጥበቃ ስር ከቆዩ በኋላ በራሴ ጠባቅዎች እያስጠበኩ ባለሁበት ሁኔታ 5 ቀን ያለፈበት ዲክላራሲዮን ነው በሚል እግራቸው ታስሮ ተኝተው እያለ ግመሎቹ በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሱዳን ሊሻገሩ ነው በሚል መውረሱ ተገቢ ባለመሆኑ ይለቀቅልኝ ሲል አመልክቷል፡፡ የአሁን አመልካችም ግመሎቹ የይግባኝ ባይ አለመሆናቸው ለዚህም ደግሞ በወቅቱ መቅረጫ ጣቢያው ዲክላራሲዮኑ ሲሰረዝ በባለሥልጣኑ ቁጥጥር ሥር ከሚገኙ ግመሎች መካከል የይግባኝ ባይ ግመሎች የሚገኙ እንደሆኑ ለማጣራት በአካል ቀርቦ እንዲለያቸው ቢጠየቅ በማፈግፈግ መብቱን አልተጠቀመም፡፡ በተደረገው የመስክ ምልከታም የይግባኝ ባይ ግመሎች እንዳልተገኙ አረጋግጠናል፡፡ በተጨማሪም ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ 5 የስራ ቀናት ያለፈበትና ቀጣዩ የጉምሩክ ሥነ ሥረዓት ያልተጀመረበት በመሆኑ ይግባኝ ባይ ህጋዊ ዲክላራሲዮን አለው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም ውሳኔው ይጽናልኝ በሚል መልስ ሰጥቷል፡፡ የኢፌዴሪ ታክስ ይግባኝ ኮምሽን አከራክሮ በመ/ቁጥር ታይኮ ከተ-1642 ሴኔ 3 ቀን 2011 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 15 መሰረት ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዲክላራሲዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማሳወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ 5 የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ሥነ ሥረዓት ካልተጀመረ ዲክላራሲዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል ሲል ይደነግጋል፡፡ በመመሪያ ቁጥር 118/08 አንቀጽ 20(4 እና 5) እቃ ወደ ሀገር እንዲገባ ወይም እንዲወጣ ከተፈቀደ ቀን ጀምሮ በተለያየ ምክንያት ሳይፈጸም ከቀረ በ10 ቀናት ውስጥ ሲያሳውቅ ሊሰረዝ እንደሚችል ይገልጻል፡፡ እንዲሁም ከዚህ በላይ ከቆየ በበቂ ምክንያት እስከ 1 ዓመት በሆነ ጊዜ አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶ ዲክላራሲዮኑ እንደሚሰረዝ ይገልጻል፡፡ ይሁንና ቀርቦ ያላሰረዘ እንደሆነ መብቱ የሚቀር ይሆናል፡፡ በመሆኑም ግመሎቹ ዲክላራሲዮን ተሰጥቶበት ወደ ውጪ ሳይወጡ የቀሩና መልስ ሰጪም የሚያውቅ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ዲክላራሲዮን መሰረዝ የመ/ሰጪ መብት ሲሆን እያወቀ መቆየቱ ተገቢ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ይ/ባይ ግመሎቹ ወደ ውጪ መውጣት የማይችሉ ከሆነ ዲክላራሲዮን አሰርዞ ከጉምሩክ ክልሉ ማውጣት ሲኖርበት መ/ሰጪም ከጉምሩክ ክልሉ እንዲወጡ ማስገንዘብ ሲገባ በዝምታ መታለፉ ተገቢ አይደለም፡፡ በመሆኑም ይ/ባይ ጊዜ ያለፈበት ዲክላራሲዮንና ግመሎቹ ወደ ውጪ መውጣት የማይችሉ መሆኑን እያወቀ ዲክላራሲዮን ማሰረዝ ስገባው በጉምሩክ ክልል ውስጥ ማቆየቱ ተገቢ ባለመሆኑ መወረሱ ስህተት አይደለም ሲል የመ/ሰጪን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ባይ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ አከራክሮ በመ/ቁጥር 243070 ሐምሌ 3 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ባይ በህጋዊ መንገድ 43 ግመሎች ወደ ውጪ ለመላክ በመ/ሰጪ ፈቃድ በድንበር ላይ የተገኘ መሆኑ የተረጋገጠና ባልተወቀ ሁኔታ ወደ ውጪ ሳይላኩ የቆዩና የይግባኝ ባይ ዲክላራሲዮን 5 ቀን ያለፈበት መሆኑ ታውቋል፡፡ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 15(1) እቃ ወደ ወጪ ሳይላክ የቀረና በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ቀጣይ የጉምሩክ ሥነ ሥረዓት ካልጀመረ ዲክላራሲዮኑ ሊሰረዝ እንደሚችል ይገልጻል፡፡ ካልተሰረዘ ግን ምን እንደሚሆን የሚገልጽ ባለመሆኑ ካልተሰረዘ ጸንቶ እንዳለ የሚያመለክት በመሆኑ መ/ሰጪ የይ/ባይን ግመሎች ካለአግባብ የወረሰ መሆኑን የሚያረጋግጥ በመሆኑ መ/ሰጪ የግመሎቹን

በወቅቱ ዋጋ መሰረት ለይ/ባይ ይከፈል ሲል ወስኗል፡፡ መ/ሰጪ የአሁን አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 195827 ጥር 18 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት ዲክላራሲዮን ጸንቶ ባለበትና ባልተሰረዘበት ሁኔታ ግመሎቹ ሊወረሱ አይገባም ሲል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 15 እና ከመመሪያ ቁጥር 118/2008 አንቀጽ 20 አኳያ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ መጋቢት 22 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ሚያዝያ 12 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ 43 ግመሎች ወደ ውጪ ለመላክ ህጋዊ መስፈርቶቹን አሟልቶ በአሁን አመልካች ፈቃድ ዲክላራሲኖን ተሰጥቷቸው በጉምሩክ ክልል የገቡና ወደ ውጪ ሳይላኩ የቆዩና ግመሎቹን ወደ ውጪ መላኪያ ጊዜ 5 የስራ ቀን ያለፈበትና ግመሎቹ በጉምሩክ ክልል ውስጥ የተገኙ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በህጋዊ መንገድ ወደ ውጪ የሚላኩ እቃውች በተፈቀደው ቀን ሳይላኩ በቀሩበት ጊዜ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 15 ዲክላራሲዮን አቅራቢው ዲክላራሲዮኑ ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማሳወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ 5 የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ሥነ ሥረዓት ካልተጀመረ ዲክላራሲዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ የመመሪያ ቁጥር 118/08 አንቀጽ 20(4 እና 5) ደግሞ እቃ ወደ ሀገር እንዲገባ ወይም እንዲወጣ ከተፈቀደ ጀምሮ በተለያየ ምክንያት ሳይፈጸም ከቀረ በ10 ቀናት ውስጥ ሲያሳውቅ ሊሰረዝ ይችላል ሲል ደንግገው ይገኛሉ፡፡ የአሁን ተጠሪ ግመሎቹን በተፈቀደለት ጊዜ ውስጥ ወደ ውጪ ሳይልካቸው 5 የስራ ቀን አልፎበታል፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ዲክላራሲዮኑን አሰርዞ ግመሎቹን ከጉምሩክ ክልል ማስወጣት የሚገባው ሲሆን ዲክላራሲዮኑ ካልተሰረዘ በዲክላራሲዮኑ መጠቀም ይችላል የሚል ትርጉም የሚሰጠው ሳይሆን ዲክላራሲዮኑን በማሰረዝ ሊያገኝ የነበረውን መብት የሚያጣ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ማለት ዲክላራሲዮኑ የመላኪያ ጊዜ ካለፈበት ግመሎቹን ከጉምሩክ ክልል አውጥቶ እንደገና ወደ ውጪ መላኪያ ማስፈቀጃ ዲክላራሲዮን የሚያወጣ አንጂ ጊዜ ባለፈበት ዲክላራሲዮን ወደ ውጪ መላክ የሚችል አይደለም፡፡ እንዲሁም የዚህ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀጽ 15 ድንጋጌ በህጋዊ መንገድ በጉምሩክ ክልል ውስጥ የገቡ ወደ ውጪ የሚላኩ እቃዎች በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ውጪ ሳይላኩ የመላኪያ ጊዜው ያለፈበት አንደሆነ ላኪው ዲክላራሲዮኑን በማሰረዝ የሚሰጡትን መብቶች መጠቀም የሚችል ሲሆን ዲክላራሲዮኑን ካላሰረዘ ግን ውደ ውጪ ሊልካቸው በጉምሩክ ክልል ውስጥ የገቡት እቃዎች ህግ ወጥ ሆነው እንደ ኮንትሮባንድ እቃ ይወረሳሉ የሚል ትርጉም የሚያሰጠውም አይደለም፡፡ እቃ ወደ ውጪ ለመላክ በህጋዊ መንገድ በጉምሩክ ክልል የገባ እቃ የመላኪያ ጊዜው ካለፈበት ከጉምሩክ ክልል በማስወጣት ወደ መደበኛው ሁኔታ እንዲመለስ ከሚደረግ በቀር በህጋዊ መንገድ በጉምሩክ ክልል የገባ እቃ የመላኪያ ጊዜ ስላለፈበት ብቻ በህገ ወጥ መንገድ ወደ ወጪ ለማስወጣት የጉምሩክ ክልል ውስጥ እንደ ገባ እቃ እንደ ኮንትሮባንድ ተቆጥሮ የሚወረስ ስለመሆኑ የጉምሩክ አዋጁ አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ከዚሁ አንጻር አይቶ አሁን አመልካች ካለ አግባብ የወረሰውን የተጠሪ ግመሎች ለአሁን

ተጠሪ በወቅቱ በነበራቸው ዋጋ አንዲመለስ ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 195827 ጥር 18 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 243070 ሐምሌ 3 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ/ቁጥር 289667 ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መ/ቁ/ 203210

ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ አቶ ገመቹ ቤኩማ፡- ጠበቅ ፍቅሬ ሞያ ቀረቡ

ተጠሪ፡ ሒና ፋርም ኃ/የተ/የግ/ማህበር፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ አመልካች ያቀረበዉ ጊዜ ያለፈበት ይግባኝ ማስፈቀጃ ጥያቄ ተቀባይነት ባለማግኘቱ የቀረበ አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን የአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ በተጠሪ ሆቴል ውስጥ ተቀጥሬ እየሰራሁ እያለ ያለጥፋት የስራ ውል ስለአቋረጠብኝ የስራ ስንብት ክፍያዎች እንዲከፈለኝ በማለት ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በሰጠዉ መልስ አመልካችን አላሰናበትንም ይልቁንም አመልካች ካለበት ዕዳ ለመሸሽ ሲል ስራውን ለቆ በመሄዱ ተጠሪ ላይ ጉዳት ደርሷል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር መርምሮ የስራ ውሉ በአሰሪዉ ስለመቋረጡ ያላስረዳ በመሆኑ ተጠሪ የስራ ውሉ ያላግባብ አቋርጧል ለማለት አልተቻለም በማለት የክፍያ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ያልተከፈለ ደመወዝ እና የዓመት እረፍት እንዲከፈለው ሐምሌ 30 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ያቀረበዉ ይግባኝ ጊዜ አልፎበታል ስለተባለ የይግባኝ ጊዜ ያለፈበት ምክንያት በመግለጽ መስከረም 08 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ አቅርቦ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ይግባኙን በወቅቱ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማቅረብ ያልቻለው የአመልካች ጠበቃ አጋጠመኝ ባሉት እክል ምክንያት በፍቃድ መጠየቂያው ማመልከቻ ላይ የተገለፀው ምክንያት ይግባኙን በጊዜው ለማቅረብ ያልቻለው በአመልካች ጠበቃ ወይም ነገረ ፈጅ ወይም በወኪሉ ያለመቅረብና በነዚሁ ጉድለት መሆኑ የታወቀ እንደሆነ ምክንያቱ እንደበቂ ምክንያት እንደማይወሰድ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 326(2) በህጉ የተመለከተ በመሆኑ ይግባኙ በጊዜ ያልቀረበው በበቂ ምክንያት አይደለም በማለት የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታውን ውድቅ አድርገዋል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበዉ አቤቱታ ይዘት ባጭሩ በሕግ የተፈቀደው የ30 ቀን ጊዜው ሳያልፍ በ26/12/2012 ዓ.ም ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሬጅስትራር የይግባኝ አቤቱታዬን አቅርቤ የስር መዝገብ ግልባጭ እንዲላክ በማህተም አድርጎ ለሥር ፍ/ቤት ተመርቶ፣በዚሁ መሰረት ለስር ፍ/ቤት አቅርቤ በዚሁ ቀን በ26/12/2012 ዓ.ም የመዝገብ ግልባጭ ተሰጥቶኝ በቦርሳዬ አድርጌ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ለማቅረብ ዝግጅት ላይ እያለሁ ከቦርሳዬ ጋር ጠፍቷል፡፡በመሆኑም የይግባኝ አቤቱታዬን አቅርቤ የይግባኝ ፋይል ቁጥር አሰጥቼ የይርጋ ጊዜ አቋርጫለሁ፣በጊዜ ማቅረብ ያልቻኩት የመዝገብ ግልባጩን ነው፣ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት የይግባኝ ጊዜው ሳያልፍ ጊዜው አልፏል፣በቂ ምክንያት አልቀረበም በማለት ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ውሳኔው ተሽሮ ይግባኙን ለማቅረብ እንዲፈቀድልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ዋና ፍርድ የተሰጠው ሐምሌ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ሲሆን ይግባኝ አቤቱታ ያቀረበው ደግሞ ነሐሴ 26 ቀን 2012 ዓ.ም ከመሆኑ አኳያ በወቅቱ ይግባኙ አልቀረበም ሊባል የሚችልበት አግባብ አለው ወይ የሚለው ነጥብ ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡ተጠሪ መጥሪያ ድርሶት መልስ ባለማቅረቡ የጽሁፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉ ክሱ የስራ ዉል መቋረጥ በመቃወም የቀረበ የግል የሥራ ክርክር ሲሆን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ይግባኙ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚገባዉ በሰላሳ ቀን ዉስጥ መሆን እንዳለበት የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 139/3/ይደነግጋል፡፡በተያዘዉም ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የተሰጠዉ በሐምሌ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ሲሆን ይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ያቀረበው ነሐሴ 26 ቀን 2012 ዓ.ም ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ነገር ግን ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የቀረበዉ የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልበጣ እና የይግባኝ ቅሬታ ብቻ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ግልባጭ እንዲቀርብ በሬጅስትራር ጽ/ቤት በመታዘዙ ይህ ተሟልቶ እስኪቀርብ በዚህ ሂደት ጊዜ ያለፈበት ስለመሆኑ መዝገቡ ያሣያል፡፡ከዚህ እንደምንገነዘበዉ አመልካች የይግባኝ ቅሬታዉንና የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ይግባኝ ማቅረቢያ በህጉ የተመለከተዉ ሰላሳ ቀን ሳያልፍ ለይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ማቅረቡን ያሣያል፡፡ይሁን እንጂ የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ግልባጭ ተያይዞ ባለመቅረቡ መዝገቡ ተከፍቶ ለችሎት ሳይቀርብ ጊዜዉ እንዳለፈበት አከራካሪ ባይሆንም የአመልካች ጉድለት ነዉ ተብሎ መወሰዱ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ማየት አስፈላጊ ነዉ፡፡

የፍትሃብሔር ስነ ስርዓት ስለይግባኝ ማመልካቻ ይዘትና አቀራረብ የሚደነግግዉ ክፍል ላይ እንደተመለከተዉ ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ የሰጠዉ ፍርድ ቤት የመዝገብና የፍርድ ግልባጭ ትክክል ግልባጭ ለመሆኑ ታትሞበትና ተፈርሞበት ከይግባኙ ማመልከቻ ጋር ተያይዞ ለይግባኝ ሰሚ ቤት መቅረብ እንዳለበት የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 327/2/ ላይ ተደንግጓል፡፡ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈለግ ለፍርድ ቤቱ አሳዉቆ የይግባኝ ቅሬታዉን አዘጋጅቶ ካቀረበ የፍርዱን እና የመዝገቡን ትክክለኛ ግልባጭ አሟልቶ መስጠት የፍርድ ቤቱ ሃላፊነት መሆኑን ነዉ፡፡ከዚህ አኳያ በፍርድ ቤት ያለዉ አሠናዊ አሰራር ሲታይ የመዝገብ ግልባጭ ወይም መዝገቡ ለይግባኝ ሰሚ ችሎት የሚቀርበዉ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ሲጠየቅ ወይም በችሎት ሲታዘዝ መሆኑን ያሣያል፡፡ይህ አሰራር በአንድ በኩል ከህጉ ጋር የሚጣጣም አለመሆኑን በሌላ በኩል ደግሞ በፍርድ ቤቶች ካለዉ የሥራ ጫና አኳያ የመዝገብ ግልባጭ እስከሚዘጋጅ የይግባኝ ጊዜ እንዳያልፍበት ታስቦ የተዘረጋ አሰራር ከመሆኑ አንጻር ሲታይ በዚህ ሂደት የሚፈጀዉ ጊዜ በተከራካሪ ወገን ጉድለት ነዉ ተብሎ ሊወሰድ የሚገባ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ጉዳዩም በዋናነት መታየት የሚገባዉ የይግባኝ መብት በማያጣብብ ሁኔታ መሆኑን ልብ ይለዋል፡፡ይሁንና የመዝገቡ ግልባጭ ተሟልቶ ለባለጉዳዩ ከተሰጠ ሳይዘገይ ለይግባኝ

ሰሚዉ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡በተያዘዉም ጉዳይ አመልካች የይግባኝ ቅሬታዉንና የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ የይግባኝ ማቅረቢያ ሰላሳ ቀን ሳያልፍበት ለይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ማቅረቡ አከራካሪ አይደለም፡፡ነገር ግን የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ግልባጭ ለመጠባበቅ ተብሎ በዚህ ሂደት ጊዜ ያለፈበት በመሆኑ ለዚህ ዋነኛ ምክንያት የአመልካች ጠበቃ ወይም የባለጉዳዩ ጉድለት ነዉ ሊባል አይገባም፡፡በሌላ በኩል በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ሬጅስትራር ጽ/ቤት ትእዛዝ መሰረት የሥር መዝገብ ግልበጭ ለአመልካች ጠበቃ ከተሰጠ በኋላ ይህ ሰነድ ለይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ እንደጠፋባቸዉ የአመልካች ጠበቃ ያቀረቡትን ምክንያት ተገቢነትና አሳማኝነት ሳይመረምር የጠበቃዉ ጉድለት ነዉ የሚለዉ የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሊከሰት የሚችል እዉነታን ያላገናዘበ በመሆኑ ተገቢ ምክንያት ሆኖ አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የይግባኝ ጊዜ ሳያልፍ የይግባኝ ቅሬታ እና የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ለይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት አቅርበዉ እያለ በፍርድ ቤቱ አሰራር ምክንያት የስር መዝገብ ግልባጭ ተያይዞ ባለመቅረቡ ለተፈጠረዉ መዘግየት ምክንያቱ የአመልካች ወይም የጠበቃዉ ቸልተኝነትና ጉድለት ነዉ በማለት የሥር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ህጉን እና በፍርድ ቤቱ ያለዉ አሰራር ያስከተለዉን ሁኔታ ያላገናዘበ ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1ኛ/የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/256736 ላይ በ09/04/2013ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/ ይህ ዉሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ አስር የስራ ቀን ዉስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል ብለናል፡፡ይጻፍ

**መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 203206

ህዳር 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡-አቶ ወንድወሰን ፍልፍል -- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ወይንሽት ወ/ገብርኤል- አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መሃል ያለውን የአፈፃፀም ክርክር አስመልክቶ የሰጠው ትዕዛዝ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤት መፅናቱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይኸው ስሕተት እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻነት ሲሆን አመልካች በስር ፍርድ ቤት የፍርድ ባለዕዳ የነበሩ ሲሆን ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ነበሩ፡፡

በግራ ቀኙ መሃል ባለው የሰሌዳ ቁጥር 2-38101 አአ መኪናን አስመልክቶ አመልካች ህዳር 09 ቀን 2013 ዓም በተፃፈ አቤቱታ አከራካሪው መኪና አቶ ደጀኔ ዘውዴ ለተባሉ አድራሻቸው ግንደበረት ከተማ ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር 238 ነዋሪ ለሆኑት የተሸጠ መሆኑን ገልፀው የፌደራል ፖሊስ በዚህ አድራሻ ፈልጎ እንዲያመጣ እንዲታዘዝላቸው የጠየቁ ሲሆን ይህንን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ በሰጠው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ትዕዛዝም አመልካች መግለፅ ያለባቸው አሁን መኪናው ያለበትን መሆኑን፤መኪናው ስለመሸጡ ፍርድ ቤቱ በዋናው ውሳኔ ላይም ያልገለፀ መሆኑን፤መኪናው ተንቀሳቃሽ ከመሆኑ አንፃር አመልካች መኪናው ያለበትን የመግለፅ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን መነሻ በማድረግ አመልካች መኪናውን የያዘውን ግለሰብና አሁን ያለበትን ለፌደራል ፖሊስ እንዲያሳዩና ፌደራል ፖሊስም ተሸከርካሪውን በተገኘበት በመያዝ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም መኪናውን ከ7 አመት ከ1 ወር በፊት በ06/05/2006 ዓም በተፈረመ ውል ለአቶ ደጀኔ ዘውዴ ጫላ በሽያጭ አስተላልፌ አስረክቤ እያለ ፤ውሳኔው ሲሰጥም መኪናው በእኔ እጅ ባልነበረበት ፤ገዢው መኪናውን ገዝተው ከተረከቡ በኋላ የት እንደወሰዱት የማውቀው ነገር በሌለበት ፤መኪናውን ማቅረብና ውሳኔውን መፈፀም አለብህ በማለት የተሰጠው ትዕዛዝ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.392(1) እና (2) እንዲሁም በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 69471 እና 29344 የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ የሚፃረር በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች መኪናውን የሸጡ መሆኑንና የሸጡለትንም ግለሰብ አድራሻ ለፍርድ ቤቱ አስረድተው በፖሊስ እንዲቀርብለት እየጠየቁ አመልካች መኪናውን ካለበት እንዲያቀርቡ የታዘዘበትን አግባብ ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስም የፍቺ ክርክሩን በያዘው ፍርድ ቤት መኪናው እንዳይሸጥ ታግዶ ስለነበረ በዚህ ምክንያትም ስም ለማዛወር ስለማይችሉ ሆነ ብለው ቀኑን ወደ ኋላ በማድረግ በጋብቻ ውስጥ እንደተሸጠ በማድረግ ያቀረቡት እንጂ መኪናው ጋብቻ ውስጥ እያለን ያልተሸጠ በመሆኑ፤የመኪናው መሸጥ በዋናው ክርክር ጊዜ ያልተነሳ በመሆኑ አሁን እንደ አዲስ ሊነሳ ስለማይችል፤መኪናው የተሸጠ ከሆነ የጋራ ሀብት ተብሎ ሲወሰን በይግባኝ ያላሻረው ስለሆነ ፤መኪና ተሸጠ የሚባለውም ስመሀብቱ ሲዘዋወር በመሆኑና የመኪናው ስም ያልተዛወረ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፡ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ፍርዱን የሚያስፈፅመው ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈፀም ተስማሚ ነው ብሎ የሚገምተውን ትዕዛዝ የመስጠት ስልጣን ያለው መሆኑን የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.392(1) ያመለክታል፡፡አከራከሪው መኪና መሸጡን ጠቅሰው የገዢውን አድራሻ ጭምር በማመልከት መኪናው በፖሊስ ተፈልጎ እንዲቀርብ ህዳር 09 ቀን 2013 ዓም በተፃፈ አቤቱታ ያመለከቱት አመልካች መሆናቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡አመልካች በዚህ አግባብ አፈፃፀሙ በአከራካሪው መኪና ላይ እንዲቀጥል ካመለከቱ በኋላ መኪናው ያለበትን

አሁናዊ አድራሻ ለፖሊስ እንዲያሳዩ በችሎቱ ሲታዘዙ አመልካች ሀሳባቸውን በመቀየር በመኪናው ላይ ፍርዱ ሊፈፀም አይችልም በማለት የተከራከሩበትን በቂና አሳማኝ ምክንያት በክርክራቸው ላይ አላመለከቱም፡፡

በገዛሁት መኪና ላይ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይገባም በማለት የመከራከሩ ድርሻ መኪናውን በእርግጥም ገዝተው መብታቸውን አረጋግጠው ከሆነ የገዢው ድርሻ ሆኖ እያለ አመልካች መኪናውን ገዝተዋል የሚሏቸውን ሰው አላግባብ በመወከል መኪናው ላይ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይገባም ሊፈፀም የሚችል ፍርድ የለም በማለት ህዳ 09 ቀን 2013 ዓም ካቀረቡት አቤቱታ በተቃራኒ መከራከራቸው አሳማኝ ሆኖ ስላላገኘነው በዚህ አግባብም በአከራካሪው መኪና ላይ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች መኪናው የሚገኝበትን አሁናዊ አድራሻ ለፖሊስ እንዲያመለክቱ ማዘዙና ይህ ትዕዛዝ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መፅናቱ የሚነቀፍ ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ.86371 በቀን 08/03/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው የአፈጻፀም ትዕዛዝና ይህንን ትዕዛዝ በማፅናት የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.257832 ጥር 20 ቀን 2013 ዓም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

**ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**

ማ/አ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 203198
መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ መህቡባ ቢላል- አልቀረቡም ከተባለ በኋላ ጠበቃ አሊ አወል ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ነጃት ቢላል- አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች የካቲት 22 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 107958 ጥቅምት 09 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 260898 ጥር 24 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አዋሳኙ በክሱ የተገለጸው እና በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 ውስጥ የሚገኝ በግምት 200 ካ.ሜ የሚሆን ቤት እና ይዞታ ከአቶ አወል ባሌ ጥር 05 ቀን 1994 ዓ.ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የገዙ መሆኑን፤ በስማቸውም መብረት እና ውሃ አስገብተው የሚጠቀሙበት መሆኑን፤ ተጠሪ እህታቸው ስለሆኑ በ 2007 ዓ.ም ከውጪ ሐገር ሲመጡ በግቢው ውስጥ በሚገኙ ሁለት ክፍል ቤቶች ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ እንዲያርፉበት የፈቀዱላቸው መሆኑን፤ ሆኖም ተጠሪ ቤቱን እንዲለቁ ሲጠየቁ ለመልቀቅ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን እና ይባስ ብለው ሁከት ፈጥራብኛለች በማለት ክስ የመሰረቱባቸው መሆኑን በመግለጽ ቤቱን ለቀው እንዲወጡ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። ተጠሪ ለክሱ መልስ እንዲሰጡ መጥሪያ ተልኮላቸው ስላልቀረቡ ጉዳያቸው በሌሉበት የታየ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የአመልካችን ክስ እና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ሁለት ክፍል ቤቶች ለቀው እንዲያስረክቧቸው የጠዩት ተጠሪ ወደ ቤቱ የገቡት በአመልካች ፈቃድ ለተወሰነ ጊዜ ነው በማለት ነው፤ ሆኖም በመዝገቡ ተከሳሽ የሆኑት ተጠሪ በዚሁ ችሎት በአመልካች ላይ በመ.ቁ 104651 ባቀረቡት ክስ በተሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ለክሱ ምክንያት ወደ ሆነው ቤት የገቡት የካቲት 10 ቀን 1996 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ከአመልካች ላይ ገዝተው መሆኑ ስለተረጋገጠ እና ይህ የሽያጭ ውል ያልፈረሰ በመሆኑ ተጠሪ ቤቱን ለቀው የሚያስረክቡበት የሕግ አግባብ የለም በማለት ወስኗል።

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አቤቱታቸው በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 70/ሀ መሠረት በሌለበት ጉዳዩ የሚታይን ሰው ከሳሽ ካቀረባቸው ማስረጃዎች በቀር ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን የሚጠቅሙ ማናቸውንም ማስረጃዎች አያይም፤ ከመዝገቡ ጋር ያልተያያዙ ማስረጃዎች ተከሳሹ እንዳቀረባቸው ተደርጎ የተከሳሽን መብት በሚጠብቅ መልኩ ውሳኔ ሊሰጥ አይገባም፤ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠው አመልካች ያቀረብኳቸውን ምስክሮች ሳይሰማ እና የሰነድ ማስረጃዎችንም ሳይተች ነው፤ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች  የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ ለክሱ መልስ ሳይሰጡ እና የግራቀኙ ማስረጃ ሳይሰማ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ሊያስረክቡ አይገባም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። አመልካች የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ተልኮላቸው ለመቀበል ፍቃደኛ እንዳልሆኑ ስለተረጋገጠ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል።

የጉዳዩ አመጣጥ  በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

በዚህ ችሎት ትዕዛዝ መሠረት ከቀረቡት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥራቸው 107958 እና 104651 ከሆኑት መዝገቦች ይዘት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ክስ የቀረበብኝ መሆኑን ያወቅኩት በመ.ቁ 104651 ባለን ክርክር በቀረብኩ ጊዜ ነው በማለት በሌሉበት ጉዳያቸው እንዲታይ የተሰጠው ትዕዛዝ እንደነሳላቸው አቤቱታ አቅርበው አቤቱታቸው ውድቅ የተደረገባቸው መሆኑን፤ ክሱ በተሰማበት እለትም አመልካች ተጠሪዋ ቤቱ የራሴ ነው በሚል በዚያው ችሎት በመ.ቁ 104651 ክስ የመሰረቱባቸው መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ያሳወቁ መሆኑን፤ በሁለቱም መዝገቦች የቀረበው ጉዳይ በአንድ ዳኛ

የታየ እና በተመሳሳይ እለት ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑን፤ ተጠሪ ከሳሽ በሆኑበት እና አመልካችም ቀርበው ክርክር በተደረገበት የመ.ቁ 104651 በሆነው መዝገብ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት የያዙት ከአመልካች ላይ ገዝተውት ስለመሆኑ የካቲት 10 ቀን 1996 ዓ.ም የተደረገ የሽያጭ ውል አቅርበዋል፤ የሽያጭ ውሉ በግራቀኙ መካከል የተደረገ እና በአመልካችም የተፈረመ ስለመሆኑ በሽያጭ ውሉ ላይ በእማኝነት የተጠቀሱት ምስክሮች ያስረዱ በመሆኑ አመልካች ተጠሪዋ ቤቱን እንዲለቁ በማለት የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድ ሲል የወሰነ መሆኑን እና ይህንኑ መሠረት በማድረግ ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ በሆነው የመ.ቁ 107958 በሆነው መዝገብ ተጠሪ በቤቱ የገቡት አመልካች እንደሚሉት ለጊዜው ፈቅደውላቸው ሳይሆን የካቲት 10 ቀን 1996 ዓ.ም ከአመልካች ጋር በተደረገ የሽያጭ ውል በመሆኑ ቤቱን ሊለቁ አይገባም በማለት የወሰነ መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ነገር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ምላሽ የሚያስፈልገውም የስረ ነገር ጭብጥ እና ተከራከሪ ወገኖችም ተመሳሳይ ሆነው ጉዳዩ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ቀርቦ በመሰማት ላይ እያለ ሌላው ፍ/ቤት ይህንኑ አንድ የሆነውን ጉዳይ ተቀብሎ ለመከራከር አይችልም በማለት ተመሳሳይ የሆነው ጉዳይ በአንድ ፍ/ቤትም ሆነ በሌላ ፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ክርክሩ ሊቀጥል እንደማይገባ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8(1) ይደነግጋል፡፡ ይኸው ሥርዓት ሳይፈፀም ቀርቶ ተመሳሳይ የሆነውና በተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖች የተነሳው ጉዳይ በተለያየ ክስ አማካኝነት በተለያየ ፍ/ቤት ቀርቦ በመሰማት ላይ የሚገኝ መሆኑ ከታወቀም የክርክሩ ተነጣጥሎ መታየት ለዳኝነት ሥራ አመራር ወይም ለትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ የማይመች ወይም የማይገባ ሆኖ ስለሚገኝ ተጣምሮ መታየት ያለበት ስለመሆኑ የዚሁ ሕግ ቁጥር 11 ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝበናል፡፡ ይህም ክርክሮችን ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት በአፋጣኝ እንዲታዩ ለማድረግ እና ተለያይተው በሚቀርቡ ክሶች ላይ የተጣረሰ እና ውሳኔ እንዳይሰጥ ለማድረግ ስለመሆኑ ከድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ በየፊናቸው ያቀረቡት ክስ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የቀረበ በመሆኑ በሁለቱም መዝገቦች የቀረበው ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 11 መሠረት ተጣምሮ መወሰን ነበረበት፡፡ ሆኖም የስር ፍርድ ቤት ምንም እንኳን በዚሁ መሠረት ሁለቱንም መዝገቦች አጣምሮ ያልወሰነ ቢሆንም ውሳኔዎቹን በተመሳሳይ ቀን የሰጠ እና በአንደኛው መዝገብ የሰጠውን ውሳኔ በሌላው መዝገብ ላይም በምክንያትነት የተጠቀመበት በመሆኑ በሁለቱም መዝገቦች ላይ የሰጣቸው ውሳኔዎች ተመሳሳይ ውጤት ያላቸው ናቸው፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለዚች ችሎት ባቀረቡት ክርክር የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት የሚከራከሩት ተጠሪ ጉዳያቸው በሌለበት የታየ ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤቱ የአመልካችን ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት ሲገባው ከመዝገቡ ጋር ያልተያያዙ ማስረጃዎችን ተጠሪ እንዳቀረቧቸው በማድረግ የተጠሪን መብት በሚጠብቅ መልኩ ውሳኔ መስጠቱ አግባብ አይደለም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ አግባብ የሚከራከሩ ቢሆንም አንድ ፍርድ ቤት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ውሳኔ የሚሰጠው ከሳሽ የሆነው ተከራከሪ ወገን ያቀረበውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ

ሳይሆን ተከሳሹ ቀርቦ በተከራከረ ጊዜ ተከሳሹ ያቀረበውን ማስረጃ ጭምር በመመልከት እንዲሁም ለጉዳዩ አወሳሰን ጠቃሚ መስሎ ሲታየው በክርክሩ ሒደት የተረዳውን እውነታ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ምንም እንኳን ተጠሪ ጉዳያቸው በሌሉበት የታየ ቢሆንም አመልካች ክሱ በተሰማበት እለት ተጠሪዋ በዚያው ችሎት የመ.ቁ 104651 በሆነው መዝገብ ሁከት ተፈጥሮብኛል በማለት ክስ ያቀረቡባቸው መሆኑን ለችሎቱ የገለጹ በመሆኑ እና ተጠሪ አቅርበውታል የተባለው ክስም በዚያው ችሎት የቀረበ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቱ የመ.ቁ 104651 በሆነው መዝገብ ተጠሪ በቤቱ የገቡት አመልካች እንደሚሉት ለጊዜው ፈቅደውላቸው ሳይሆን የካቲት 10 ቀን 1996 ዓ.ም ከአመልካች ጋር በተደረገ የሽያጭ ውል መሠረት ስለመሆኑ የተረጋገጠ እና ይህ የሽያጭ ውል ያልፈረሰ በመሆኑ ተጠሪ ቤቱን ለቀው ሊያስረክቡ አይገባም በማለት መወሰኑ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 107958 ጥቅምት 09 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 260898 ጥር 24 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝበፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

### ትዕዛዝ

- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥራቸው 107958 እና 104651 የሆኑት መዝገቦች ወደ መጡበት ይመለሱ፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ማ/አ**

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 202879

ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች-** ወ/ሮ ዲዮን ማክፋርላን፡- ጠበቃ ለገሠ ቀርበዋል

**ተጠራ-** ላየን ኸርት አካዳሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፡- ነፈጅ ሹሜ አለሙ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ስንብትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች ከሳሽ፣ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን አመልካች በቀን 07/01/2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ተጠሪ እኔ ባለሁበት የስራ መደብ ላይ በተመሳሳይ ለሚሰሩ ሰራተኞች የሐምሌ እና የነሐሴ ደሞዝ ሲከፍል ለእኔ ግን የሚገባኝ ክፍያ ባለመክፈል በፈፀመው ህገ-ወጥ ተግባር ሞራሌ የተነካ በመሆኑ ያልተከፈለኝን የሁለት ወር ደሞዝ፣ የስራ ስንብት ክፍያ ፣ ካሳ፣ ክፍያ በተገቢው ጊዜ ውስጥ ባለመክፈሉ ቅጣት እና የዓመት እረፍት ክፍያ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀው ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በቀን 02/02/2012 ዓ.ም ጽፎ በሰጠው መልስ አመልካች በቀን 26/12/2011 ዓ.ም እና በቀን 04/13/2011 ዓ.ም በፃፉት ኢሜል በራሳቸው ፍቃድ ስራቸውን የለቀቁ ስለመሆኑ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ከቀን 27/12/2011 ዓ.ም በኋላ ስራቸው ላይ ያልተገኙ በመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ አይደለም፤ በዚህም ምክንያት አመልካች የጠየቁትን ክፍያ ለመክፈል አንገደድም፤ ደሞዝን

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በሚመለከት የገንዘብ እጥረት የገጠመን በመሆኑ ምክንያት ሐምሌ ወር በሁለት ጊዜ ክፍያ ከፍለናል፤ የነሐሴ ወርን በሚመለከት አመልካች ያለማስጠንቀቂያ ስራቸውን የለቀቁ በመሆኑ ለእኛ የሚከፈል ነው፤ ይከፈል ቢባል እንኳን በይርጋ ይታገዳል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ለአመልካች በተደጋጋሚ ጊዜ ደሞዝ ባለመክፈል ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ አመልካች የስራ ውላቸውን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጣቸው ህጋዊ ነው፤ የስራ ውሉን መቋረጥ ተከትሎ ያለውን ውጤት በሚመለከት ተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ፣ ካሳ፣ የ14 ቀን የዓመት እረፍት ክፍያ፣ ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት የግማሽ ወር ደሞዝ እና የአንድ ወር ከ15 ቀን ያልተከፈለ ደሞዝ በድምሩ ብር 170,228.50 ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች የስር ፍርድ ቤት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ማቋረጡ የህግ መሠረት ያለው መሆኑን አረጋግጦ እያለ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43 መሠረት ካሳ እንዲከፈለኝ አለመወሰኑ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት ይግባኛቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት በሌላ መዝገብ ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ሁለቱን መዝገቦቹ አጣምሮ ከመረመረ በኋላ አመልከች ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውላቸውን ማቋረጣቸው ተገቢ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ፣ ካሳ እና የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል ሽሮ የዓመት እረፍት ክፍያ፣ ያልተከፈለ ደሞዝ እንዲከፈል እና ክፍያ በመዘግየቱ ምክንያት ቅጣት እንዲከፈል የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ በአመልካች የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ላማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 16/06/2013 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ የሀምሌ እና ነሀሴ ወር 2011 ዓ.ም ደሞዝ ባለመክፈሉ ምክንያት አመልካች የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጤ ተገቢ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 43 መሠረት ካሳ እንዲከፈለኝ አለመወሰኑ እና የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ውሳኔውን ማጽናቱ፤ እንዲሁም ተጠሪ ለሁለት ወር ደሞዝ ያልከፈለ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ድርጊቱ ከሁለት ጊዜ በላይ አልተፈፀመም በማለት ለህጉ የተሳሳተ ትርጉም ሰጥቶ ከህገ-ወጥ ስንብቱ ጋር በተያያዘ ያሉ ክፍያዎች ሊከፈሉ አይገባም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ተጠሪ የወሰደው የስራ ስንብት እርምጃ ህጋዊ ነው የመባሉን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 32(1)(ሐ) አንጻር መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ጥሪ ተደርጎለት በቀን 11/08/2013 ዓ.ም ጽፎ በሰጠው መልስ ደሞዝ በተደጋጋሚ አለመክፈልን በተመለከተ ለአመልካች ያልተከፈላቸው የሐምሌ ወር ደሞዝ ሲሆን ስራቸውን የለቀቁት ደግሞ የነሐሴ ወር ደሞዝ ከመከፈሉ አምስት ቀናት አስቀድመው በመሆኑ ደሞዝ በተደጋጋሚ

አልተከፈላቸውም አያስብልም፤ ድርጊቱ የተደጋገመ ካልሆነ ደግሞ አመልካች የስራ ውላቸውን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጣቸው ህገ-ወጥ በመሆኑ ሊከፈላቸው የሚገባ ካሳም ሆነ የስንብት ክፍያ የለም፤ በዚህ ረገድ በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢነት ያለው በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል። አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተው ተከራክረዋል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካቾችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ከተያዘው ጭብጥ እና ለጉዳዩ እግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመረዉም አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩት የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ ተጠሪ በተደጋጋሚ ለአመልካች ደመወዝ ባለመክፈሉ ምክንያት በመሆኑ እና ይህ መሆኑ ደግሞ የስራ ዉሉ በህገ ወጥ የተቋረጠ ነዉ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በአዋጁ አንቀጽ 43 መሠረት ለተጠሪ ካሳ እንዲከፈል አለመወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነዉ በማለት ነዉ። በሌላ በኩል በግራ ቀኝ መካከል የነበረዉ የስራ ዉል ግንኙነት የተቋረጠዉ በአመልካች አነሳሽነት እንጂ በተጠሪ አለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ አመልካችም ይህን ክደዉ አይከራከሩም። ስለሆነም የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ በተጠሪ ሳይሆን በአመልካች በሆነበት ሁኔታ የስራ ዉሉ በህገ ወጥ መንገድ የተቋረጠ ነዉ በሚል የስራ ዉሉ በአሠሪዉ በህገ ወጥ መንገድ ሲቋረጥ ብቻ ተፈፃሚ የሚሆነዉን የአዋጅ ቁጥር 377/96 (ለክርክሩ መነሻ የሆነ ጉዳይ የተፈጠረዉ አዋጅ ቁጥር 377/96 ተሽሮ በሌላ አዋጅ ከተተካ በኋላ በመሆኑ ተፈፃሚነት ያለዉ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ነዉ) አንቀጽ 43 ድንጋጌ በመጥቀስ አመልካች የሚያቀርቡት ክርክር ዉሉ የተቋረጠበትን ምክንያት እና ህጋዊ ዉጤቱን ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት ያለዉ ሆኖ አልተገኘም።

ይልቁንም ከተያዘዉ ጉዳይ ተፈጥሮ አንፃር መታየት ያለበት ነጥብ በሠራተኛዉ አነሳሽነት የስራ ዉል የሚቋረጥበትን ሁኔታ እና ህጋዊ ዉጤቱ ነዉ። የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 የተመለከተዉን መሠረት በማድረግ ማየቱ ተገቢ ነዉ። ሠራተኛዉ ለአሠሪዉ የ30 ቀን የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የስራ ዉል ማቋረጥ የሚችል በመርህ ደረጃ በአዋጁ የተመለከተ ሲሆን (አንቀጽ 31 ይመለከቷል) ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳያስፈልግ ሠራተኛዉ የስራ ዉሉን ማቋረጥ የሚችልባቸዉንም ሁኔታዎች በአዋጁ በዝርዝር ተመልክተዋል (አንቀጽ 32/1)። ዉጤቱንም ስንመለከት ማስጠንቀቂያ መስጠት አስፈላጊ ከማይሆንባቸዉ ምክንያቶች ዉጪ በሆነ ሁኔታ ሠራተኛዉ ለአሰሪዉ የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ የስራ ዉሉን ያቋረጠ እንደሆነ ከአንድ ወር ያልበለጠ ደመወዙን ለአሠሪዉ ካሳ የመክፈል ሃላፊነት ያለበት ሲሆን፣ በአንፃሩ ማስጠንቀቂያ መስጠት አስፈላጊ የማይሆኑ ሁኔታዎች ናቸዉ ብሎ አዋጁ ከዘረዘራቸዉ ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱ በመፈጠሩ ምክንያት ሠራተኛዉ የስራ ዉሉን ያቋረጠ እንደሆነ አሠሪዉ ለሠራተኛዉ የሦስት ወር ደመወዝ የመክፈል ሃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 41(2) እና 45 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የሚከራከሩት ተጠሪ የሐምሌ እና የነሐሴ ወር ደመወዝ ባለመክፈሉ ስራቸዉን የለቀቁ መሆኑን ነዉ። የስር ከፍተኛ

ፍርድ ፍርድ ቤት ተጠሪ በዚህ ምክንያት ካሳ የመክፈል ሃላፊነት የለበትም በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ ተጠሪ የሐምሌ እና ነሐሴ ደመወዝ አለመክፈሉ በአዋጁ አንቀጽ 32(1/ሐ) መሠረት በተደጋጋሚ ግዴታዉን አልተወጣም የሚያሰኝ አለመሆኑን በመግለጽ ነዉ፡፡ ከላይ እንደተገለጸዉ ሠራተኛ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ ሳይኖርበት የስራ ዉሉን ማቋረጥ ከሚችልባቸዉ ሁኔታዎች እና በዚህም ምክንያት አሠሪዉ ለሠራተኛዉ ካሳ የመክፈል ሃላፊነት እንዲኖርበት ምክንያት ከሚሆኑት ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ አሠሪዉ ግዴታዉን በተደጋጋሚ አለመወጣቱ አንዱ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 32(1/መ) የተመለከተዉ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ይሁንና በተያዘዉ ጉዳይ ለአመልካች ያልተከፈለዉ ደመወዝ የሁለት ወር ሳይሆን የአንድ ወር ተኩል መሆኑ በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ከአዋጁ አንቀጽ 32(1/መ) አንፃር አመልካች ለተጠሪ ደመወዝ የመክፈል በአዋጁ የተጣለበትን ግዴታ በተደጋጋሚ ጊዜ አልተወጣም ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 257553 በቀን 17/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ሠ/ኃ**

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

ሰ/መ/ቁ፡-202872

ቀን፡-30/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡ ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ- ነ/ፊ እሸቱ ወርቅነህ ቀረቡ

ተጠሪ ፡ ወ/ሮ ሰብለ ሙሉነህ- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የስራ ዉል መቋረጥ የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ፤ የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ከመዝገቡ እንደሚታየዉ የተጠሪ ክስ የሚለዉ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከፍተኛ የህዝብ አገልግሎት ሀላፊ ሆኜ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 15,304 እየተከፈለኝ እየሰራሁ እያለ በህገ ወጥ መንገድ በቀን 15/11/2011 ዓ.ም ከስራ ያሰናበተኝ ስለሆነ ወደ ስራዬን እንዲመልሰኝ ወይም በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሰረት ክፍያዎች እንዲከፍለኝ በማለት ዳኝነት የጠየቀች ሲሆን አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ደንበኞች ያላመጡትን ሂሳብ እንዳመጡ በማድረግ የሌላቸውን የሂሳብ ሚዛን ወይም ቀሪ ሂሳብ በመፃፍ የማይገባቸውን ጥቅም እንዲያገኙ አድርጋለች፣እንዲሁም ይህንን የድርጅት ሰነድ አስመስላ በመስራት የወንጀል ድርጊት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ፊጽማለች፣በአጠቃላይ ወደ ባንኩ የመጣ ገንዘብ እና ከባንኩ የወጣ ገንዘብ በሌለበት በአየር ላይ የገቢና የወጪ ገንዘብ እንዳላቸው በማስመሰል ጽፋላቸዋለች፡፡ስለዚህ ባንኩ ማግኘት ያለበት ጥቅም ለሶስተኛ ወገን ጥቅም እንዲውል አድርጋለች፣ይህ ደግሞ በአዋጅ ቁ/1156/2011 አንቀጽ 27/1/መ መሰረት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል እንዲቋረጥ የሚያደርግ ጥፋት በመሆኑ ተጠሪ የተሰናበተችዉ በህጋዊ መንገድ በመሆኑ የካሳ፣ የአገልግሎት፣ የማስጠንቀቂያ እና ሌሎች ክፍያዎች አይከፈላትም፣ ሌሎች በአንቀጽ 36 እና 38 የተጠየቀው ክፍያ ክሊራንስ ካጠናቀቀች በኋላ የሚከፈል ክፍያ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ገንዘብ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው በሂሳብ ቁጥር እና በጥሬ ገንዘብ ስታስተላልፍ በባንኩ ውስጥ ያለው ገንዘብ እንዳልጎደለ አዲተሩ ገልፅዋል፣የግራ ቀኝ ማስረጃም አረጋግጧል፣ገንዘብ ወዲህ ወዲያ በመተላለፉ ምክንያት ሃላፊው ለግለሰብ ደብዳቤ ጽፏል ለተባለው ተጠሪ ደብዳቤ ለመፃፍ ስልጣን እንደሌላት ተረጋግጧል፡፡ስለዚህ አመልካች ያለጥፋት ተጠሪን ከስራ በህገ ወጥ መንገድ አሰናብቷል በማለት ወደ ስራዋ እንዲመልሳት ወይም ወደ ስራ የማይመልሳት ከሆነ ደግሞ ውዝፍ ደመወዝ፣የአገልግሎት ክፍያ፣የ2011ዓ.ም ቦነስ፣ የ33 ቀናት የዓመት እረፍት፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የካሳ ክፍያ፣ክፍያ ለዘገየበት እና ካዝና መጠባበቂያ ገንዘብ በድምሩ ብር 461,346.09 እንዲከፈላት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዳማ ከተማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካች ያቀረበው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች አዲት አድርገው ያገኙት ውጤት ተጠሪ ገቢ ያልሆነ ገንዘብ በአየር ላይ ገቢ እንደሆነ ጽፋ በደንበኛ ሂሳብ ላይ እንዲታይ ካደረገች በኋላ ወደ ሌላ ደንበኛ ስም እንዲዛወር ያደረገች መሆኑና ተጠሪ ይህንንም ያደረገችዉ በሃላፊዋ በተመራው መሰረት መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም ከድርጅቱ ደንብና መመሪያ ዉጪ በመሆኑ ሃላፊነት የሚያስከትል መሆኑን፤የአመልካች ስራ የንግድ ስራ ከመሆኑ አንፃር ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልግና መልካም ስም ለማትረፍ በደንበኞች ዘንድ ታማኝ ሆኖ ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት ትልቁ አላማ ሆኖ እያለ ተጠሪ የአሰሪና ሰራተኛ ህግና የመ/ቤቱ ደንብ ተቃራኒ በሆነ መልኩ የፈፀመች መሆኑ ስለተረጋገጠ በአዋጅ ቁ/1156/2011 አንቀጽ 27(1)መ መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለመሰናበት በቂ ምክንያት ነው፣ ስለዚህ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ሌሎች ከፍያዎች ውድቅ በማድረግ የተጠራቀመ ፕሮቪደንት ብር 130,000.00 የመጠባበቂያ ገንዘብ ብር 36,507.47፣ ያልተጠቀመችበት የአመት እረፍት የ13.36 ቀን ብር 6,815.38 በአጠቃላይ ብር 173,322.85

ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በክፍያ ረገድ ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፤የተጠራቀመው ጠቅላላ የፕሮቪደንት ፈንድ ድምር ብር 121,203.35 ሆኖ እያለ ተጠሪዋ የጠየቀችውን ብር 130,000.00 እንዲከፈል መወሰኑ ስህተት በመሆኑ ሊስተካከል ይገባል፣በተጨማሪም ሰበር ችሎት በመ/ቁ102994 በሆነ ፋይል ላይ እንደወሰነዉ በስነ-ምግባር ምክንያት ከስራ ለተሰናበተ ሰራተኛ የሚከፈል ፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ሰራተኛዉ ራሱ ያዋጣው ገንዘብ ብቻ በመሆኑ የተጠሪ መዋጮ ብር 30,300.84 ሲሆን ይህ ገንዘብ ደግሞ ስለተከፈላት በዚህ ረገድ የሚከፈላት ክፍያ የለም ተብሎ እንዲስተካከል፣የአመት እረፍት በተመለከተ የ33.36 ቀናት ክፍያ የተከፈላትና በፍ/ቤት ትዕዛዝ የቀረበው ማስረጃ 20 ቀናት የአመት እረፍት በብልጫ እንደወሰደች ተረጋግጦ እያለ የ20 ቀናት ብቻ እንደተከፈለ በማየት ልዩነቱ የ13.36 ቀናት እንደገና እንዲከፈል የሰጠው ውሳኔ ስህተት በመሆኑ እንዲታረምልን፣የተከፈለው ብር 30,300.84 የፕሮቪደንት ፈንድ እንጂ የቦነስ ክፍያ አይደለም፣ተጠሪ ባጠፉችው ጥፋት ከተሰናበተች በኋላ ስለተፈቀደው ቦነስ ሊከፈላት አይገባም ተብሎ እንዲታረም በማለት አመልክቷል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች የአመት ዕረፍት ክፍያ የተከፈላት ስለሆነ በድጋሚ ሊከፈላት አይገባም እያለ ይህ ሳያጣራ በድጋሚ ይከፈል ተብሎ የተወሰነበት አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት መልስ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ በተመለከተ የሚጠራቀመው ለሰራተኛ ጥቅም ሲሆን መከፈል ያለበት መሆኑ በስር ፍ/ቤት በማስረጃ ተረጋግጦ የተወሰነ መሆኑን፣ሰበር ችሎቱ የህግ ስህተት ማረም እንጂ የማስረጃ ምዘና ስልጣን እንደሌለዉ፣የአመት እረፍት በተመለከተ ያልተከፈለኝ የ33 ቀን ነው ብዬ ክስ ያቀረብኩ ሲሆን ፍ/ቤቱ ከማህደር ጭምር በማጣራት ቀሪ የ13.36 ቀን ያልተጠቀምኩበት የአመት እረፍት እንዳለኝ አጣርቶ እና አረጋግጦ ውሳኔ የሰጠበት ጭብጥ በመሆኑ የተፈፀመ ስህተት የለም፤ቦነስ ክፍያም ለሁሉም ሰራተኞች ተከፍሎ ለእኔ የሚከለከልበት ምክንያት የለም፤አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን የቀረበዉን አቤቱታ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ በተጠሪ ጥፋት ስለመሆኑ ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በይግባኝ የተለወጠ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ስለዚህም ስንብቱ ህጋዊ ነዉ የተባለዉ ተጠሪ በስራ ላይ የፈጸመችዉን ጥፋት መሰረት በማድረግ መሆኑን መዝገቡ ያሣያል፡አሁን እያከራከረ ያለዉ ስንብቱ ህጋዊ ነዉ መባሉን ተከትሎ የተወሰነዉ ክፍያ አግባብነት ያለዉ መሆን አለመሆኑ ላይ ነዉ፡፡

የስራ ዉል ሲቋረጥ ለሰራተኛዉ የሚከፈሉት ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንደነገሩ ሁኔታ ማለትም የስራ ዉሉ እንደተቋረጠበት ምክንያት የሚለያይ መሆኑን ከአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሰረታዊነት የሚታየዉ ዉሉ የተቋረጠበት አግባብና ህጋዊ ዉጤቱን በመመርመር ነዉ፡፡የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 36፣39፣42 እና 43 ድንጋጌዎች እንደሚያስገነዝቡን የስራ ዉሉ ሲቋረጥ ለሰራተኛዉ የሚከፈለዉ ክፍያ ዓይነት እና መጠን የሚወሰነዉ በዋነኛነት በአዋጁ በተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሆን በተጨማሪነት በህብረት ስምምነት ወይም በድርጅቱ የሥራ ደንብ እንደሁም የስራ ዉሉ የሚያስገኝለትን መብትና ጥቅም ካለ ይህንኑ በማገናዘብ ነዉ፡፡በተያዘዉ ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት እንደተረጋገጠዉ የስራ ዉል የተቋረጠዉ ተጠሪ በስራ ላይ በፈጸመችዉ ጥፋት በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነዉ ስለተባለ ዉጤቱም ከዚህ አኳያ የሚወሰን ነዉ፡፡እንዲህ በሆነ ጊዜ ለሰራተኛዉ የሚከፈል ክፍያ እንደነገሩ ሁኔታ ስራ ላይ እያለ ያልተከፈለ ደመወዝ፣ያልተጠቀመበት የዓመት እረፍት እና በድርጅቱ ህብረት ስምምነት ወይም የስራ ደንብ ወይም የሥራ ዉል የተፈቀዱ ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች መኖራቸዉ ሲረጋገጥ በዚሁ አግባብ የሚፈጸም ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 4/5/፣ 36፣ 77/4/ እና 135 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚህም ጉዳይ ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ለተጠሪ የወሰነዉ ክፍያ ያልተጠቀመችበት የዓመት እረፍት የ13.36 ቀን፣ የተጠራቀመ ፕሮቪደንት ፈንድ እና የካዝና መጠባበቂያ የሚሉት ናቸዉ፡፡ቦነስን በሚመለከት የ2011ዓ.ም ብር 30,300.84 የተከፈላት መሆኑ ተረጋግጧል በሚል የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሻሩን የዉሳኔዉ ይዘት ያሣያል፡፡አመልካች አሁንም እነዚህ ክፍያዎች በዓይነትም በመጠንምተገቢ አይደሉም በማለት ተከራክሯል፡፡በዋናነት የዓመት እረፍት፣የፕሮቭደንት ፈንድ እና የቦነስ ክፍያ ላይ ያቀረበዉን አቤቱታ በቅደም ተከተል መርምረናል፡፡

የመጀመሪያዉ የዓመት እረፍት ክፍያ የሚመለከት ነዉ፡፡በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ/1156/11 አንቀጽ 77/5/ እንደተደነገገዉ የሥራ ዉሉ በሚቋረጥበት ጊዜ ሰራተኛዉ ያልተቀመበት የአመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተለዉጦ እንደሚከፈለዉ ተመልክቷል፡፡ተጠሪም ያልተጠቀመችበት 33.36 ቀናት የዓመት ወደ ገንዘብ ተለዉጦ እንዲከፈላት ዳኝነት መጠየቋን መዝገቡ ያሣያል፡፡ በዚህ ረገድ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የ13.36 ቀናት ብቻ የወሰነላት ቢሆንም አመልካች ይህ ገንዘብ ከደመወዝ ጋር የተከፋላት መሆኑንና የ20 ቀናት በእላፊ መዉሰዷን አስመልክቶ ያቀረበዉ ክርክር ሳይመረመር የ13.36 ቀናት እንዲንከፍል መወሰኑ ስህተት ነዉ የሚል አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪ በበኩሏ ፍርድ ቤቱ በማስረጃ አጣርቶ ዉሳኔ መስጠቱን ገልጻ ተከራክራለች፡፡ከክርክሩ እንደሚታየዉ ተጠሪ ያልተጠቀመችበት የአመት እረፍት ምን ያህል ነዉ? ለዚህ የተከፈለ ገንዘብ አለ ወይስ የለም? የሚለዉ የፍሬነገር ክርክር ጉዳይ ነዉ፡፡ከዚህ አኳያ ፍሬነገር የመመርመርና በማስረጃ የማጣራትና የመመዘን ስልጣን ያለዉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተጠሪን ማህደር ጭምር በማስቀረብ ያልተጠቀመችበት የዓመት እረፍት 13.36 ቀን ብቻ መሆኑን አረጋግጧል፡፡በዚህም ልክ ወደ ገንዘብ ተለዉጦ ብር 6,815.38 እንዲከፈላት መወሰኑን ተገንዝበናል፡፡ይህንን ፍሬነገር ክርክር ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት አጣርቶ ዉሳኔ የሰጠበት መሆኑን ዉሳኔዉ ይዘት በግልጽ ያሣያል፡፡ሰበር ችሎቱ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ የመመርመር ስልጣን የለዉም፡፡በእርግጥ በማስረጃ አቀባበል እና ምዘና ረገድ ቅቡልነት ያላቸዉ መርሆዎች ጥሰት ሲኖር ይህንኑ የማረም ጉዳይ ይመለከቷል፡፡በዚህ ጉዳይ ግን የስር ፍርድ ቤት የተጠሪን የግል ማህደር ጭምር በማስቀረብ ያልተጠቀመችበት 13.36 ቀን የዓመት እረፍት እንዳላት ከድምዳሜ የደረሰ መሆኑን ስለተገነዘብን በዉሳኔዉ ላይ የማስረጃ አቀባበል ወይም ምዘና መርህ ጥሰት ተፈጽሞበታል የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

ቀጥሎ መታየት ያለበት ጉዳይ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ነዉ፡፡ለተጠሪ የፕሮቭደንት ፈንድ ክፍያ መብት አመልካች ለሰራተኞች ያደረገዉ የጥቅማ ጥቅም ባኬጅ የዘረጋዉ ስርዓት ስለመሆኑ በአመልካችም የታመነ ጉዳይ ነዉ፡፡ይሁንና የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ በተጠሪ ጥፋት ስለሆነ ሊከፈል የሚገባዉ ሰራተኛዉ ያጠራቀመዉ ፕሮቭደንት ገንዘብ መጠን ብቻ ነዉ በማለት የጥቅማ ጥቅም ፓኬጁን እና ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/102994 ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ ድጋፍ በማድረግ ተከራክሯል፡፡በመሰረቱ የሥራ ዉሉ በሰራተኛዉ ጥፋት ሲቋረጥ አሰሪዉ የሚከፍለዉ የፕሮቪደንት ፈንድ መጠን አመልካች እንደሚለዉ ሰራተኛዉ ያጠራቀመዉ ብቻ ነዉ ወይሥ ከሁለቱም ወገን የተሰበሰበዉ ነዉ?የሚለዉን ጥያቄ ለመመለስ የጥቅማ ጥቅም ፓኬጁን ይዘት

በመመርመር ነዉ፡፡በዚህ ረገድ የክፍያዉ መጠን አስመልክቶ የቀረበዉን ክርክር ፍርድ ቤቱ ከጥቅማ ጥቅም ፓኬጁ ይዘት አንጻር ስለመመርመሩ መዝገቡ አያሣይም፡፡ስለዚህም የሥራ ዉሉ በተጠሪ ጥፋት መቋረጡ ከግምት ዉስጥ ገብቶ በፕሮቭደንት ፈንድ ክፍያ መጠን ላይ የሚኖረዉ ዉጤት ምንድነዉ? የሚለዉ ጭብጥ መጣራት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡በዚህ ረገድ የቀረበዉ ክርክር ተገቢነት ያለዉ መሆን አለመሆኑ ሳይጣራ መታለፉ የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት መሆኑን ያሣያል፡፡ይህ ጉዳይ ሳይጣራ ደግሞ ድምዳሜዉ ተገቢ ነዉ ወይም አይደለም ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘንም፡፡ስለዚህም ፕሮቭደንት ፈንድ ክፍያን በተመለከተ ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባዉ የገንዘብ መጠን ከሁለቱም ወገን የተሰበሰበዉ ገንዘብ ባጠቃላይ ነዉ ወይስ ከተጠሪ ደመወዝ ተቀንሶ የተጠራቀመዉ ብቻ ነዉ? መጠኑስ ምን ያህል ነዉ? የሚለዉ በስር ፍርድ ቤት ክርክር ተደርጎ በማስረጃ ተጣርቶ ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡

የመጨረሻዉ የቦነስ ክፍያ የሚመለከት ነዉ፡፡ከክርክሩ እንደተገነዘብነዉ ተጠሪ ሥራ ላይ በነበረችበት 2011.ዓ.ም ድርጅቱ ሌሎች ሰራተኞች ቦነስ ስለከፈለ ድርሻዋ እንዲከፈላት የጠየቀች ሲሆን የሥር ፍርድ ቤትም ቦነስ እንዲከፈላት ወስኗል፡፡በዚህ ላይ በአመልካች በኩል የቀረበዉ ክርክር ቦነስ እንዲከፈል የተደረገዉ ባንኩ ባለዉ የሰራተኛ ጥቅማ ጥቅም ፓኬጅ መሰረት ስለመሆኑና በባንኩ ቦርድ ዉሳኔ መሰረት ቦነስ ከመከፈሉ በፊት ስራ የለቀቀ ሰራተኛ ቦነስ የማግኘት መብት የለዉም የሚለዉን የስር ፍርድ ቤት አልመረመረም የሚል ነዉ፡፡በእርግጥ ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ቦነስ አይገባትም ወይም ይገባታል የሚል ጭብጥ ሳይመረምር ቦነስ ብር 30, 30,300.84 ለተጠሪ ተከፍሏል በሚል የወሰነ ቢሆንም የአመልካች አቤቱታ እንደሚያሣዝን ይህ ገንዘብ ቦነስ ሳይሆን ተጠሪ ያጠራቀመችዉ የፕሮቭደንት ፈንድ ነዉ ይላል፡፡በዚህ ረገድ የከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ስርዓቱን ጠብቆ የሚታረም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆነ ቦነስ ለተጠሪ ሊከፈል ይገባል ወይስ አይገባም የሚለዉ ነጥብ ከጥቅማ ጥቅም ከፓኬጁ አንጻር መታየት አለበት፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ የቦነስ ክፍያ መሰረቱ በድርጅቱ የጥቅማ ጥቅም ፓኬጅ ለሰራተኛዉ የተፈቀደ ጥቅም ስለሆነ አከፋፈሉን በሚመለከት በፓኬጁ የተመለከተ ሁኔታ ካለ ክርክሩ ከዚህ አኳያ ተመርምሮ ዉሳኔ ሊሰጥበት ይገባል ማለት ነዉ፡፡ይህ ሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ጉዳዮች በሰጠዉ ዉሳኔ እንዳመለካተዉ የቦነስ ክፍያ ዓላማ ሰራተኛዉን ይበልጥ ለማትጋትና ምርታማነቱን ለማሳደግ በመሆኑ ቦነስ ክፍያ ሳይቀበል ስራ የለቀቀ ሰራተኛ የመብቱ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ አከራካሪ ከሆነ ከዉሉ አንጻር መታየት የሚገባዉ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ስለሆነም ለተጠሪ የ2011ዓ.ም የቦነስ ክፍያ የሚገባት መሆን አለመሆኑን

ለመወሰን የድርጅቱን የጥቅማ ጥቅም ፓኬጅ እና የቦርዱን ዉሳኔ ይዘት መመርመር ነበረበት፡፡ፍርድ ቤቱ ክርክሩን ከዚህ አንጻር ሳይመረምር ማለፉ ስነስርዓታዊ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡

ሲጠቃለል ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ክርክሩን መርምሮ የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ በተጠሪ ጥፋት ነዉ በሚል ስንብቱ ህጋዊ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ከፍል ላይ ቅሬታ የቀረበበት አይደለም፡፡ሆኖም ክፍያን አስመልክቶ የፕሮቭደንት ፈንድ አከፋፈልና መጠኑን እንዲሁም የቦነስ ክፍያ አይገባትም በማለት አመልካች ያቀረባቸዉ መከራከሪያ ነጥቦች በአግባቡ ሳይመረመር እና ሳይጣራ ዉሳኔ መስጠቱን ስለሚያሣይ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ሌላዉ ተጠሪ ያልተጠቀመችበት የዓመት እረፍት በገንዘብ ተለዉጦ ብር 6,815.38 እና የካዝና መጠባበቂያ ብር 36,507.47 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፈል የተወሰነዉ ማስረጃን እና ህጉን መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አልተገኘም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1ኛ/በዚህ ጉዳይ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/35516 ላይ በ14/05/2013ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህንኑ በማጽናት የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/335005 ላይ በ21/05/2013ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ/ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የዓመት እረፍት እና የካዝና መጠባበቂያ ለተጠሪ እንዲከፈል የሰጠዉ ዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡

3ኛ/የፕሮቭደንት እና ቦነስ ክፍያን በተመለከተ ከላይ በፍርድ ሀተታ ላይ በተገለጸዉ አግባብ ግራቀኙን በማከራከርና በማስረጃ በማጣራት ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 343/1/ መሰረት ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሰናል፡፡

4ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**<u>መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡</u>**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ ሂ/መ

ማነታወሸ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 202839

ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመካው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡ አቶ ሰለሞን አሰፋ- አልቀረቡም

ተጠሪዎች ፡ ቡና ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር -ነ/ፈጅ ቁምነገር ካሣሁን -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የስራ ውል ከተቋረጠ በኋላ የተወሰነ የቦነስ ክፍያ ይከፈለኝ በሚል የቀረበ የአሰሪ እና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ጥር 28 ቀን 2011 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ክስ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በስራ አስፈጻሚነት ስሰራ ቆይቼ የ2010 በጀት አመት ከተጠናቀቀ በኋላ የስራ ውሌን አቋርጫለሁ፡፡ ተጠሪ የ2009 እና የ2010 ዓ.ም.

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቦነስ የሁለት ወር ደመወዝ ለሰራተኞቹ ከፍሏል። እኔም ለተገኘው ውጤት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስለነበረኝ የሁለት ወር ደመወዜን ብር 38,992 ተጠሪ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል።

ተጠሪም መጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ ነሐሴ 8 ቀን 2010 ዓ.ም. ተጠሪ የሰራተኞች ቦነስ እና አመታዊ የደመወዝ ጭማሪ አፈጻጸም መመሪያ አውጥቷል። በዚህ መመሪያ ላይ የቦነስ ክፍያ የሚፈጸመው በስራ ላይ የሚገኙ ሰራተኞችን ይዞ ለማቆየት መሆኑ ተመልክቷል። የተጠሪ ቦርድም ነሐሴ 21 ቀን 2010 ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ቦነስ ከስራ ለለቀቀ ሰራተኛ እንደማይከፈል በቃለ ጉባኤ ወስኗል። በመሆኑም አመልካች የቦነስ ክፍያው በሚፈጸምበት ጊዜ ከስራ የለቀቁ በመሆኑ የቦነስ ክፍያው አይገባቸውም በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪ ቦነስን በተመለከተ አለ የሚለው መመሪያ በዳይሬክተሮች ቦርድ የጸደቀ ባለመሆኑ ተፈጻሚነት የለውም። በቦርድ አባላት በቃለ ጉባኤ የተወሰነውም ከስራ የለቀቁ ሰራተኞች ቦነስ እንደማይከፈላቸው በግልጽ የሚያመለክት አይደለም። በመሆኑም ለአመልካች ቦነስ እንዳይከፈል በግልጽ የሚከለክል ህግ ስለሌለ ለአመልካች ብር 38,992 ከወለድ፣ ወጪ እና ኪሳራ ጋር ይከፈላቸው በማለት ወስኗል። ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የተጠሪ ቦርድ የስራ ውሉ የተቋረጠ ሰራተኛ ቦነስ እንደማይከፈለው ወስኗል። የስር ፍርድ ቤት አጠቃላይ የቃለ ጉባኤውን ይዘት ሳይመለከት ቃለ ጉባኤው ለአመልካች ተፈጻሚ አይሆንም ማለቱ ተገቢ አይደለም። በመሆኑም የአመልካች የስራ ውል ቦነስ ከመከፈሉ በፊት ስለተቋረጠ የተጠሪ ቦርድ በቃለ ጉባኤ በወሰነው መሰረት የቦነስ ክፍያ አይገባቸውም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሯል።

አመልካች በየካቲት 15 ቀን 2013 ዓ.ም. የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረቡት ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ሲሆን ይዘቱም የተጠሪ ቦርድ ከስራ ለለቀቀ ሰራተኛ ቦነስ ሊከፈለው አይገባም በሚል የውሳኔ ሀሳብ ቀርቦለት የተወያየ ቢሆንም በቃለ ጉባኤው የውሳኔ ኃሳቡን አላጸደቀውም። ስለዚህ ቃለ ጉባኤው እንዳይከፈለኝ ስለማይከለክል የይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ይታረምልኝ የሚል ነው።

የሰበር አጣሪ ችሎትም የአመልካችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ አመልካች ስራ የለቀቁት ቦነስ ከመከፈሉ በፊት ነው በሚል ሊከፈላቸው አይገባም የተባለበትን አግባብ የዳይሬክተሮች ቦርድ በነሀሴ 12 ቀን 2010 ዓ.ም. በቃለ ጉባኤ ከወሰነው አንጻር ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል።

ተጠሪ በሐምሌ 28 ቀን 2013 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ የተጠሪ ቦርድ ነሐሴ 12 ቀን 2010 ዓ.ም. በቃለ ጉባኤ ከስራ የለቀቀ ሰራተኛ ቦነስ እንደማይከፈለው ወስኗል። አመልካች በራሳቸው ፍቃድ ከስራ ለቀው እያለ ቦነስ እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው ከቦነስ ክፍያ አላማ እና መንፈስ ውጪ ነው። ስለዚህ በይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል።

አመልካችም በጥቅምት 5 ቀን 2014 ዓ.ም. ተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በስር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ተገቢነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች የጠየቁትን የቦነስ ክፍያ ተጠሪ ልከፍል አይገባም በማለት የሚከራከረው የተጠሪ ቦርድ ነሐሴ 12 ቀን 2010 ዓ.ም. በቃለ ጉባኤ ከስራ የለቀቀ ሰራተኛ ቦነስ እንደማይከፈለው ወስኗል፡፡ አመልካችም የቦነስ ክፍያ ተወስኖ ከመፈጸሙ በፊት ከስራ ለቀዋል በሚል ነው፡፡ አመልካችም የቦነስ ክፍያው እንዲከፈል በተጠሪ የተወሰነው የስራ ውላቸው ከተቋረጠ በኋላ መሆኑን ክደው ያልተከራከሩ ሲሆን አጥብቀው የሚከራከሩት ተጠሪ የሚጠቅሰው ቃለ ጉባኤ ቦነስ እንዳይከፈለኝ የሚከለክል አይደለም በሚል ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ የተገለጸው ቃለ ጉባኤ የስራ ውሉ ለተቋረጠ ሰራተኛ ለሰራበት ጊዜ የተከፈለ ቦነስ እንዳይከፈል የሚከለክል አይደለም የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ በተቃራኒው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠቀሰው ቃለ ጉባኤ አጠቃላይ ይዘት ሲታይ ከስራ የለቀቀ ሰራተኛ ቦነስ እንደማይከፈለው መወሰኑን ያመለክታል የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ስለዚህ ዋናው በዚህ ሰበር ችሎት እልባት ማግኘት ያለበት ጉዳይ ነሐሴ 12 ቀን 2010 ዓ.ም. የተጠሪ ቦርድ በቃለ ጉባኤ ከስራ የለቀቀ ሰራተኛ ቦነስ እንደማይከፈለው ወስኗል ወይስ አልወሰነም? የሚለው ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የተጠቀሰውን ቃለ ጉባኤ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ያደረገ በመሆኑ እኛም ቃለ ጉባኤውን ተመልክተናል፡፡ እንደተመለከትነው በቃለ ጉባኤው 3ኛ ገጽ ውሳኔ ከሚለው አርእስት ከፍ ብሎ እስከ በጅት አመቱ መጨረሻ ያገለገሉ ሰራተኞች ቦነስ ለምን ይከለከላሉ የሚል ሀሳብ ተነስቶ የቦነስ አላማ በስራ ላይ ያሉ ሰራተኞችን ለማበረታታት ስለሆነ በስራ ላይ ለሌሉ ሰራተኞች ቦነስ መክፈል ጥቅም የለውም በሚል ቦነሱ እስከሚከፈልበት ድረስ ከስራ የለቀቁ ሰራተኞች ቦነስ እንደማይከፈላቸው መወሰኑን ተገንዝበናል፡፡ በእርግጥ በቃለ ጉባኤው ውሳኔ በሚል አርእስት ስር ከተጠቀሱ ውሳኔዎች ውስጥ ቦነስን የሚመለከት ውሳኔ የለም፡፡ ይህ ማለት ግን ውሳኔ ተብሎ አርእስት ባይሰጠውም ወይም ውሳኔ ከሚለው አርእስት በላይ ባለው የቃለ ጉባኤው ክፍል ቦነስን የሚመለከት ውሳኔ ከተቀመጠ ተፈጻሚነት አይኖረውም ወይም እንደተወሰነ ሊቆጠር አይገባም ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም የቃለ ጉባኤው አጠቃላይ ይዘት ሲታይ በስራ ላይ ለሌለ ሰራተኛ ቦነስ እንደማይከፈለው የተወሰነ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ቃለ ጉባኤው የቦነስ ክፍያን አይመለከትም በሚል የደረሰበትን መደምደሚያ ማረሙ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ቦነስ ከአሠሪዉ ለሠራተኛዉ በጉርሻ መልክ የሚከፈል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 53(2/ሐ) ላይ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አከፋፈሉ የሚመራዉ በአሠሪዉ በሚዘረጋዉ ሥርዓትና

ደንብ ሲሆን አሠሪው ለዚህ ዓላማ በሚያወጣው ደንብ/መመሪያ የቦነስ ክፍያ የሚፈጸምበትን ቅድመ ሁኔታ እንዲሁም የክፍያው አፈፃፀም በሠራተኛው ላይ የሚያስከትለውን ልዩ ግዴታ ጭምር ያካተተ ሊሆን ይችላል፡፡ በህብረት ስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር የቦነስ ክፍያ በአሠሪው መልካም ፈቃድ የሚፈጸም እንጂ በአሠሪው ላይ በህግ የተጣለ የክፍያ ግዴታ ባለመሆኑ የክፍያውን አፈፃፀም እንዲሁም የሚያስከትለውንም ህጋዊ ውጤት አስመልክቶ በዚህ መልኩ አሠሪው የሚያወጣው ደንብ/መመሪያ/የቃለ ጉባኤ ውሳኔ ወይም ከሠራተኛው ጋር የሚደረግ ስምምነት ካለ ህጋዊ ውጤት ተሰጥቶት እንደየአግባብነቱ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባው እንጂ እንደ ሌሎች የሠራተኞች መሠረታዊ መብቶች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ላይ ከተመለከቱት ዝቅተኛ መስፈርቶች (minimum standards) አንፃር ታይቶ ውጤት እንዲኖረው ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የቦነስ ክፍያ የጠየቁት በስራ ላይ ለነበሩበት ጊዜ የተከፈለውን ቢሆንም የቦነስ ክፍያው በተጠሪ ተወስኖ ተፈጻሚ የተደረገው አመልካች ከስራ ከለቀቁ በኋላ በመሆኑ እና ከስራ የለቀቀ ሰራተኞ ቦነስ እንደማይከፈለው የተጠሪ ቦርድ በቃለ ጉባኤ የወሰነ በመሆኑ ለአመልካች የቦነስ ክፍያው ሊከፈላቸው አይችልም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ለአመልካች እንዲከፈል የወሰነውን የቦነስ ክፍያ በመሻሩ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሌለ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1ኛ. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 243556 በህዳር 16 ቀን 2013 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**ማ/አ**

**የማይነበብ የአምስት ደኞች ፊርማ አለበት**

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

??/? /??? 202810
?? 27/3/2014 ?/?

-ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - ወ/ሮ ደቡብ ገ/ጊዮርጊስ -ቀረቡ

ተጠሪ - አቶ ታደሰ ወልዴ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች የካቲት 9 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 247029 ታህሳስ 2 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር180038 ሐምሌ 10 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታዋን በማቅረቧ ነው፡፡ ቅሬታዋም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የምትቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የምትለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤት የመንግስት ቤት ከጋብቻ በፊት እንደተገኘ የግል ንብረቶች ተቆጥሮ ልትካፈል አይገባም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን አመልካች ባቀረበችው ክስ ከተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ጋር የነበረን ጋብቻ በ30/4/2011 ዓ/ም ፈርሷል፡፡ ከተከሳሽ ጋር በጋብቻ ውስጥ በጋራ ያፈራናቸው ንብረቶች ከ1 እስከ 59 ድረስ የቤት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እቃዎች ዘርዝራ የጋራ ንብረታችን በመሆኑ ያካፍለኝ 2. መኪና የሰ/ቁጥር 2-42143 የሆነች የጋራ ንብረታችን በመሆኗ ያካፍለኝ 3. የመንግስት ቤት በሁለታችን ስም ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑ ያካፍለኝ ስትል ጠይቃለች፡፡ ተከሳሽም ከሳሽ የጠየቀችው የቤት እቃዎች ከጋብቻ በፊት ያፈራኋቸው ያለውን ዘርዝሮ የግሌ ነው አለ፡፡ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 3 ውስጥ ያለው የቤት ቁጥር 603 የሆነው ከሳሽ ከሌሎች ወራሾች ጋር በውርስ ያገኘችው ሲሆን በጋብቻ ውስጥ እያለን ወጪ አውጥተን እድሳት ያደረግንበት በመሆኑ የወጪውን ግማሽ 25,000 ትክፈለኝ፣ መኪና የሰ/ቁጥር 2-42143 ከጋብቻ በፊት ያፈራሁት ንብረት ስለሆነ የግሌ ነው፡፡ የመንግስት ቤት የሆነው የቤት ቁጥር 326 ከጋብቻ በፊት የነበረኝን የቤት ቁጥር 402 በሆነው ምትክ በቅያሪ የተሰጠኝ በመሆኑ ልትካፈል አይገባም በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 180038 ሐምሌ 10 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ከሳሽና ተከሳሽ የተማመኑባቸውን የቤት ውስጥ እቃዎች ይካፈሉ፡፡ ቴሌቪዥን፣ ትሪ፣ ውሃ ማፍያ፣ የቅቤ እቃ፣ ብርድ ልብስ የተከሳሽ የግል ንብረቶች ናቸው፡፡ መኪና የሰ/ቁጥር 2-42143 በተመለከተ የተሰሙት የሰው ምስክሮች ተከሳሽ ከጋብቻ በፊት በስጦታ ያገኘ መሆኑ ቢመሰክርም ያስመዘገበበትን ቀን ለማወቅ ሊብሬ ያላቀረበ በመሆኑ የተመዘገበው በትዳር ውስጥ መሆኑን የሚያመለክት በመሆኑ የጋራ ንብረት ነው፡፡ ተከሳሽ ከሳሽ በውርስ ያገኘችው ቤት ላይ ወጪ አድርጌያለሁ ያለውን በተመለከተ የተሰሙት ምስክሮች የከሳሽ ወንድም ከውጪ ብር ልኮላት ከሳሽ ያሳደሰችው መሆኑን በተሻለ ሁኔታ ያስረዳች በመሆኑ ለተከሳሽ የምትከፍለው ገንዘብ የለም፡፡ የመንግስት ቤት በተመለከተ ተከሳሽ ከጋብቻ በፊት የነበረውን የመንግስት ቤት በጋብቻ ውስጥ የተቀየረለት መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ለከሳሽ ሊያካፍላት አይገባም፡፡ ቀበሌው በቤቱ ላይ የመወሰን ሥልጣኑን ይህ ውሳኔ አይከለክለውም ሲል ወስኗል፡፡ ከሳሽ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርባ በመ/ቁጥር 247029 ታህሳስ 2 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኝዋን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ ግራ ቀኙ በስር ፍ/ቤት በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ መፍረስን ተከትሎ በነበረ የንብረት ክፍፍል ለክርክር ምክንያት የሆነው የመንግስት የቤት ቁጥር 326 በጋብቻ እያለ ከመንግስት የተከራዩት መሆኑ በስር ፍ/ቤት በተረጋገጠበት ሁኔታ ቤቱን ተጠሪ ከጋብቻ በፊት ከመንግስት ተከራይቶ በነበረው የቤት ቁጥር 402 ትክ ነው በሚል እና አመልካች በውርስ ያገኘችው ቤት አለ በሚል ለተጠሪ እንዲሆን የተወሰነበትን አግባብነት ከቤተሰብ ህጉ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሰኔ 11 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታዋን በማጠናከር ተከራክራለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አሁን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ምክንያት የሆነው የመንግስት ቤት የሆነ የቤት ቁጥር 326 በተመለከተ ሲሆን የአሁን ተጠሪ ይህ ቤት ቀድሞ ከጋብቻ በፊት የቤት ቁጥር 402 ከመንግስት ተከራይቼ በነበረው ትክ የተቀየረልኝ በመሆኑ በጋብቻ ውስጥ የተከራየሁት ባለመሆኑ የአሁን አመልካች ልትካፈል አይገባም የሚል ክርክር ያቀረበ ሲሆን የአሁን አመልካች ደግሞ ቤቱ የመንግስት ቤት በመሆኑ እና ይህ የቤት ቁጥር 326 በጋብቻ ውስጥ እየለን ከመንግስት የተከራየን በመሆኑ እንደ የግል ንብረት ከጋብቻ በፊት የተከራየሁት ነው በሚል ልትካፈል አይገባም መባሉ ተገቢ አይደለም

የሚል ክርክር አላት፡፡ የመንግስት ቤት በተመለከተ የመኖሪያ ቤት ችግር ያለባቸው ሰዎች በኪራይ የሚሰጥ ሲሆን አሁን አመልካችንና ተጠሪን ያከራከረው የመንግስት ቤት በትዳር አብረው በቆዩበት ጊዜ በጋራ ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፡፡ የአሁን አመልካችም ሆነ ተጠሪ የራሳቸው የሆነ መኖሪያ ቤት የሌላቸው ነው፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከረው ቤት የመንግስት ቤት እንደመሆኑ ተከራዮች በቤቱ በኪራይ የመጠቀም መብት ነው ያላቸው፡፡ የአሁን አመልካችና ተጠሪ ከተጋቡ በኋላ በኪራይ አብረው ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፡፡ በዚህ የመንግስት ቤት ሁለቱም የቤት ችግር ያለባቸው እና የራሳቸው ቤት የሌላቸው አብረው ሲጠቀሙበት የቆዩትን ቤት እንደ ግል ንብረት ታይቶ ከጋብቻ በፊት ተከራይቶ የነበረው ቤት በትዳር ውስጥ ተለውጦለት ነው በሚል አንዱን ወገን ከቤቱ በማስወጣት የሚሰጥ ውሳኔ ፍትሐዊ ውሳኔ ሆኖ አይገኝም፡፡ የአሁን ተጠሪም ቢሆን የመንግስት ቤቱን ተከራይ የሆነና የቤት ስለነበረበት በኪራይ የሚኖርበት ሲሆንየአሁን አመልካችም በተመሳሳይ የቤት ችግር ያለባት በመሆኑ ሁለቱም በቤቱ ተጠቃሚነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ በቤቱ መጠቀም እንዲችሉ ሊካፈላቸው ሲገባ የአሁን አመልካች ከቤቱ አንዳትካፈል መወሰኑ ካለአግባብ የተሰጠ ውሳኔ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የኢፌዴሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 41(3) የኢትዮጵያ ዜጎች ሁሉ በመንግስት ገንዘብ በሚካሄዱ ማህበራዊ አግልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት እንዳላቸው ተደንግጎ ይገኛል፡፡ እንዲሁም የኢፌዴሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 35(2) ሴቶች በዚህ ሕገ መንግስት በተደነገገው መሰረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው ሲል ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኙን ያከራከረውን የመንግስት ቤት የአሁን አመልካችና ተጠሪ ተመሳሳይ የቤት ችግር ያላቸው ሆኖ እያለና በዚህ ቤት ሁለቱም በጋራ ለረጅም ጊዜ ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑ እየታወቀ የሁለቱንም መብት በሚጠቅም መልኩ አንዲካፈሉ መወሰን ሲገባ አመልካች ቤቱን ለቃ አንዲትወጣ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 247029 ታህሳስ 2 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር180038 ሐምሌ 10 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. የመንግስት ቤት የሆነው የቤት ቁጥር 326 አመልካችና ተጠሪ ተካፍሎላቸው በኪራይ አንዲኖሩበት ብለናል፡፡

3. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማአያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

ሰ/መ/ቁ፡-202737

ቀን፡-29/03/2014ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ አቶ ረጋሳ ጉርሙ ጠበቃ ጋዲሳ ቡታ ቀረቡ

ተጠሪ፡ ወ/ሮ ዘነበች ግ/መንፈስ- ጠበቆች ዘበነ ፍቅሬ እና አዲሱ አየነው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ያለፍርድ ቤት ፈቃድ በተወዉ ጉዳይ ላይ የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም ተብሎ የተሰጠዉን ብይን ለማስለወጥ ነዉ፡፡የክርክሩ መነሻ የቤት ሽያጭ ውል የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ላይ የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን የአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ከሚች ባለቤታቸው አቶ ተሾመ አፈወርቅ ጋር በመሆን በቀን 06/12/1996 ዓ.ም በአ/አ/ክ/ቂ/ክ/ክተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 047 የካርታ ቁጥር ሴ.ኬ.አሲ/02/31/1229/001040/01 የሚታወቅ መኖሪያ ቤት ለአመልካችና ለአቶ ፀጋዬ ግ/መንፈስ ሽጠዋል፣ቤቱን እንዲለቁ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/153563 ቤትን አንዲለቁልኝ ክስ አቅርቤ ፍ/ቤቱን አስፈቅጄ ያነሳሁት ቢሆንም ተጠሪ ቤቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ተጠሪ ቤቱን ለቀው እንዲወጡና እንዲያስረክቡኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋዋል፡፡ተጠሪ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በበኩላቸዉ በቀን 12/05/2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረበውት መልስ አመልካች በመ/ቁ.153563 ላይ ቤቱን ከተጠሪ ለመረከብ ተመሳሳይ ክስ አቅርቦ አመልካቹ በውሉ በተመለከተው ጊዜ የሽያጭ ገንዘቡን ባለመክፈሉ የውል ግዴታውን ስላልተወጣ የባለቤትነት መብት ስለሌው ለቀን ልናስረክብ እንደማይገባ መከራከሪያ አቅርበን እያለ አመልካች በቀን 10/04/2011ዓ.ም በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.278 መሰረት በፈቃዱ ክሱን ለመተው ማመልከቻ አቅርቦ ፍ/ቤቱም በ11/04/2011ዓ/ም ከሻስ ክስ በማቋረጡ ለተጠሪ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍል በማለት መዝገቡን ዘግቷል፣ስለሆነም ያለፍርድ ቤት ፈቃድ በተወዉ ጉዳይ አዲስ ክስ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፣በተጨማሪም የቤት ሽያጭ ውሉ ተፈጽሟል የተባለዉ ከ16 እና ከ17 ዓመታት በፊት ስለሆነ በፍ/ህ/ቁ/1845 መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል፣እንዲሁም በፍ/ህ/ቁ. 2892(3) መሰረት ሻጩ ውሉን እንደ ውሉ ቃል ከመፈፀም መዘግየቱን ከተረዳበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1(አንድ) ዓመት ድረስ ውሉ እንዲፈፀምለት ካልጠየቀ በቀር ገዢው ውሉ በግዴታ እንዲፈፀም የማድረግ መብቱን ያጣል፣ስለዚህ በ1 (አንድ) ዓመት ውስጥ ስላልጠየቀ በይርጋ ውድቅ ይደረጋል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬነገር ረገድ አማራጭ ክርክር ማቅረባቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም በተጠሪ በኩል የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የግራ ቀኝ ክርክር ሰምቶና መርምሮ በመጀመሪያዉ ክስ አመልካች ክሱ እንዲቋረጥ አቤቱታቸውን ሲያቀርቡ ሌላ ጊዜ ክስ ለማቅረብ ፍርድ ቤቱ እንዲፈቀድላቸው የጠየቁ ሳይሆን ክርክሩ እየገፋ በመምጣቱ ውጣ ውረዶች ስለበዛባቸው ክሱን ማቋረጥ እንደፈለጉ የሚያሳይ ነው፡፡ፍ/ቤቱም ከሳሽ(የአሁኑ አመልካች) ያቀረቡትን አቤቱታ በመቀበል ከሳሽ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278 /2/ መሰረት በማየት ጉዳዩን በተመለከተ አዲስ ክስ እንዲያቀርቡ አልፈቀደም፡፡እንዲህ ከሆነ አመልካች ክሱን የተውት ከፍ/ቤት ፈቃድ ውጭ እንደሆነና አመልካች አስፈላጊውን ኪሳራ ለተጠሪ ከፍለው መዝገቡ መዘጋቱን እንዲሁም አመልካችም ጉዳዩን በተመለከተ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደማይችል በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.279(1) ስር ተደንግጓል፣ስለዚህ አመልካች አሁን አዲስ ክስ ማቅረባቸው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(2) እና 279(1) መሰረት አግባብነት የለውም በማለት ክሱን ውደቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ይግባኙ አያስቀርብም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰት መዝገቡን ዘግቷል፡፡የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፣ቤቱን እንዲለቁልኝ ሲጠይቅ ተጠሪ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.153563 ላይ ክስ መስርቼ ስንከራከር ከቆየን በኋላ ፍ/ቤቱን አስፈቅጄ ክስ ያቋረጥኩበት ምክንያት ተጠሪ የባለቤቱ እህት በመሆናቸው እና ተጠሪ የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ ጥያቄም ውሉ ህጋዊ ነው ተብሎ ስለተወሰነ ከዚህ በኋላ ተጠሪ አለቅም የሚሉበት ምንም ህጋዊ ምክንያት የለም በፈለኩ ጊዜ ይለቁልኛል በሚል እሳቤ ፍ/ቤት አስፈቅጄ ክሱ ተቋርጧል፡፡ ፍ/ቤት ሳላስፈቅድ በራሴ ፈቃድ ለመተው ቢፈልግ ኖሮ ፈቃድ ለመጠየቅ አቤቱታ ለፍ/ቤት ባላቀረብኩ ነበር፡፡የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 279(1) የሚመለከተው በራሱ ፈቃድ

ፍ/ቤትን ሳያስፈቅድ ክሱን የተወ ወይም ያቋረጠ ከሳሽን ሲሆን እኔ ግን ለፍ/ቤት አመልክቼ ፍ/ቤቱም ክሴን እንዲተው የፈቀደልኝ መሆኑን የቀረበው ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ስለዚህ አዲስ ክስ ማቅረብ አትችልም በማለት የተሰጠው ብይን የንብረት ባለቤት የመሆን መብቴን የሚቃረን ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ብይን ነው በማለት ብይኑ እንዲታረም አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ግራ ቀኙ ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም በሚል የተሰጠ ውሳኔ ጸንቶ ባለበት ሁኔታ ተጠሪ ቤቱን እንዲለቁ አመልካች በስር ፍ/ቤት ተጠሪ ላይ ያቀረቡትን የክስ አቤቱታ ቀደም ሲል ተጠሪ ቤቱን ይልቀቁልኝ ብለው ክስ አቅርበው በራስዎ ፈቃድ አመለክተው እንዲቋረጥ አድርጓል በማለት አቤቱታቸው ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ 278 እና 279 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸዉ በቀን 30/11/2013ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ በስር ፍርድ ቤት እየተከራከርን እያለ አመልካች ክሱን መተዋቸውን ለፍ/ቤት አመልክተዋል፣ነገር ግን ወደ ፊት በሙሉ ወይም በከፊል አዲስ ክስ የማቅረብ መብት አልጠየቁም፣አላስጠበቁም፣የጀመርኩት ክስ በሙሉ ፍቃድ ማቋረጠን አረጋግጣለሁ የሚል እንጂ አዲስ ክስ ለማቅረብ አይደለም፣የፍ/ቤቱም ትእዛዝ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(1) መሰረት ክስ መቋረጡ ያረጋግጣል፡፡በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(1) መሰረት ክስ ሲቋረጥ ወደፊት ክስ ለማቅረብ ያልተፈቀደለት መሆኑን በፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.116869 እና 158314 ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል፣አዲስ ክስ ማቅረብ የሚቻለው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(2) መሰረት በፍ/ቤት ፈቃድ ሲቋረጥ ነው፡፡ይርጋን በተመለከተ አመልካች ያቀረበው የመፋለም ክስ ሳይሆን በሽያጭ ውል መነሻ ተገደው ቤቱን እንዲያስረክቡኝ የሚል ስለሆነ እና በስር ፍ/ቤት ያልተነሳና በዚህ ረገድም የህግ ስህተት እንዳልተፈፀመ ስለተረጋገጠ አቤቱታው ውድቅ ሆኖ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡ መርምረን እንደተገነዘብነዉ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ተጠሪ የሸጡላቸዉን ቤት ለቀዉ እንዲያስረክቧቸዉ እንዲወሰን የሚል ሲሆን ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ የዳኝነት ጥያቄ በመ/ቁ.153563 ላይ አቅርበዉ አመልካቹ ክሱን ለመተዉ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት መዝገቡ የተዘጋ መሆኑ አላከራከረም፡፡ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካች ክሱን ሲያቋርጡ አዲስ ክስ እንዲያቀርቡ ፍርድ ቤቱ አልፈቀደላቸዉም በማለት ነዉ፡፡አመልካች አጥብቀዉ የምከራከሩት ክሱን ያቋረጥኩት ፍርድ ቤቱን አስፈቅጄ ስለሆነ አዲስ ክስ ከማቅረብ አያግደኝም በማለት ነዉ፡፡

በህግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር የፍትሓብሔር ክርክር የሚመራዉ በፍትሓብሔር ስነስርዓት ህግ በተደነገገዉ አግባብ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 1 ድንጋጌ ይዘት የምንገዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡የፍትሓብሔር ስነስርዓት ህግ ዓይነተኛ አላማ የፍትሓብሔር ክርክር የሚመራበትን ስርዓት በመደንገግ የፍርድ ሂደት በፍትሃዊነት እንዲመራ በማድረግ የተከራከሪ ወገኖችንም ሆነ የፍርድ ቤቱን ሀብት እና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ ክርክሩ እልባት እንዲያገኝ ማስቻል ነዉ፡፡ይህንኑ ዓላማ ለማስካት ያስችላሉ ተብለዉ ከተዘረጉት ስርዓቶች አንዱ ከሳሽ ወገን በአንድ ጉዳይ ላይ ተደጋጋሚ ክስ እንዳያቀርብ ለመከላከል የተዘረጋዉ ስርዓት የሚመለከት ነዉ፡፡በዚህ መዝገብ ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ ከሳሽ ወገን ክሱን ለመተዉ መቻሉና ዉጤቱን የሚመለከተዉ ድንጋጌ ነዉ፡፡

አንድ ክስ ከቀረበ በኋላ በማናቸዉም ጊዜ ከሳሹ ያቀረበዉን ክስ በማንሳት ከተከሳሾቹ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ከክሱ ዉጭ ለማድረግ ወይም ያቀረበዉን ክስ በሙሉ ወይም በከፊል ለመተዉ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278/1/ ስር የተመለከተ ሲሆን ፍርድ ቤቱ አቤቱታዉን ተቀብሎ ትእዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ከሳሽ ወገን ክሱን ለማንሳት ወይም ለማቋረጥ የጠየቀበትን ምክንያት መርምሮ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ከሳሹ አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚችልበትን መብት መጠበቅ የሚችል ስለመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ (2) ስር ተመልክቷል፡፡ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ በአንድ በኩል ከሳሹ በግል ጉዳዩ ላይ የመወሰን መብቱን ተጠቅሞ ክሱን ለመተዉ የሚችል መሆኑን በሌላ በኩል ከሳሹ በፈቃዱ በተወዉ ነገር ላይ አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚችለዉ ፍርድ ቤት መብቱን የተጠበቀለት ሲሆን ብቻ መሆኑን ነዉ፡፡በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278/2/ ስር እንደተመለተዉ ከሳሹ በሌላ ጊዜ አዲስ ክስ እንዲያቀርብ ሊፈቅድለት የሚችለዉም በክሱ አቀራረብ ስርዓት ጉድለት ያለበት ሲሆን ወይም አዲስ ክስ ለማቅረብ ሊያስፈቅድለት የሚችል በቂ ምክንያት ሲኖር እና ፍርድ ቤቱ ምክንያቱን ተቀብሎ መብቱን የጠበቀለት እንደሆነ ነዉ፡፡በሌላ አገላለጽ በቁጥር 278/2/ የተነገረዉን ባለመጠበቅ ከሳሹ ከፍርድ ቤት ፈቃድ ሳይቀበል ክሱን በሙሉ ወይም በከፊል የተወ እንደሆነ አዲስ ክስ ለማቅረብ እንደማይችል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 289/1/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ስለዚህም የቀረበዉ አዲስ ክስ ተገቢነት ያለዉ መሆን አለመሆኑ የሚወሰነዉ ክሱ በፍርድ ቤት ፈቃድ ወይም ያለፍርድ ቤት ፈቃድ የተቋረጠ ወይም የተተወ መሆን አለመሆኑ በመመርመር እንደሆነ ያስገነዝበናል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይዘት መገንዘብ እንደተቻለዉ አመልካች ቀደም ሲል በዚሁ ጉዳይ በመ/ቁ/ 153563 ላይ ያቀረበዉን ክስ ለመተዉ መፈለጉን ገልጾ ለፍርድ ቤቱ ባቀረበዉ ማመልከቻ መሰረት መዝገቡ የተዘጋ ስለመሆኑና መዝገቡም የተዘጋዉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ 278/1/ መሰረት መሆኑን ያመላክታል፡፡የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ መርምሮ አመልካች ክሱን የተወዉ ሌላ ጊዜ አዲስ ክስ ለማቅረብ ከፍርድ ቤቱ ፈቃድ አግኝቶ አለመሆኑንና ያቀረበዉም ማመልካቻ ፈቃድ ለመጠየቅ ሳይሆን ክሱን መቋረጡን ፍርድ ቤቱ እንዲያዉቀዉ ለማድረግ የቀረበ ስለመሆኑ ይዘቱን ቁምር በመመርመር ያረጋገጠዉ ጉዳይ ነዉ፡፡አመልካች አሁንም የሚከራከረዉ ለፍርድ ቤቱ ያቀረበዉ ማመልካቻ ፍርድ ቤቱን ለማሳወቅ ተደርጎ መወሰዱ ስህተት ነዉ የሚል ነዉ፡፡ይሁንና መዝገቡ እንደሚሳየን አመልካች በቀን 10/04/2011ዓ.ም ለፍርድ ቤቱ ያቀረበዉ ማመልከቻ ይዘት ‹‹...ክርክሩ

እየገፋ በመምጣቱ ከሳሽ አላስፈላጊ ዉጣ ዉረዶችን በመተዉ የጀመርኩትን ክስ ክርክር በሙሉ ፈቃድ ክሴን ለማቋረጥ ...›› በሚል በቃለ መጎላ ተደግፎ የቀረበ አቤቱታ መሆኑን የሚገልጽ እንጂ በጉዳዩ ላይ ሌላ ጊዜ አዲስ ክስ ለማቀርብ የፍርድ ቤቱን ፈቃድ የጠየቀ መሆኑን የሚያሣይ አይደለም፡፡ክሱን ለማቋረጥ ያቀረበዉም ምክንያትም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278/2/ ስር ከተደነገጉት ምክንያቶች አንዱም ስለመኖሩ የማያሳይ ነዉ፡፡ፍርድ ቤቱ ማመልከቻዉን መርምሮ የሰጠዉ ትእዛዝ ይዘትም ክሱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278/1 መቋረጡን የሚገልጽ እንጂ አዲስ ክስ ለማቅረብ መብት የተጠበቀለት መሆኑን አያሣይም፡፡የመዝገቡ ይዘት ይህንን የሚያሳይ ሆኖ እያለ አመልካች ፍርድ ቤት ፈቃድ አግኝቻለዉ በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ መሰረት ያለዉ ሆኖ አላገኘም፡፡ከዚህ አኳያ በተጠሪ በኩል የቀረበዉን መቃወሚያ መነሻ በማድረግ የስር ፍርድ ቤትም መ/ቁ/153563 ላይ የተጀመረዉ ክርክሩ የተቋረጠበትን አግባብ መርምሮ ከሳሹ ክሱን በራሱ ፈቃድ የተወዉ መሆኑን እንጂ በፍርድ ቤት ፈቃድ የተወዉ መሆኑን የሚያሣይ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ ስህተት ነዉ የሚባልበት ምክንያት የለም፡፡እንዲህ በሆነ ጊዜ ደግሞ ከሳሽ ወገን በዚያዉ ጉዳይ ላይ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደማይችል የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 289/1 በግልጽ ደንግጓል፡፡የስር ፍርድ ብይን መሰረቱም ይኸዉ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሰል ክርክሮች ላይ ይህ በሰር ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔም ይህንኑ የሚያጠናክር ነዉ፡፡ሰበር መ/ቁ/116869 ፣158314 እና ሌሎች መመልከት ይቻላል፡፡

ሲጠቃለል በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ ይህንኑ የሥነስርዓት ህግ ድንጋጌ እና በተመሳሳይ ክርክሮች ላይ ሰበር ችሎቱ የሰጠዉን ዉሳኔ ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አልተገኘም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ዉሳኔ**

1ኛ/የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/236492 ላይ በቀን 29/09/2012ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/194704 ላይ በቀን 30/04/2013ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ጽንቷል፡፡ 2ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**<u>መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡</u>**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማነታወሸ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-202693

ቀን፡-28/03/2014ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ከድራ ጂብሪል አበዲድ -አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሀዲዮ ኬይራ-አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 26/05/2013 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ሽሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00181 በ19/05/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልጸው በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻነት ሲሆን አመልካች እና በዚህ የሰበር ክርክር በተከራካሪነት ያልተመዘገቡት ኢስማሃን ጅብሪል በፌደራል የመጀመሪያ ደረጀ ሽሪዓ ፍርድ ቤት የፍርድ ባለዕዳዎች የነበሩ ሲሆን ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ነበሩ፡፡

የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች እና በስር 2ኛ የፍርድ ባለዕዳ ላይ ባቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ባቀረብኩት የወራሽነት አቤቱታ መሰረት ጉዳዩ በአጣሪዎች ከተጣራ በኋላ የውርስ ሀብት ነው ተብሎ በተወሰነልኝ መሰረት ይዞታው የውርስ ሀብቴ መሆኑ በተረጋገጠው መሰረት እንዲፈፀምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡አመልካች በሰጡት መልስም በሽሪዓ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

188/92 አንቀጽ 4(2) መሰረት በፍርድ ቤት ቀርበን ለመዳኘት አንፈልግም በማለት ያመለከትን በመሆኑ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ዘግቶ ማሰናበት ሲችል ጉዳዬን ማየት የለበትም፡፡ጉዳዩን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት አቅርበን ታይቶ የመጨረሻ እልባት ያገኘ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ዘግቶ ሊያሰናብተኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፌደራል መጀመሪያ ደረጀ ሽሪዓ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በሰጠው ብይንም አመልካች እና የስር 2ኛ የፍርድ ባለዕዳ ስለውርስ ማጣራቱ ሂደት ማወቅ አለማወቃቸውን አስመልክቶ ወጥነት ያለው ክርክር አለማቅረባቸውን፣ተጠሪ የውርስ ሀብቱ ተጣርቶ የውርስ ድርሻቸውን ለመውረስ ያቀረቡት አቤቱታ ከህጉ አንፃር ክርክር የሚያስነሳ አለመሆኑን እና በሽሪአ ፍርድ ቤቱ የተያዘው የውርስ ማጣራት ሂደት አስቀድሞ የተጀመረ ሆኖ እያለ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በድጋሚ ተከፍቶ መታየቱ አግባብ አለመሆኑን በመጥቀስ የአሁን ተጠሪ ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ሊቀጥል ይገባል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡አመልካች እና የስር 2ኛ የፍርድ ባለዕዳ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለድሬደዋ ፌደራል ከፍተኛ ሽሪዓ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙ ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአጭሩ፡- የሽሪዓ ፍርድ ቤት የውርስ ሀብትን በተመለከተ አከራካሪ ሲሆን ጉዳዬን ለመዳኘት ስልጣን የሚኖረው በአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 4(2) ስር እንደተገለፀው በተከራካሪዎች ፈቃድና ስምምነት መሰረት እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አንድ ተከራካሪ ወገን በሽሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት አልፈልግም ያለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የአስገዳጅነት ባህሪ ያለው የዳኝነት ስልጣን ሊኖረው አይችልም ፡፡

ይሁን እንጂ የፌደራል መጀመሪያ ደረጀ ሽሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ አለመሆናችንን መግለፃችንን እያወቀ ወዲያው መዝገቡን መዝጋት ሲገባው በአስገዳጅነት መዳኘቱ አግባብ አይደለም፣ አንድ ሰው የፍርድ ባለዕዳ ሊባል የሚችለው በፍርድ ቤት ተከሶ የተፈረደበት ሲሆን ብቻ ሆኖ እያለ የአሁን አመልካች እና እህቱ ላይ እስካሁን ድረስ በተጠሪ አማካይነት የቀረበብን ክስም ሆነ ያስፈረደብን ፍርድና ውሳኔ በሌለበት እኛ ወራሾች ሳንፈቅድ በሽሪዓ ፍርድ ቤት የፀደቀ የውርስ ሀብት ማጣሪያ ሪፖርት ቢኖር እንኳንም እኛ ተወላጆች ያልተሳተፍንበት ከመሆኑም በላይ ሪፖርት እንደ አንድ ማስረጃ የሚያገለግል በሌላ ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል እንጂ እንደ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተቆጥሮ አፈፃፀም የሚደረግበት ባልሆነበት፣ የሚች ወላጅ አባቱ አቶ ጂቢሪል አበዲድ እና ሚች ወላጅ እናቱ ወ/ሮ አዊያ ዋወራህ የውርስ ሀብት መደበኛ በሆነው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.72370 ተጣርቶ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ የፀደቀ ከመሆኑም በተጨማሪ በአሁን ተጠሪ ላይ በመ/ቁ.76758 ክስ መስርተንባቸው ወራሽ እንዳልሆኑ ተረጋግጦ ተፈርዶባቸው በአፈፃፀም መ/ቁ.78088 ተስተናግዶ የአፈፃፀም ሂደቱም ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ እያለ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ታይቶ ፍፃሜ ያገኘውን ጉዳይ ወደ ጎን በመተው ውሳኔውን ለመቀልበስ ስለተፈለገ ብቻ ጉዳዬን እንደገና በፌደራል

መጀመሪያ ደረጀ ሸሪዓ ፍርድ ቤት መደኘት መሰረታዊ የሕግ ስሕተት በመሆኑ አመልካች ባቀረብኳቸው ቅሬታዎች መሰረት ጉዳዪ ታይቶ የስር የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ይሻርልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ አመልካች ጉዳዪ ታይቶ በመደበኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኘና አፈፃፀሙም በዛው ፍርድ ቤት ይደረግልኝ በማለት ያቀረበውን የመቃወሚያ ክርክር የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ወደ ጎን ትተው አፈፃፀሙ ይቀጥል ያለበትን አግባብ ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስም የአሁን ተጠሪ ከአመልካች ቀድሜ በድሬደዋ ፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 05388 ላይ ለክርክር መነሻ የሆነው ንብረት ላይ የሚስትነት ድርሻ ያለኝ ስለሆነ ንብረቱ እንዲጣራልኝ አቤቱታ አቅርቤ እየተጣራ ባለበት የአሁን አመልካች የሚኝ ባለቤቴ ልጆች ነን በማለት ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው ተከራክረው በንብረቱ ላይ ተጠሪ የሚስትነት ግማሽ ድርሻ ያለኝ ስለመሆኑ አመልካችና ሌሎች የሚኝ ባለቤቴ ልጆች ደግሞ በቀሪው ድርሻ ላይ የውርስ መብት ያለችው ስለመሆኑ ተወስኗል፡፡አመልካች ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት ላይ ተጠሪዋ የሚስትነት ድርሻ ያላቸው ስለመሆኑ አስቀድሞ ተከራካሪ በሆኑበት ጉዳይ ላይ የተሰጠ ፍርድ መኖሩን እያወቁ ተጠሪን በቤቱ ላይ ምንም መብት እንደሌለኝና 50 ዓመት የኖሩቡበትን ቤት በሕገ ወጥ መንገድ ነው የያዘችው ብለው ክስ አቅርበው መጥሪያ ሳይደርሰኝ ለመቀበል እምቢተኛ እንደሆንኩ አድርገው ቃለ መሃለ አቅርበው ጉዳዪ በሌለሁበት እንዲታይ በማድረጋቸው ይህንን በመቃወም አቤቱታ አቅርቤ በክርክር ላይ እንገኛለን፡፡

ተጠሪ በሸሪዓ ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረብኩት የአሁን አመልካችን መልስ ሰጭ አድርጌ ባለመሆኑ የእኔን አቤቱታ በመረጥኩት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት አቅርቤ የመዳኘት መብቴ ሕግ መንግስታዊ ነው፡፡የአሁን አመልካችን በአቤቱታዬ ላይ መልስ ሰጭ አድርጊያት ቢሆን ኖሮ በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፈቃደኛ አይደለሁም በሚል የምታቀርበው ክርክር ተቀባይነት ይኖረው ነበር፡፡ነገር ግን ተጠሪ አመልካችን መልስ ሰጭ አድርጌ ባለቀረብኩበት አቤቱታ ጣልቃ ለመግባት አመልክታ በፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ አይደለሁም በሚል የምታቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ሲሆን በሸሪዓ ፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር ላይ ጣልቃ ገብቶ መከራከር በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ስምምነትን እንደመስጠት የሚያስቆጠር ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰመ/ቁ 45806 በቅጽ 10 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ከአመልካች በፊት ንብረት እንዲጣራልኝ አቤቱታ ሳቀርብ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ለመግባት አመልክተውና ተከራክረው የተወሰነውን በውሳኔውም ቅሬታ አድሮባቸው ይግባኝ ጠይቀው የፀናባቸውን ጉዳይ ለዚህ ፍርድ ቤት የክርክሩን ይዘት ለውጠው በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ ሳንሆን ተወስኖብናል ሲሉ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ስላልሆነ ፍርድ ቤቱ

ሊቀበለው አይገባም፡፡ስለሆነም የተከበረው ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ከመነሻውም የአፈፃፀም አቤቱታ ሊቀርብበት የሚችል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ አለን? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን የሰበር ክርክር ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ ተጠሪ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መሰረት በማድረግ በተያዘው የውርስ መዝገብ ላይ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀፅ 4(2) መሰረት በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት አንፈልግም በማለት ያመለከቱ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተመለከተ ሲሆን አመልካች ይህ መቃወሚያቸው ታልፎ በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፈቃዳቸውን ባልሰጡበት ለአፈፃፀም ክሱ መነሻ የሆነው ውሳኔ መሰጠቱ አግባብ አለመሆኑን በመግለፅ የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

በመሰረቱ ከላይ እንደተመለከተው ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት አቤቱታቸውን ያቀረቡት የውርስ ሀብቱ ተጣርቶ የውርስ ድርሻቸውን እንዲለይ በመሆኑ ይህ ደግሞ በመሰረታዊነት መብት አለን ባዮችን ወይም ወራሾችን መወሰን፤የሚች ኑዛዜ ካለ መፈለግ፤በዚህ ኑዛዜ መሰረት ተጠቃሚዎችን መወሰን፤ውርሱን ማስተዳደር፤የውርሱን ተከፋይ ገንዘብ መሰብሰብና እዳዎችን መክፈል፤የሚቹን ንብረት ማጣራትና ማፈላለግ፤የኑዛዜ ስጦታዎችን መክፈልና የመሳሰሉት ተግባራት የሚከናወኑበት ሆኖ በመጨረሻም የሚች ወራሽ መሆኑን የሚገልፅ አልያም ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ ጭምር የሚያመለክት የወራሽነት ማስረጃ የሚሰጥበት በመርህ ደረጃ በአንድ ወገን አመልካችነት የሚቀርብ  ከህጉ አንፃር ክርክር የሌለበት ከመሆኑ አንፃር አመልካችና የስር 2ኛ የፍርድ ባለዕዳ በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ባይፈቅዱም በተጠሪ ፈቃደኝነት የቀረበውን አቤቱታ መሰረት አድርጎ የስር ፍርድ ቤት የወራሽነት የምስክር ወረቀት መስጠቱ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ነገር ግን ለተጠሪ የውርስ ሀብቱ ተጣርቶ የወራሽነት የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው በመሆኑ ይህንን የምስክር ወረቀት መሰረት በማድረግ ተጠሪ ከወራሾች ጋር በስምምነት መከፋፈል ካልቻሉ በድርሻቸው መጠን ዳኝነት ከፍለው ይሄው መብታቸው በፍርድ እንዲረጋገጥ ዳኝነት ባልጠየቁበት፤የወራሽነት የምስክር ወረቀት ተጠሪ የዳኝነት በድርሻቸው መጠን ከፍለው መብታቸው በፍርድ እንዲረጋገጥ ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የሚሰጣቸው ብቻ ሆኖ እያለ፤በዚህ አግባብም የወራሽነት የምስክር ወረቀት በራሱ ፍርድ ስላልሆነ አፈፃፀም ሊጠየቅበት እንደማይችል በሰበር መዝገብ ቁጥር 18576 አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶ እያለ የስር ፍርድ ቤት የወራሽነት የምስክር ወረቀቱን መሰረት አድርጎ የቀረበውን የአፈፃፀም አቤቱታ ተቀብሎ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ብይን መስጠቱና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ከፍተኛ ሽሪአ ፍርድ ቤት ይህንኑ የስር ፍርድ ቤት የፈፀመውን ስነስርዐታዊ ግድፈት ሊያርም ሲገባ ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ወስነናል፡፡

# ውሳኔ

1. በድሬደዋ ፌደራል መጀመሪያ ደረጀ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 07901 በቀን 22/04/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት አፈፃፀሙ ይቀጥል በማለት የሰጠው ብይን እና የፌደራል ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 00181 በቀን 19/05/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት ይህንን ብይን በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በተጠሪ አቤቱታ መሰረት ውርስ ተጣርቶ የተሰጠው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ተጠሪ በድርሻቸው መጠን ዳኝነት ከፍለው መብታቸው በፍርድ እንዲረጋገጥ ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የሚፈጥር እንጂ አፈፃፀም ሊጠየቅበት የሚችል ፍርድ አይደለም ብለናል፡፡
3. በሰበር ሰሚው ችሎት ተለዋጭ እስኪደርሰው ድረስ በድሬደዋ ፌደራል መጀመሪያ ደረጀ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 07901 የተጀመረው የአፈፃፀም መዝገብ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ በቀን 30/06/2012 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሂ/መ

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**
**ሰበር ሰሚችሎት**

የሰ/መ/ቁ. 202681
ቀን ፡- ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- 1. ወ/ሮ ከበቡሽ ቡሎ
2. ወ/ሮ አስቴር አበበ
3. ወ/ሮ ወርቅነሽ አሰፋ
4. ወ/ሮ ወይንሸት ተክሌ
5. ወ/ሮ ቆንጂት ዘውዴ
6. ወ/ሪት አስናቁ ዓለሙ
7. ወ/ሮ እየሩሳሌም ገለቱ
8. ወ/ሮ አጸደ አረሩ
9. ወ/ሮ ተረፉ አረሩ
10. ወ/ሮ ጠጅነሽ ቱኒ

ቀረቡ (1-5) ቀረቡ (6-10)

ተጠሪ ፡- አቶ መንግሥቱ ባለህ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች የስር ከሳሾች ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በተጠሪ የንግድ ሥራ በልብስ ስፌት፣ በልብስ እጅ ሥራና ዝምዘማ የሥራ መደብ ተቀጥረን ስንሰራ ነሀሴ 28 ቀን 2011 ዓ/ም ከሕግ ውጭ በቃል ከሥራ አሰናብቶናል፡፡ የሥራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ስለሆነ የአገልግሎት ክፍያ፣ ካሣ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የዓመት ዕረፍት፣ ትርፍ ሰዓት የተሰራበት ክፍያ እንዲሁም ክፍያው ለዘገየበት

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ቅጣት እንዲከፈላቸው እና የሥራ ልምድ እንዲሰጣቸው ዳኝነት ጠይቀዋል። ተጠሪ ያቀረቡት መልስ በሕመም ምክንያት የተወሰኑ ወራትን አልነበርኩም፤ በዚህ ጊዜ በአደራ ሥራውን ሲያስተዳድሩ የነበሩት ባለቤቴና ልጄ ናቸው። የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት በመግጠሙ ጥሬ ዕቃ በገበያው ላይ ማግኘት አልተቻለም። በዚህ ለአመልካቾች ስራ ሳይሰሩ የሰኔ እና ሀምሌ ወር 2011 ዓ/ም ደመወዝ ተከፍሏል። እጥረቱ ሊቀረፍ ስላልቻለ ሠራተኞች ሳይሰሩ ከሚመላለሱ ተብሎ ብር 5,000.00 በመክፈል በመስከረም ወር እንዲመለሱ ገልጸን የተለያየን ቢሆንም በመስከረም ወር ስራ ለመጀመር መቅረብ ሲገባቸው ከሥራም ሳይሰናበቱ ክስ አቅርበዋል። አሁንም ወደሥራቸው ቢመለሱ ተቃውሞ የለኝም በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 107631 የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት ከቀረበው ማስረጃ በተሻለ የተረጋገጠው አመልካቾች በመስረም ወር 2012 ዓ/ም ወደሥራ ተመልሰው የነበሩ ቢሆንም ሥራ የለም ተብለው የተሰናበቱ መሆኑ ነው። በጥሬ ዕቃ ዕጥረት የተሰናበቱ ቢሆንም በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 28 መሠረት የሚደረግ ስንብት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሊከናወን የሚገባ ሲሆን ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጡ አመልካቾችን ከሥራ ማሰናበታቸው ከሕግ ውጭ የሥራ ውሉ እንደተቋረጠ ያረጋግጣል። ሥለሆነም የሥራ ሥንብቱ ሕገ-ወጥ ነው። ካሣ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት፣ የዓመት ዕረፍት ክፍያ ተጠሪ ለአመልካቾች ሊከፍሉ ይገባል፤ የሥራ ልምድም ይሰጣቸው በማለት ሲወስን ትርፍ ሰዓት ሥራ መሰራቱ አልተረጋገጠም በማለት ዳኝነቱን ውደቅ አድርጓል። ተጠሪ ያቀረቡትን ይግባኝ የተቀበለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ አመልካቾች በክሳቸው የሥራ ውሉ ተቋረጠ በተባለበት ቀን ከሥራ የተሰናበቱ ስለመሆኑ ምስክሮቻቸው አላስረዱም። የተጠሪን ባለቤትና ልጅ እንደቀጣሪ በመቁጠር እንዲሁም የተጠሪ ምስክሮች መስከረም ወር ላይ እንዲመለሱ ተነግሯቸዋል በማለት መመስከራቸው፣ 2ኛ ምስክርም ከዚህ በኋላ እንዳትመጡ አላልኩም በማለት ያስረዳው ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ተጠሪ አመልካቾችን ከሥራ ማሰናበታቸውን አላስረዱም። የሥር ፍርድ ቤት በግራቀኙ ያልተነሳን መከራከሪያ በማንሳት በጥሬ ዕቃ ዕጥረት ነው የተሰናበቱት ማለቱ ተገቢ አይደለም። ማስጠንቀቂያ አለመስጠትም የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ከሚያስከፍል በስተቀር ስንብቱን ሕገ-ወጥ አያደርገውም። ተጠሪ አምነው ያልከፈሉት ክፍያ ስለመኖሩ የቀረበ ክርክርና ማስረጃ ሳይኖር ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት እንዲከፈል መወሰኑ ስህተት ያለበት ነው። ስለሆነም የሥራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በሚል ካሣ፣ የሥራ ስንብት፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት ተጠሪ እንዲከፍሉ የተሠጠውን የውሳኔ ክፍል ሽሯል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የሥራ ውላችን ከሕግ ውጭ መቋረጡ በማስረጃ ተረጋግጧል። የተጠሪ ባለቤትና ልጅ ሥራውን በአደራ ያስረከቧቸው ስለመሆኑ ተጠሪም አምነዋል። ውሳኔው ሕግን የተከተለ አይደለም የሚል ነው። የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ የማስረጃ ምዘና መርሕን የተከተለ ስለመሆን አለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ የታዘዙ ሲሆን ያቀረቡት መልስ አመልካች ከሥራ መሰናበታቸውን

አላስረዱም፡፡ ማስረጃው ተመዝኖ የተወሰነ ስለሆነ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የአመልካቾች የሥራ ውል የተቋረጠው በአሠሪው አነሳሽነት ወይስ በሠራተኛው አነሳሽነት? የሚለውን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በተጠሪ የንግድ ሥራ በልብስ ስፌት፣ በልብስ እጅ ሥራና ዝምዘማ የሥራ መደብ ተቀጥረን ስንሰራ ነሀሴ 28 ቀን 2011 ዓ/ም ከሕግ ውጭ በቃል ከሥራ አሰናብቶናል፡፡ የሥራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ስለሆነ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው እና የሥራ ልምድ እንዲሰጣቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት በመግጠሙ ጥሬ ዕቃ በገበያው ላይ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በዚህ ለአመልካቾች ስራ ሳይሰሩ የሰኔ እና ሀምሌ ወር 2011 ዓ/ም ደመወዝ ተከፍሏል፡፡ እጥረቱ ሊቀረፍ ስላልቻለ ሠራተኞች ሳይሰሩ ከሚመላለሱ ተብሎ ብር 5,000.00 በመክፈል በመስከረም ወር 2012 ዓ/ም እንዲመለሱ ገልጸን የተለያየን ቢሆንም በመስከረም ወር ስራ ለመጀመር መቅረብ ሲገባቸው ከሥራም ሳይሰናበቱ ክስ አቅርበዋል፡፡ አሁንም ወደሥራቸው ቢመለሱ ተቃውሞ የለኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የሥራ ውል የሚቋረጠው አንደኛው በሕግ ወይም በሥምምነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች አነሳሽነት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 24 በሕግ መሠረት ውል የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ተዘርዝረዋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 25 ደግሞ በሥምምነት ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ ይገልጻል፡፡ በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ በአዋጁ ከአንቀጽ 26-30 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 31 እና 32 ደግሞ በሠራተኛው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበትን ሁኔታ ደንግጓል፡፡ የአዋጁ ድንጋጌ አንቀጽ 31 በአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለአሠሪው በመስጠት ሠራተኛው ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል የሚገልጽ ነው፡፡ ሌላው በሠራተኛው አነሳሽነት የሚፈጸም የሥራ ውል ማቋረጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 32(1)(ሀ እስከ ሐ) የተመለከተ ሲሆን በሕጉ የተዘረዘሩት ምክንያቶች አሠሪው የሠራተኛውን ሠብዓዊ ክብርና ሞራል መንካቱ፣ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር በሠራተኛው ላይ መፈጸም፣ ለሠራተኛው ደኅንነት ወይም ጤንነት አደጋ ሊያደርስ የሚችል ምክንያት እያለ አሠሪው ተገቢውን እርምጃ ካልወሰደ ወይም ሌላ አሠሪው ለሠራተኛው መፈጸም ያለበትን ግዴታ በመደጋገም ካልፈጸመ ሠራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ማቋረጥ የሚችልበትን ሁኔታ አስቀምጧል፡፡

በተያዘው ጉዳይ እያከራከረ ያለው የአመልካቾች የሥራ ውል በተጠሪ አነሳሽነት የተቋረጠ ነው ወይስ በአመልካቾች በራሳቸው ሥራውን በመተዋቸው የሚል ነው፡፡ አመልካቾች የሥራ ውላችን በተጠሪ የተቋረጠ ነው ያሉ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 2001(1) እና በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 259 እና 260 መሠረት የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ጠቅሶ የሚከራከር ወገን ፍሬ ነገሩ ስለመኖሩ የማስረዳት ግዴታ ስላለበት ውሉ በተጠሪ መቋረጡን ማስረዳ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃዎች ሰምቶ አመልካቾች

በተጠሪ ስለመሰናበታቸው ተረጋግጧል በማለት የወሰነ ቢሆን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ ማስረጃው በአግባቡ አልተመዘነም በሚል አመልካቾች በክሳቸው የሥራ ውሉ ተቋረጠ በተባለበት ቀን ከሥራ የተሰናበቱ ስለመሆኑ ምስክሮቻቸው አላስረዱም፡፡ የተጠሪን ባለቤትና ልጅ እንደቀጣሪ በመቁጠር እንዲሁም የተጠሪ ምስክሮች መስከረም ወር 2012 ዓ/ም ላይ እንዲመለሱ ተነግሯቸዋል በማለት መመስከራቸው፣ 2ኛ ምስክርም ከዚህ በኋላ እንዳትመጡ አላልኩም በማለት ያስረዳው ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ተጠሪ አመልካቾችን ከሥራ ማሰናበታቸው በሚገባ አላስረዱም ሲል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የማስረጃ ምዘና ሂደት የተፈጸመ የማስረጃ ሕግና ማስረጃ ምዘና መርሕ ጥሰት መኖሩን የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ ስለሆነም አመልካቾች በተጠሪ የሥራ ውላቸው መቋረጡን ያላስረዱ በመሆኑ ካሣ፣ የሥራ ስንብት፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት ተጠሪ የሚከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 249944 ጥር 27 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡- 202581

ቀን፡- 26/02/2014ዓ.ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ረሂማ አብዱላሂ

ተጠሪዎች ፡-1.ከዲር ዮሱፍ በከር

2. ሰይዳ ረመዳን

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጋራ የሆነ የእርሻ መሬት በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ነዉ የተባለዉ ዉል ቀሪ እንዲደረግና ይዞታዉን ለማስለቀቅ እንዲሁም አላባ ለማስከፈል የቀረበ ክስ የመዳኘት ሥልጣን የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በተጠሪዎችና በስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ መስጠፋ ዩሱፍ ላይ በሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ለ30 ዓመታት በትዳር ተሳስረን አብረን ስንኖር በሐረር ክልል በድሬ ጠያራ ወረዳ በአቦከር መጠሪ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ዉስጥ ያለንን አንድ ጥማድ ከግማሽ የሆነ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰዉን የእርሻ መሬት ያለእኔ ፈቃድ በሕገ-ወጥ መንገድ ለአሁን ተጠሪዎች በሽያጭ አስተላልፈዋል፡፡ በዚህ ምክንያት በአመት 20 ኩንታል ማሽላ በማምረት ማግኘት የምንችለዉን በኩንታል በብር 1200.00 ሂሳብ ብር 24,000.00 አሳጥዉኛል፡፡እየተቃወምኩ በመሬቱ ላይ ተጠሪዎች ቤት ሰርተዉበታል፡፡ስለሆነም

ዉሉ ሕገ-ወጥ ስለሆነ እንዲፈርስና የገነቡትን ቤት አፍርሰዉ ይዞታዬን እንዲለቁ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የስር 1ኛ ተከሳሽ ለክሱ በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ከአመልካች ጋር በጋራ የያዙት መሬት እንደሆነና ያለአመልካች ፈቃድ በማንኛዉም ሁኔታ ማስተላለፍ እንደሌለብኝ ባለማወቅ ለተጠሪዎች በማስተላለፌ ተጠሪዎች በእርሻ መሬታችን ላይ ቤት ሊሰሩበት ስለቻሉ በአመልካች ጥያቄ መሰረት ቢወሰን አልቃወምም የሚል ይዘት ያለዉ መልስ ሰጥተዋል፡፡2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ መኖሪያ ቤት ለመግዛት እየፈለጉ ባሉበት የስር 1ኛ ተከሳሽ በመሬቱ የመጠቀም መብታቸዉን ለማስተላለፍ ፈልገዉ የመጠቀም መብታቸዉን ብር 100,100.00 ሸጠዉልናል፡፡ የመሬት ባለቤትነት ለመዉሰድ በሂደት ላይ እንገኛለን፡፡መሬቱ በዚህ አግባብ እንደተላለፈልንና ቤት ስንሰራም አመልካች እያወቁ አልተቃወሙንም በማለት ክሱ ዉድቅ እንዲደረግላቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 17912 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ሰምቶና መርምሮ በቀን 26/01/2012 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የስር 1ኛ ተከሳሽ ያለተጠሪ ፈቃድ ባልና ሚስት ሆነዉ ከአመልካች ጋር በጋራ ባለይዞታ የሆኑበትን የመሬት ይዞታ ለተጠሪዎች በሽያጭ በማስተላለፍ ያደረጉት ዉል የፌዴራል ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 68ን የሚቃረን በመሆኑ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 69 መሰረት ዉሉ ፈርሶ ተጠሪዎች የገነቡትን ግንባታ በራሳቸዉ ወጪ አፍርሰዉ መሬቱን ለቀዉ እንዲወጡና ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 04953 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 22/10/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ክስ የመሰረቱት ፍርድ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሰረት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን አለዉ በማለት ቢሆንም ግራ ቀኝ የኦሮሚያ ክልል ነዋሪዎች በመሆናቸዉ፣ዉሉ የተደረገበት የመሬት ይዞታ የሚገኘዉ በሐረሪ ክልል ዉስጥ የሚገኝ በመሆኑ ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ የሚያደርግ ምክንያት በሌለበት እንደፌዴራል ጉዳይ ተቀብሎ መዳኘቱ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም አመልካች ክስ ሲመሰርቱ በግምት ብር 24,000.00 ምርት የሚገኝበት መሬት እንደሆነ ጠቅሰዉ ያቀረቡት ክስ ስለሆነ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ልክ የሚገመት ክስ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ተቀብሎ ለመዳኘት የሚያስችል ስልጣን ሳይኖረዉ የሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሯል፡፡በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በመ/ቁጥር 00124 ላይ በቀን 24/03/2013ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ አቤቱታቸዉን ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 07/10/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ግራ ቀኝ በተለያዩ ክልሎች ነዋሪ መሆናችን ስለተረጋገጠ የስር የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደፌዴራል ጉዳይ በመቁጠር ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ ሆኖ ሳለ ተጠሪዎችም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን እንደሌለዉ ገልጸዉ ያቀረቡት መቃወሚያ ሳይኖር ዉሳኔዉ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሻሩ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/2 ስር የተደነገገዉንና በሰ/በ/ቁጥር 144613 ላይ የተሰጠዉን ዉሳኔ የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት

የተፈጸመበት ነዉ፡፡እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረብኩትን የሰበር አቤቱታ ምርምሮ ለሰበር እንዲቀርብ አዞ ግራ ቀኝ የጽሁፍ ክርክር አቅርበን ለዉሳኔ በተቀጠረበት ቀን ጉዳዩ ለሰበር አያስቀርብም በማለት ዉሳኔ የሰጠበት አግባብ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 እና ከቁጥር 339-348 ስር ስለዉሳኔ አሰጣጥ የተደነገገዉን ሥነ ሥርዓት የተከተለ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማጣራት ያስቀርባል ብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ወደኋላ ተመልሶ አያስቀርብም በማለት ዉሳኔ የሰጠበት አግባብ ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በቀን 05/11/2013 ዓ/ም የተፃፈ መልስ በማቅረብ ግራ ቀኝ በአንድ ክልል ዉስጥ ነዋሪ ስለሆንና ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬትም በሐረሪ ክልል የሐረሪ ከተማ አካል ሆኖ የሚገኝ በመሆኑ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን ያለዉ የከተማ ነክ ፍርድ ቤት በመሆኑ የስር የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በፌዴራል ዳኝነት ሥልጣን ተቀብሎ መዳኘቱ ስህተት ነዉ ተብሎ በመሻሩ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት መልሳቸዉን ሰጥተዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ በተጨማሪ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደፌዴራል ጉዳይ ቆጥሮ በዉክልና ሥልጣን አከራክሮ መወሰኑ ተገቢ አይደለም ተብሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዉሳኔዉ በመሻሩ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካችና ተጠሪዎች ነዋሪነታቸዉ በአንድ ክልል ዉስጥ እንደሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡የክሱ ስረ ነገር እና በአመልካች የተጠየቀዉ ዳኝነት አመልካች ያለፈቃደ የጋራ ባለይዞታ የሆንኩበትን የእርሻ መሬት ባለቤቱ ለተጠሪዎች በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገዉ ዉል ቀሪ ሆኖ ተጠሪዎች እየተቃወምኩ የሰራሁትን ቤት አፍርሰዉ መሬቱን እንዲለቁ ይወሰንልኝ የሚል እንደሆነ ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡እንዲሁም ለክሱ መሰረት የሆነዉ ዉልም የተደረገዉም ሆነ ተሸጠ የተባለዉ መሬት የሚገኘዉ በሐረሪ ክልል ዉስጥ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዘንድ ክሱ ሲቀርብ በሥራ ላይ በነበረዉ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/2 መሰረት መደበኛ ነዋሪነታቸዉ በተለያዩ ክልሎች ዉስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንደሆነ በተደነገገዉ መሰረት የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ መደበኛ የመኖሪያ አድራሻ በተለያዩ ክልሎች ዉስጥ መሆኑ ከተረጋገጠና ክርክር ያስነሳዉ ንብረት ግምት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ሥልጣን ሥር የሚወድቅ መሆኑ ካረጋገጠ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/4 መሰረት በዉክልና ጉዳዩን ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ሆኖም በተያዘዉ ጉዳይ የግራ ቀኙ መደበኛ አድራሻ በአንድ ክልል ዉስጥ መሆኑ ከመረጋገጡም በላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል የተደረገዉና እንዲፈጸም የታቀደዉ መሬቱ

በሚገኝበት ሐረሪ ክልል ዉስጥ በመሆኑ ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ የሚያደርግ ምክንያት የለም፡፡ስለሆነም የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደፌዴራል ጉዳይ በመቁጠር በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን አከራክሮ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት መሻሩና ጉዳዩ የክልል ጉዳይ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል ስህተት የተፈጸመበት አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በሰጠዉ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ያቀረረቡትን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ተጠሪዎችን ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ካደረገ በኋላ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337ን በመጥቀስ የክልሉ ሰበር የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መሰረዙን ከቀረበዉ ክርክር ተገንዝበናል፡፡ እስካሁን የሰበር ችሎት ክርክሮችን የሚመራበት የተለየ ሥነ ሥርዓት ሕግ ባለመኖሩ በሥነ ሥርዓት ሕጎች ለመደበኛ ክስና ለይግባኝ ክርክሮች አመራር የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ለሰበር በሚሆን መልኩ አመሳስሎ ተግባራዊ የማድረግ የዳበረ የሰበር ችሎቶች አሰራር መኖሩ ግልጽ ነዉ፡፡በዚህ አግባብ የክልልም ሆነ የፌዴራል የሰበር ሰሚ ችሎቶች የሥነ ሥርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች ሲጠቀሙ በሥነ ሥርዓት ሕጎች የተዘረጋዉን የክርክር ሂደቶች አፈጻጸም ቅደም ተከተል በተቻለ መጠን በጥንቃቄ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ለፍትሐ ብሔር ይግባኝ ክርክር አመራር በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 እና 338/1 መሰረት የይግባኝ ማመልከቻዉንና የመጀመሪያዉ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ የሰጠበትን መዝገብ ግልባጭ በመመርምርና ይግባኝ ባይን በመስማት መልስ ሰጭ ቀርቦ እንዲከራከር ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ከሰጠ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ሕግን መርምሮ እንደነገሩ ሁኔታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341፣343/1 እና 348/1 መሰረት ዉሳኔ ሊሰጥ ይገባል እንጂ ወደኋላ ተመልሶ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337ን በመጥቀስ የይግባኝ ማመልከቻዉ በመሰረዝ መወሰን የሚችልበት ሥነ ሥርዓት አግባብ የለም፡፡በተመሳሳይ ለይግባኝ ክርክር አመራር የተቀመጠዉን ሥነ ሥርዓት በመጠቀም የሰበር ክርክር ሲመራም የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ የሆነ ወገን መልስ አቅርቦ እንዲከራከር ከተደረገ በኋላ በስር ፍርድ ቤት የመጨረሻ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩ ተመርምሮ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ከተባለ እንዲታረም ካልሆነም የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲጸና ከሚወሰን በስተቀር ሂደቱን ወደኋላ በመመለስ የፍ/ብሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 ተጠቅሶ በሰበር ችሎት እንዲመረመር የሚያስችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ የሰበር አቤቱታዉ የሚሰረዝበት አግባብ የለም፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲመረመር ትእዛዝ ሰጥቶ ተጠሪዎች መልስ ሰጥተዉ ከተከራከሩ በኋላ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337ን በመጥቀስ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመሰረዝ ትእዛዝ የሰጠበት መንገድ ሊታረም የሚገባዉ የክርክር አመራር ጉድለት ነዉ፡፡ሆኖም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት የይግባኝ ማመልከቻም ሆነ የሰበር አቤቱታን በመሰረዝ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ከዉጤት አንጻር ሲታይ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ የማጽናት ያክል ሕጋዊ ዉጤት ያለዉ

ነዉ፡፡በመሆኑም ከመነሻዉም ክርክሩ የፌዴራል ጉዳይ ባልሆነበት እንደፌዴራል ጉዳይ ተቆጥሮ የተወሰነበት የክርክር አመራር ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑና ጉዳዩ የክልል ጉዳይ ስለሆነ እንደአዲስ ክስ ቀርቦበት ሥልጣን ባለዉ በሐረሪ ክልል ፍርድ ቤት ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ከመሆኑ አንጻር በማየት ከዚህ አኳያ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዘንድ የተፈጠረዉን የክርክር አመራር ጉድለት አልፈነዋል፡፡ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17912 ላይ በቀን 26/01/2012 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04953 ላይ በቀን 22/10/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በመሻር የወሰነዉና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁጥር 00124 ላይ በቀን 24/03/2013ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. ይህ ዉሳኔ አመልካች ሥልጣን ባለዉ የክልሉ ፍርድ ቤት ክስ ከማቅረብ አያግዳቸዉም፡፡
3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡- 202486

ቀን፡-30/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ አዲሱ ዓለሙ- አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ መስከረም ንጉሴ- ጠበቃ ዳጨው ዳመና- ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር መዝገቡ የቀረበው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ የአመልካች ሚኒባስ መኪና በሆነ ተሳፍረን በምንንዝበት ጊዜ ከቆመ ተሸከርካሪ ጋር በመጋጨቱ በቀኝ እግሬ የታፋ አጥንት እና በግራ እግሬ ከጉልበት በታች አጥንት ስብራት በመድረሱ 28% ቋሚ አካል ጉዳት ደርሶብኛል፡፡ የጉዳት ካሣ ብር 406,230.00፣ የሕክምና ወጪ ብር 90,770.00፣ የአልሚ ምግብ ወጪ ብር 2,000.00 እና የሞራል ካሣ ብር 1,000.00 በድምሩ ብር 500,00.00 አመልካች እንዲከፍሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች የሠጡት መልስ በንግድ ሕጉ መሠረት በውል ስትንዝ ነው ጉዳቱ የደረሰው፣ የቀረበው የጉዳት

መጠን የተጋነነ የሚል ሲሆን ለመኪናው የመድን ሽፋን የሠጠው መድን ድርጅት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ የጉዳት ካሣ ብር 350,844.00፣ የሕክምና ወጪ ብር 90,770.00፣ የምግብ ብር 2,000.00 እና የሞራል ካሣ ብር 1,000.00 አመልካች እንዲከፍል እና የመድን ሽፋን የሠጠው ድርጅት ብር 40,000.00 እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ በመዝገብ ቁጥር 180599 የተሰጠው ውሳኔ ጉዳቱ የደረሰው ተጠሪ ተሳፍረው በሚጓዙበት ጊዜ ስለሆነ በንግድ ሕግ ሊገዛ ይገባል፤ የአመልካች ኃላፊነት የሚወድቀው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 597(1) ስር ነው ወይስ በአንቀጽ 599 የሚለውንና የጉዳት ካሣውን በርትዕ እንዲወስን ጉዳዩን ለሥር ፍርድ ቤት መልሷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ከተመለሰለት በኋላ ጉዳቱ የደረሰው በአጓዡ ጥፋቱ ነው ወይስ አይደለም ለሚለው ጭብጥ ግራቀኙ ማስረጃ መስማት ሳያስፈልግ የትራፊክ ሪፖርት እንዲቀርብ ባሳሰቡት መሠረት ማስረጃውን በማስቀረብ መዝኖ ጉዳቱ የደረሰው በአጓዡ ጥፋት መሆኑ ስለተረጋገጠ የአመልካች ኃላፊነት በንግድ ሕጉ ቁጥር 599 መሠረት የሚወድቅ ስለሆነ ተጠሪ በጉዳቱ ምክንያት በቤታቸው የሠራተኛ ወጪ የሚያስከትልባቸው በመሆኑና ወደሥራ ሲሄዱ የሚያስፈልገውን የትራንስፖርት ወጪ በቀሪ ዕድሜያቸው ጊዜ በማስላት የጉዳት ካሣ ብር 228,000.00፣ የሕክምና ወጪ ብር 90,770.00፣ የምግብ ብር 2,000.00 እና የሞራል ካሣ ብር 1,000.00 ለተጠሪ እንዲከፍልና መድን ድርጅት ከሚከፍለው ብር 40,000.00 ውጭ ያለውን ካሣ አመልካች እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ይግባኝ እና የሠበር አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዘዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የሥር ፍርድ ቤት በ21/12/2012 ዓ/ም ተጨማሪ ማስረጃው ሊያያዝ አይገባም በማለት ብይን ከሰጠ በኋላ ብይኑን በራሱ ሽሮ የትራፊክ ሪፖርቱን በመቀበል መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ከተመለሰ በኋላ አዲስና ተጨማሪ ማስረጃ ሊቀበል አይገባም፡፡ ቋሚ የአካል ጉዳቱ 28% ሆኖ እያለ በ100% ጉዳት ካሣው መሰላቱ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ተመልክቶ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው መመሪያ መሰረት መወሰን አለመወሰኑን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪ የሠጡት መልስ ግራቀኛችን የሠው ማስረጃ አናሰማም በትራፊክ ሪፖርት መሠረት ይወሰን በማለት ባሳሰብነው መሠረት ማስረጃው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቀርቦ ተመዛዝኖ መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ ለተያዘው ጭብጥ አስፈላጊ ማስረጃ ተቀብሎ ካሣውን በርትዕ አመዛዝኖ ተገቢ ነው ተብሎ ሊጸና ይገባል ብለዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራኙን ክርክር፣ የሠበር አጣሪ ችሎት የያዘውን ጭብጥ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ያቀረቡት ክስ የአመልካች ሚኒባስ መኪና በሆነ ተሳፍረን በምንጓዝበት ጊዜ ከቆመ ተሽከርካሪ ጋር በመጋጨቱ በቀኝ እግሬ የታፋ አጥንት እና በግራ እግሬ ከጉልበት በታች አጥንት ስብራት በመድረሱ 28% ቋሚ አካል ጉዳት ደርሶብኛል፡፡ የጉዳት ካሣ ብር 406,230.00፣ የሕክምና ወጪ ብር

90,770.00፣ የአልሚ ምግብ ወጪ ብር 2,000.00 እና የሞራል ካሣ ብር 1,000.00 በድምሩ ብር 500,00.00 አመልካች እንዲከፍሉ የሚል ሲሆን አመልካች በበኩሉ በንግድ ሕጉ መሠረት በውል ስትንገዝ ነው ጉዳቱ የደረሰው፣ የቀረበው የጉዳት መጠን የተጋነነ በማለት ተከራክሯል። ጉዳዩ ቀደም ሲል እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ በመዝገብ ቁጥር 180599 ሚያዚያ 29 ቀን 2012 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔ ጉዳዩ በንግድ ሕጉ እንዲገዛ እና አንገቡ ጥፋት ያለበት መሆን አለመሆኑ በጭብጥነት ተመርመሮ እንዲወሰን ለሥር ፍርድ ቤት መልሷል። የተመለሰለት ፍርድ ቤት ግራቀኙ ማስረጃዎቻቸውን ለማሰማት ባለመፈለጋቸውና የአንገቡ ጥፋት መኖር አለመኖር በትራፊክ ሪፖርት ተመስርቶ እንዲወሰን ማስረጃው እንዲቀርብ ባሳሰቡት መሠረት ማስረጃውን አስቀርቦ አንገቡ ጥፋት ያለበት ስለሆነ የአመልካች ኃላፊነት የሚወሰነው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 599 መሠረት ነው ሲል ድምዳሜ ላይ ደርሷል።

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው የሥር ፍርድ ቤት በ21/12/2012 ዓ/ም ተጨማሪ ማስረጃው ሊያያዝ አይገባም በማለት ብይን ከሰጠ በኋላ ብይኑን በራሱ ሽሮ የትራፊክ ሪፖርቱን በመቀበል መወሰኑ እና ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ከተመለሰ በኋላ አዲስና ተጨማሪ ማስረጃ መቀበሉ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም በማለት ተከራክረዋል። ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል። ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የመለሰው አንገቡ ጥፋት ያለበት መሆን አለመሆኑ በጭብጥነት ተይዞ እንዲወሰን ሲሆን የተመሰረተው የፍሬ ነገርን ጭብጥ ያካተተ በመሆኑ ጉዳዩ በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚገባው ነው። አመልካችና ተጠሪ በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዘረዘሯቸውን ማስረጃ ማሰማት እንዳልፈለጉና የፍሬ ነገር ጭብጡ በትራፊክ ሪፖርት መሠረት እንዲወሰን ማስረጃው እንዲቀርብ እንዲታዘዝ ያመለከቱ ስለመሆኑ ከውሳኔው ግልባጭ ይዘት ተገንዝበናል። ፍርድ ቤት የማስረጃው መቅረብ አምኖበት ከአሶሳ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ማስረጃው እንዲያቀርብ ማዘዙም ጉዳዩ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 መሠረት መመራቱን ያመላክታል። በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 መሰረት ተከራካሪዎች ካቀረቧቸው የሠው ሆነ የሠነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ ለክርክሩ አወሳሰን ጠቃሚ የሆነ ማስረጃ ፍርድ ቤቱ የማስቀረብ ስልጣን እና ኃላፊነት እንዳለበት ያስገነዝባል። ሕጉ ኮመን ሎው እና ኮንቲኔንታል ሎው የሕግ ሥርዓት የሚከተሉ ሀገሮችን አጣምሮ የያዘ እና ከኮመን ሎው የህግ ሥርዓት ከሚከተሉ ሀገሮች በተለየ ለዳኛው ጉዳዩንና ግራቀኙ የሚያቀርቡትን ማስረጃ ከማዳመጥ ያለፈ ተግባር እንደሰጠው ያሳያል። ድንጋጌው እውነትን የመፈለግ ዓላማ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ እንዳለው የሚያሳይ እና ዓላማው እንዲሳካ የማድረግም ኃላፊነት የዳኛውም እንደሆነ ያስረዳል። ወደሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩ የተመለሰው በፍሬ ነገር ጭብጥ ተመስርቶ ከመሆኑ አኳያ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ከተመለሰለት በኋላ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግና ፍትሐዊነትን ሊያሳካ በሚችል መልኩ ማስረጃውን እንዲቀርብ ከማድረግ ሕጉ የመከልከል ሀሳብ አለው ሊባል አይችልም። ተጠሪ የሕክምና ማስረጃና የትራፊክ ሪፖርት በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርብላቸው ጠይቀው የሥር ፍርድ

ቤት በ21/12/2012 ዓ/ም የሕክምና ማስረጃ ሊያያዝ የማይገባው ስለመሆኑ ብይን የሠጠ ቢሆንም አሁን አከራካሪ ሆኖ የቀረበው የትራፊክ ሪፖርት በተመለከተ የሠጠው ትዕዛዝ ባለመኖሩ በክርክሩ ሂደት ማስረጃውን አስቀርቦ መዝኖ መወሰኑ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የማስረጃ አቀባበል ሆነ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘውም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ተሳፍረውበት የነበረው ሚኒባስ በፍጥነት ሲሽከረከር መንገዱን ለቆ ከቆመ ከባድ ሎቤድ ተሽከርካሪ ጋር መጋጨቱ የተረጋገጠ ነው በሚል በንግድ ሕጉ አንጽ 599 መሠረት ጉዳቱ የደረሰው በአጓዡ ጥፋት ስለመሆኑ ድምዳሜ ላይ መድረሱን ይሕ ሰበር ሰሚ ችሎትም የሚቀበለው ነው፡፡ ተጠሪ ዘለቄታዊ የአካል ጉዳቱ 28% መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ጉዳት ከደረሰባቸው በኋላም መደበኛ ሥራቸው የቀጠሉ በመሆኑ በቀጥታ የገቢ መቋረጥ ያላስከተለ ቢሆንም በተጠሪ እግር ላይ የደረሠው ጉዳት ዘላቂ በመሆኑ አሁን የሚሠሩትን የሥራ ዓይነት ማከናወን ቢችሉም እንኳን ለወደፊት ማንኛውንም ዓይነት የሥራ ተግባር ማከናወን ላይ እክል እንደሚሆንባቸውና አጠቃላይ የመሥራት አቅማቸውን እንደሚቀነስ ይገመታል፡፡ የጉዳት ካሣ ሲወሰን ግምት ውስጥ መግባት ከሚኖርበት ጉዳይ አንዱ በአጠቃላይ በተጎጂው ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት እንደሰው በአጠቃላይ የመሥራት ኃይል ቅነሳ /General utility/ እንደሆነ በሰበር ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 19338 አስገዳጅ ትርጉም የተሠጠበት ነው፡፡ በአጠቃላይ የመሥራት ኃይል መቀነሱ ለወደፊት የሚደርስ ጉዳት (future damage) እንደሚያስከትል የሚታወቅ ሲሆን ትክክለኛ ጉዳቱ ግን ለማወቅና ለመለየት ስለሚያስቸግር በፍ/ሕ/ቁ. 2102 እንደተመለከተው ጉዳት መድረሱ ተረጋግጦ ነገር ግን የጉዳት መጠኑን ማወቅ ካልተቻለ ካሣውን በርትዕ መወሰን ይችላል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በርትዕ ካሣውን ለማስላት ተጠሪ በጉዳቱ ምክንያት ከሚያጡት ገቢ አንጻር ሳይሆን ጉዳቱ ከሚያስከትለው ተጨማሪ ወጪ በመነሳት በቤታቸው የሠራተኛ ወጪ የሚያስከትልባቸው በመሆኑና ወደሥራ ሲሄዱ የሚያስፈልገውን የትራንስፖርት ወጪ በቀሪ ዕድሜያቸው ጊዜ በማስላት የጉዳት ካሣ ብር 228,000.00 መወሰኑ ተጠሪ ሙሉ ገቢያቸውን እንዳጡ አድርጎ እንዳሰላው ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቱ ምክንያታዊ የሆኑ ጉዳዮችን በመያዝ ካሣውን በርትዕ መወሰኑ ሆነ የሕክምና ወጪ ብር 90,770.00፣ ለምግብ ብር 2,000.00 እና የሞራል ካሣ ብር 1,000.00 አመልካችና በሥር ፍርድ ቤት ለተሸከርካሪው የመድን ሽፋን የሠጠው ጣልቃ ገብ በየድርሻቸው እንዲከፍሉ ውሳኔ መስጠቱ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

## ውሳኔ

1. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 11078 ጥር 20 ቀን 2013 ዓ/ም፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 11058 ጥር 05 ቀን 2013 ዓ/ም እና የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12050 ታህሳስ 08 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**<u>ትዕዛዝ</u>**

- **የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡**
- **አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ**
- **መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ዜ/መ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 202114

ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካቾች**- 1. ሀድሌ ኢብራሂን

2. ኡመር ኢብራሂን

3. መሀመድ አደን

4. ኡመር መታን

5. መሀመድ አህመድ አብዲ

6. መታን መሀመድ

7. መሀመድ አረብ

**ተጠሪዎች**- 1. ጠይብ አብዲላሂ

2. አህመድ ጣሂር አብዲላሂ ሸያ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ እርሻ መሬትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረውም በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋፈን ዞን ጅግጅጋ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካቾች ከሳሽ፣ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡተ ክስ በሰሀሊቲ ቀበሌ ኮጃርታ ሼህ ጣሂር ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ በሰሜን ሀጂ መሀመድ

እና የጎሳ ቦታ፣ በምዕራብ ሙሳ አውሌ፣ በደቡብ ተጠሪዎች፣ በምስራቅ የአመልካቾች መሬት የሚያዋስኑትን ስፋቱ 4 ጋሻ፣ ርዝመቱ ደግሞ 7.5 ጋሻ ጠቅላላ መጠኑ 30 ጋሻ የሆነ የእርሻ መሬት ያለአግባብ ይዘውብናል፤ እንዲለቁልን ብንጠይቃቸው ፍቃደኛ ስላልሆኑ ለቀው እንዲያስረክቡን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀው ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ የያዝነው የአመልካቾች መሬት የለም፤ አመልካቾች ከክሳቸው ጋር ያቀረቡት የባለቤትነት ማስረጃ የለም፤ ክስ የቀረበበትን መሬት ከአባታችን በውርስ ያገኘነው የተጠሪዎች ይዞታ ነው፤ ከበፊት ጀምሮ ስናርሰው የነበርነውም እኛ ነን፤ በዚህ ጊዜ ውስጥም አመልካቾች መሬቱ ይገባናል የሚል ጥያቄ አላቀረቡም፤ አመልካቾች መሬቱን እንዴት እና መቼ እንዳገኙት፤ መቼስ ከይዞታቸው እንደወጣ አልገለጹም፤ አመልካቾች ወደ አካባቢው የገቡት መሬት ገዝተው ሲሆን የገዙትን መሬት የነካባቸው ሰው የለም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲደረግላቸው ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ካደመጠና ከመረመረ በኋላ የአመልካቾችን ክስ ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች መሬቱን ሊለቁ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በወረዳ ፍርድ ቤቱ የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካቾች አሁንም በውሳኔው ባለመስማማት ለክልሉ ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ በአመልካቾች የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች በቀን 01/06/2013 ዓ.ም በተፃፈ 02 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ አከራካሪው መሬት የገጠር እርሻ መሬትን የሚመለከት ሲሆን የሚገዛውም በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 128/05 ነው፤ በአዋጁ መሠረት ደግሞ ጉዳዩ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ከመሄዱ አስቀድሞ በአካባቢው በሚገኝ ገበሬ ማህበር ጽ/ቤት፣ ማህበራዊ ፍርድ ቤት፣ በአካባቢ ሽማግሌዎች እና በጎሳ መሪዎቹ መታየት እንዳለበት ቢደነግግም የስር ፍርድ ቤቶች የአዋጁን መኖር ዘንግተው ጉዳዩ በዚህ መንገድ እንዲያልፍ አለማድረጋቸው ወይም ትዕዛዝ አለመስጠታቸው፤ ክሱን ያቀረብነውና ዳኝነት የጠየቅነው አመልካቾች ሆነን እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ባልተጠየቀ ዳኝነት ላይ መሬቱ የተጠሪዎች ነው በማለት መወሰናቸው፤ እንዲሁም አመልካቾች ክስ ያቀረብንበት መሬት ስፋት 4 ጋሻ በ7.5 ጋሻ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ግን ከተጠየቀው ዳኝነት በመውጣት ስፋቱ 16 ጋሻ በ5 ጋሻ የሆነ መሬት ላይ ውሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡ ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ያስቀርባል ከመባሉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ጥሪ የተደረገላቸዉ ቢሆንም ባለመቅረባቸዉ በሌሉበት ክርክሩ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር

እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመረዉም አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት የእራሳቸዉ መሆኑን በመግለጽ ሲሆን፣ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ከአባታቸዉ አብዱላሂ ሺዴ የወረሱት የእራሳቸዉ እንጂ የአመልካቾች አለመሆኑን ገልጸዉ ተከራክረዋል። የግራ ቀኝ ክርክር ይህ ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) መሠረት መያዝ የሚገባዉ ትክክለኛ ጭብጥ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት የአመልካቾች ነዉ ወይስ ተጠሪዎች ከአባታቸዉ በዉርስ ያገኙት ነዉ? የሚል ነዉ። ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የወረዳዉ ፍርድ ቤትም በዚሁ መሠረት የግራ ቀኝ ምስክሮችን በመስማት እንዲሁም መሬቱ ከሚገኝበት ቦታ በአካል በመሄድ አጣርቶ ይህንኑ ከግራ ቀኝ ምስክሮች ቃል አንፃር በመመርመር እና በመመዘን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት በተጠሪዎች እጅ ያለ እና አመልካቾች መሬቱን ይዘዉት እንደማያዉቁ እና በመሬቱም ላይ መብት እንደሌላቸዉ በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጧል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ስለመሆኑ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። ከማስረጃ አቀራረብ እና የምዘና መርህ ጋር በተያያዘ የተፈጸመ ስህተት ካለ እንደመሠረታዊ የህግ ስህተት ታይቶ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል ቢሆንም በተያዘዉ ጉዳይ ከማስረጃ አቀራረብ እና የምዘና መርህ ጋር በተያያዘ የተፈጸመ ግድፈት ስለመኖሩ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ አያሳይም። በመሆኑም አመልካቾች ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ መሬት ላይ መብት የላቸዉም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም።

በሌላ በኩል ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ መሬት ላይ መብት እንዳላቸዉ እና በተጠሪዎች በህገ ወጥ መንገድ የተያዘባቸዉ ስለመሆኑ አመልካቾች በክሳቸዉ መሠረት የማስረዳት ሸክም ያለባቸዉ ሲሆን ይህን ግዴታቸዉን አልተወጡም፤ በአንፃሩ መሬቱ ከተጠሪዎች እጅ ወጥቶ በእጃቸዉ (በአመልካቾች) ገብቶ እንደማያዉቅ የተጠሪዎች ምስክሮች ያስረዱ ቢሆንም ይህ መሆኑ የአመልካቾችን ክስ ዉድቅ የማድረግ ዉጤት ከሚያስከትል በስተቀር ፍርድ ቤቱ መሬቱ የተጠሪዎች ነዉ በሚል እንዲወስን ምክንያት ሊሆን አይችልም። በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ከመሬቱ መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ እና በተጠሪዎች ያላግባብ የተያዘ ስለመሆኑ በክሳቸዉ መሠረት ማስረዳት ካልቻሉ እና/ወይም ይህ ክርክራቸዉ በተጠሪዎች ምስክሮች መስተባበሉን ከተረዱ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ መቆም ሲገባቸዉ ከዚህ በላይ በመሄድ መሬቱ የተጠሪዎች እንዲሆን "ወስኘላቸዋለሁ" በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የሥነ ሥርዓት ግድፈት፣ በተለይም የፍርድ ቤቶች ዉሳኔ በተጠየቀዉ ዳኝነት ላይ የተገደበ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 182 ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ የሚቃረን፣ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል። ተከታዩም ተወስኗል።

## ዉሳኔ

1. የጅጅጋ ደቡብ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1411/2011 በቀን 10/10/2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የፋፊን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 052-34/11/12 በቀን 12/05/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 05-1-201/12 በቀን 02/03/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ ተሻሽለዋል፡፡

2. አመልካቾች ከመሬቱ መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት የዳኝነት ጥያቄያቸዉን ዉድቅ በማድረግ የተሰጠ የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፤ መሬቱ የተጠሪዎች ነዉ በሚል የተሰጠ ዳኝነት ተሽሯል፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

***ሠ/ኃ***

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መ/ቁ/202092

ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡ ግርማ ለገሠ ተምትሜ፡- ቀረቡ

ተጠሪ፡ የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሳሽ ፤የአሁኑ ተጠሪ (ተከሳሽ) በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከጥር 13 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ በሾፌር ስራ መደብ ላይ እየሰራሁ እያለሁ ተጠሪ ድርጅት የጡረታ መውጫ ጊዜህ ከሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን በቁጥር ፕ/ሰ/ድ/386/2011 በቀን 18/11/2011 ዓ.ም ስራዬን እንዳቆም በደብዳቤ በግለጸልኝ መሰረት አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አሟልቼ ስራዬን ከለቀቅኩኝ በኋላ ጡረታ ሚኒስቴር በመመላለስ የጡረታ አበል ለመቀበል እንዲችል በምጠይቅበት ጊዜ የጡረታ መውጫ ጊዜዬ ሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ሳይሆን ከሐምሌ 1 ቀን 2013 ዓ.ም መሆኑን ገልጸውልኝ ወደ ስራዬ እንዲመለስ ጡረታ ሚኒስቴር ለተጠሪ ሲጽፍ ተጠሪ ድርጅት ወደ ስራ እንዲመለስ እና ደመወዝ እንዲከፈለኝ ሲጠይቅ ፍቃደኛ ባለመሆኑ የጡረታ መውጫ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጊዜዬ እስኪደርስ ወደ መደበኛ ስራዬ እንዲመልሰኝ እና የተቋረጠብኝ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም እንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ዳኝነት ያቀረበ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የሰጠው መልስ የአመልካች ሥራ የተቋረጠው በተጠሪ ጥፋት ሳይሆን አመልካች ሲቀጠር የሕይወት ታርክ ቅጽ ሲሞላ የተወለደበት ቀን ራሱ የሞላው መሰረት ተድረጎ ስህተት የተፈጠረው አመልካች በሌላ ድርጅት ሲቀጠር የሞላው የትውልድ ዘመን እና በተጠሪ ድርጅት ሲቀጠር የሞላው የትውልድ ዘመን ሲጣራ የጡረታ እድሜ ያልደረሰ መሆኑን የጡረታ ሚኒስቴር ያረጋገጠ ሲሆን ተጠሪ ድርጅትም ከመስከረም 27 ቀን 2012 ዓ.ም ስራ እንዲጀምር ቢጠየቁም ውዝፍ ደመወዝ ካልተከፈለኝ በማለት ፍቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል፡፡ ስለዚህ ወደ ስራ ቢመለስ ተቃውሞ የለንም፤ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ እንዲከፈለው የጠየቀው ውድቅ እንዲሆን በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ወደ ስራው እንዲመለስ የተባለው ተጠሪም ተቃውሞ የሌለው በመሆኑ ተጠሪ ድርጅት አመልካችን ወደ መደበኛ ስራቸው እንዲመልሱ በማለት ሲወስን ውዝፍ ደመወዝ በተመለከተ የአመልካች የጡረታ መውጫ ጊዜ ላይ ስህተት የተፈጠረው አመልካች በሞሉት የሕይውት ታሪክ ስለመሆኑ እና ወደ ስራ እንዲመለሱ በተደጋጋሚ ጥሪ ተደርጎላቸውም ፍቃደኛ አለመሆናቸውን አስረድተዋል፣ ስለዚህ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ 377/96 አንቀጽ 54(1) ደመወዝ የሚከፈለው ለተሰራ ስራ ብቻ እንደሆነ የሚደነግግ ሲሆን አመልካች በራሳቸው ጉድለት ላልሰሩበት ጊዜ ያለውን ደመወዝ ይከፈለኝ በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበው ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የተሰጠው ውሳኔ የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ግድፈት አልተገኘበትም በማለት ይግባኙን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞበታል፡፡

አመልካች በውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽመዋል በማለት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፤ተጠሪ የጡረታ መውጫ ጊዜዬን ከሀምሌ 01 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን ሀምሌ 18 ቀን 2011 ዓ.ም በደብዳቤ ሲያሳውቀኝ ከጡረታ ሚኒስቴር ሳያረጋግጥ ነው፣ አንድ ሰራተኛ ለጡረታ ሲዘጋጅ አሰሪው ከ3 እና 4 ወራት አስቀድሞ ለማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ አመልክቶ ኤጀንሲውም ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጦ የጡረታ መለያ ቁጥር አስቀድሞ ተሰጥቶት በደብዳቤ የሚያሳውቅ ሲሆን ተጠሪ ይህንን ሳያደርግ ከስራ ማስወጣቱ አግባብ የሌለው ሲሆን የጡረታ ሚኒስቴር መስከረም 26 ቀን 2012 ዓ.ም ተጠሪን በደብዳቤ ያሳወቀው ሲሆን ይህንን ካወቀ በኋላም ወደ ስራ ለመመለስ ፍቃደኛ ባለመሆኑ በስር

ፍ/ቤት ገልፀን እያለ ይህንን ሳይመረምር ደመወዝ አይከፈልም ማለቱ ስህተት ነው፡፡ ስለዚህ ተጠሪ የጡታ መውጫ ጊዜ እርግጠኛ ሳይሆን ጡረታ ውጣ ብሎኝ ለከፍተኛ እንግልት እና ችግር ዳርጎኝ ያለደመወዝ ወደ ስራ እንዲመለስ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ከሐምሌ 01 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ስራ እስከ ጀመርኩበት ድረስ ያልተከፈለኝ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም እንዲከፈለኝ እንድወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የሰበር አመልካች የጡረታ ጊዜወ ሳይደርስ መውጣቱ ከመረጋገጡ አኳያ የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪው ውዝፍ ደመወዝ የመክፈል ሀላፊነት የለበትም የመባሉን አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ታዟል፡፡

ተጠሪ ያቀረበው መልስ ባጭሩ አመልካች በተጠሪ ድርጅት ሲቀጠር የተወለደበት ቀን በአግባቡ መሙላት ሲገባው በቀድሞ መ/ቤት የሞላውን የትውልድ ቀን የተለየ የትውልድ ዘመን በመሙላቱ በራሱ ችግር የተፈጠረ ስህተት ነው፡፡ ተጠሪም አመልካች በሞላው የትውልድ ዘመን መሰረት የጡረታ መውጫ ጊዜ ስለደረሰ ለአመልካች እና ለጡረታ ሚኒስቴር በማሳወቅ ሰነዶቹን አደራጅቶ የላከው ሲሆን አመልካች በራሱ በሞላው ታሪክ የጡረታ ጊዜ ስለደረሰ የስራ ውል የተቋረጠ እንጂ ተጠሪ የፈፀመው ስህተት የለም፣ የጡረታ ማህበራዊ ኤጀንሲ ባደረገው ማጣራት በሌላ መ/ቤት በሞላው የትውልድ ዘመን የአመልካች የጡረታ መውጫ ጊዜ ሐምሌ 2013 ዓ.ም እንደሆነ መስከረም 26 ቀን 2012 ዓ.ም በደብዳቤ ባሳወቀን መሰረት አመልካች ወደ ስራ እንዲመለስ ሲጠየቅ የሀምሌ፣ ነሐሴ እና መስከረም ወር ደመወዝ ካልተከፈልኝ በማለት ፍቃደኛ ሳይሆን መቅረቱ በስር ፍ/ቤት በሰነድ እና በሰው ምስክሮች ተረጋግጦ የውዝፍ ደመወዝ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለውም፣ ስለዚህ አመልካች በራሱ ምክንያት ስራ አልሰራም በማለት ላልሰራው ስራ ደመወዝ እንዲከፈለው የጠየቀው የስር ፍ/ቤቶች ውድቅ ማድረጋቸው የህግ ስህተት የለዉም ተብሎ እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡አመልካቾች አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበዉ የዳኝነት ጥያቄ ሁለት ናቸዉ፡፡አንደኛዉ የጡረታ መዉጫ ጊዜ አልደረሰም ስለተባለ ወደ ስራ እንዲመለስ የሚል ሲሆን ሁለተኛዉ ያልተከፈለዉ ደመወዝ

እንዲከፈል እንዲወሰን የሚል ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን አጣርቶ ተጠሪ አመልካችን ወደ ስራ እንዲመልስ የወሰነ ሲሆን ክፍያን በተመለከተ ግን ስህተቱ የተፈጠረዉ አመልካች የቅጥር ዉል ላይ የሞላዉ የትዉልድ ቀንና ዘመን ስህተት መሆኑ ስለተረጋገጠ ነዉ በሚል እና የጡረታና ማህበራዊ ኤጀንሲ ከወሰነ በኋላ በራሱ ጉድለት ወደ ስራ ባለመመለሱ ያልሰራበት ደመወዝ አይከፈለዉም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን መዝገቡ ያሣያል፡፡አመልካች አሁንም አጥብቆ የሚከራከረዉ የጡረታ ጊዜ ሳይደርስ ያሠናበተኝ ተጠሪ ስለሆነ የተቋረጠዉን ደመወዝ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ነዉ፡፡

በህግ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር ደመወዝ የሚከፈለዉ ለተሰራ ስራ ብቻ መሆኑን ነገር ግን ሰራተኛዉ ለስራ ዝግጁ ሆኖ ሳለ ለስራ አስፈላጊ የሆነዉ መሳሪያ ወይም ጥሬ እቃ ሳይቀርብ በመቅረቱ ወይም በሰራተኛዉ ጉድለት ባልሆነ ምክንያት ሳይሰራ ቢዉል ደመወዙን የማግኘት መብት እንዳለዉ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 54ላይ ተደንግጓል፡፡ከዚህም የምንገነዘበዉ አሰሪ ደመወዝ ለመክፍል የሚገደደዉ አንድም ሰራተኛዉ ስራ የመስራት ግዴታዉን የተወጣ ከሆነ ሲሆን በሌላ በኩል ሰራተኛዉ ለስራ ዝግጁ ሆኖ በአሰሪዉ ጉድለት ሳይሰራ ከቀረ ስለመሆኑ ነዉ፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ያከራከረዉ ለጡረታ ደርሰሃል ተብሎ ከተጠሪ መ/ቤት ከተሰናበትበት ሐምሌ ወር 2011ዓ.ም ጀምሮ ጉዳዩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዉሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ያለዉ ደመወዝ ክፍያ የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች በዚህ ጊዜ ዉስጥ ስራ ላይ እንዳልነበር አላከራከረም፡፡ስራ ላይ ያልተገኘዉ ተጠሪ በፈጸመዉ ጥፋት ወይም ስህተት ነዉ በማለት ሲሆን ፍሬነገር የማረጋገጥ እና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጠዉ የሥር ፍርድ ቤት የጡረታ መዉጫ የቀን አቆጣጠር ስህተት የተፈጠረዉ አመልካች ለተጠሪ ባቀረበዉ መረጃ ላይ የተፈጠረ ስህተት ስለመሆኑ ተጠሪ በተሻለ ሁኔታ ማስረዳቱን አረጋግጧል፡፡ስለዚህም አመልካች ስራ ላይ ያልተገኘዉ ተጠሪ ሆነ ብሎ በፈጸመዉ ድርጊት ወይም ስህተት መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ ከሐምሌ እስከ መስከረም ወር ሰራተኛዉ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የመክፈል ሃላፊነት የሚወስድበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡በሌላ በኩል ጉዳዩ በማህበራዊ ዋስትና አጀንሲ በኩል ተጣርቶ ወደ ስራ እንዲመለስ ከተባለበት መስከረም 26 ቀን 2011ዓ.ም በኋላ ላለዉ ጊዜ ተጠሪ ወደ ስራ እንዲመለስ ጥሪ ተደርጎለት ከሐምሌ እስከ መስከረም ያለዉ ደመወዝ ካልተከፈለኝ በሚል ከተጠሪ ጋር በተፈጠረ አለመግባባበት ስራ ሳይጀምር እንደቆየ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ጉዳይ ነዉ፡፡አመልካች ወደ ስራ እንዲመለስ ከተባለበት ቀን አንስቶ ስራዉን እየሰራ ሌላዉን የመብት ጥያቄ በህግ አግባብ መጠየቅ ሲገባዉ የበኩሉን ግዴታ እንዳልተወጣ እና

ይህንን ሁሉ ጊዜ ያልሰራበት ደመወዝ እንዲከፈል መጠየቁ ምክንያታዊነት የሌለዉ መሆኑን ያሣያል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የጡረታ ጊዜ ሳይደርስ ጡረታ እንዲወጣ የተደረገዉ ራሱ በሰጠዉ መረጃ ስህተት መነሻ መሆኑ ከመረጋገጡም ባሻገር ጉዳዩ ተጣርቶ ወደ ስራ እንዲመለስ ሲጠየቅም በጊዜዉ ስራ ሳይጀምር በራሱ ጉድለት ስራዉን ሳይሰራ ለቀረበት ጊዜ ተጠሪ ደመወዝ እንዲከፍል የሚገደድበት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን በማረጋገጥ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አልተገኘም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1ኛ/የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/75623 ላይ በ14/08/2012ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ./ቁ/250131 ላይ በ13/04/2013ዓ.ም የሰጠዉ ብይን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡ 2ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**<u>መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡</u>**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

***ሠ/ኃ***

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-201990

ቀን፡-01/02/2014ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ማክሼቭ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- ወጋገን ባንክ አክሲዮን ማህበር- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የብድር ውል ይፍረስልኝ በሚል የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ታህሳስ 18 ቀን 2012 ዓ.ም በተፃፈ ክስ ከተጠሪ ጋር ሚያዝያ 11 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል ስምምነት ብር 2,631,246.08 መበደሩን፣ አከፋፈሉም ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በየሶስት ወሩ ሁኖ ወለድና የተለያዩ ወጪዎችን ጨምሮ ብር 349,124.00 መሆኑንና በ8 ጊዜ ክፍያ በ2 ዓመት ውስጥ እስከ ሚያዝያ 11 ቀን 2013 ዓ.ም ተከፍሎ እንዲጠናቀቅ መስማማታቸውን ነግር ግን ተጠሪ ክፍያው በ7 ጊዜ እንዲጠናቀቅ ማድረጉን፤ ይህም የሒሳብ መዝገብ አያያዝ ላይ ችግር መፍጠሩን፤ የወለድ መጠኑ ላይም ከፍተኛ ልዩነት በማምጣት የተስተካከለ የአዲት ሪፖርት እንዳይኖር እክል መፍጠሩን፤

በዚህም ምክንያት አመልካች የ2012 ዓ.ም የግብር ክሊራንስ አግኝቶ የንግድ ፍቃዱን ለማሳደስ አለመቻሉን እና ተጠሪም ይህን ለማስተካከል ፍቃደኛ አለመሆኑን ጠቅሶ የብድር ውሉ እንዲፈርስ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ የካቲት 24 ቀን 2012 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የብድር ስምምነቱ የተደረገው አመልካች ከመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ጋር ባደረገው የማሽነሪ አቅርቦት ውል መሰረት ግዴታውን ባለመወጣቱ ተጠሪ በሰጠው መጠኑ ብር 2,631,246.08 የሆነ የቅድመ ክፍያ እና የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና መሰረት ለመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ሰኔ 28 ቀን 2010 ዓ.ም ክፍያ በመፈፀሙና ይህ የአመልካች እዳ ወደ ብድር ውል እንዲዞር በመስማማታችን ነው፡፡ እዳው በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ በየ3 ወሩ በ8 ጊዜ ተከፍሎ የሚያልቅ ሲሆን በዚህ ላይ ምንም አይነት ልዩነት አልተደረገም፡፡ በውሉ በተገለጸው እና በታሰበው ሒሳብ ላይ ልዩነት የመጣው ተጠሪ እዳውን ለመሰቦ ሲምንቶ ፋብሪካ ከከፈለበት ጊዜ አንስቶ የብድር ውሉ እስከተደረገበት ሚያዝያ 10 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ የታሰበ ወለድ ነው፡፡ በመሆኑም ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪ ክፍያውን በ7 ጊዜ እንዳጠናቅቅ አስገድዶኛል በሚል አመልካች ለውሉ መፍረስ በምክንያትነት የጠቀሰው ከውሉ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ አይደለም፡፡ ውሉን ተከትሎ ባለ አፈፃፀም ተጠሪ በፃፈው ደብዳቤ ላይ የተፈጠረ እክል በመሆኑ ደብዳቤው እንዲሰረዝ ወይም በውሉ መሰረት እንዲፈፀም አመልካች መጠየቅ እየቻለ በፍ/ሕ/ቁ 1784 እና 1785 መሰረት አይነተኛ የውል መጣስ በሌለበት ውሉ እንዲፈርስ መጠየቁ ተገቢ አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታውን ያቀረበ ሲሆን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት በመሰረዙ ጥር 28 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ ሰበር አቤቱታውን አቅርቧል፡፡

የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ብድሩ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ በየ3 ወሩ ለ8 ጊዜ ተከፍሎ እንዲያልቅ ስምምነት የተደረገበት መሆኑን ነገር ግን በአፈፃፀም ሒደት በ7 ጊዜ እንዲከፈል መደረጉን ተጠሪ ባልካደበት የፍ/ሕ/ቁጥር 1784 እና 1785 ድንጋጌዎች እንደማያሟላ ተደርጎ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄው ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ቢባል እንኳ በአማራጭ በተጠየቀው ዳኝነት መሰረት ቀሪውን የብድር እዳ በሚመለከት አመልካች እና ተጠሪ መጀመሪያ በተደረገው ስምምነት መሰረት ውላቸውን ሊያሻሽሉ ይገባል ተብሎ መወሰን ነበረበት፡፡ እንዲሁም በግራ ቀኙ የተጠቀሱ ምስክሮች ሳይሰሙ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ የስር ፍ/ቤት ውድቅ ያደረገበትን አግባብ ግራ ቀኙ ሚያዝያ 11 ቀን 2011 ዓ.ም ካደረጉት የገንዘብ ብድር ውል አንቀፅ 2 እና ከፍ/ሕ/ቁጥር 1784ና 1785 ጋር በማገናዘብ ለመመርምር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪ መጋቢት 15 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው የብድር ውል ስምምነት አንቀፅ 2.1. በተገለፀው የአከፋፈል ሁኔታ ክፍያው በ8 ጊዜ እንዲጠናቀቅ ከተደረገው ስምምነት በተቃራኒ ተጠሪ በ7 ጊዜ ተከፍሎ እንዲጠናቀቅ አለማድረጌን በስር ፍ/ቤት በግልፅ ክርክር አቅርቤአለሁ፡፡ አመልካችም ክፍያው ከ8 ዙር ወደ 7 ዙር ስለመቀየሩ ምንም አይነት ማስረጃ ያላቀረበ ሲሆን የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በሰነድ ማስረጃ የሚረጋገጥ በመሆኑ የሰው ምስክር ሳይሰማ ክሱ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች ሰኔ 9 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሱን ያቀረበ ሲሆን የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም በግራ ቀኙ መካከል ሚያዝያ 11 ቀን 2011 ዓ.ም የተደረገው የብድር ውል ሊፈርስ አይገባም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት በስር ፍ/ቤት ከተደረጉ ክርክሮችና ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነው በግራ ቀኙ መካከል ሚያዝያ 11 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል ስምምነት አመልካች ብር 2,631,246.08 መበደሩን፣ አከፋፈሉም ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በየሶስት ወሩ ሁኖ ወለድና የተለያዩ ወጪዎችን ጨምሮ ብር 349,124.00 መሆኑንና በ8 ጊዜ ክፍያ በ2 ዓመት ውስጥ እስከ ሚያዝያ 11 ቀን 2013 ዓ.ም ተከፍሎ የሚጠናቀቅ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ አመልካች ከዚህ ስምምነት በተቃራኒ በአፈጻም ሒደት ተጠሪው ክፍያው በ7 ጊዜ እንዲፈፅም አድርጓል፤ ይህንንም ክዶ አልተከራከረም በሚል ያቀረበውን ቅሬታ ስንመለከት አመልካች ድርጊቱን አለመፈፀሙን በግልጽ ክዶ ስለመከራከሩ በስር ፍ/ቤት ፍርድ ላይ ሰፍሯል፡፡ ተጠሪ ይህንን ፍሬ ነገር ማለትም የክፍያው ጊዜ ወደ ሰባት ዙር መቀየሩን ክዶ እስከተከራከረ ድረስ አመልካች ክፍያው ከ8 ዙር ወደ 7 ዙር መቀየሩን የሚያሳይ ማስረጃ በማቅረብ በፍ/ህ/ቁጥር 2001/1 እና በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 223 ክርክሩን በማስረጃ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ተጠሪ ክዶ አልተከራከረም ከሚል በስተቀር ይህንን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ማስረጃ ስለማቅረቡ ወይም አቅርቦ አላግባብ ውድቅ የተደረገበት ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የክፍያ ጊዜ ለውጥ አለማድረጉን ክዶ የተከራከረ እና በአመልካች በኩል የክፍያ ጊዜ ለውጥ በተጠሪ ለመደረጉ የቀረበ ማስረጃ በሌለበት ተጠሪ በአመልካች ለውል ማፍረሻ ተደርጎ የቀረበውን የክፍያ ጊዜ ለውጥ አድርጓል ለማለት አይቻልም፡፡

ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት አመልካች ከውል ስምምነቱ ውጪ ተጠሪ ክፍያው በ7 ጊዜ ተከፍሎ እንዲጠናቀቅ ቢጠይቅ እንኳ ውሉን ለማፍረስ በቂ ምክንያት ይሆናል? ወይስ አይሆንም? የሚለው ይሆናል፡፡ ከተዋዋዮቹ አንዱ እንደ ውሉ ያልፈፀመ እንደሆነ ሌላኛው ተዋዋይ እንደ ውሉ እንዲፈፀምለት ወይም ውሉ እንዲሰረዝ እና ለደረሰበት ጉዳት ካሳ መጠየቅ የሚችል መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1771 ላይ ተገልጿል፡፡ ውል እንዲረዝ ሲጠየቅ ዳኞች ጥያቄውን ተቀብለው ውሉ እንዲሰረዝ የሚወስኑት በውል

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መዝገብ ቁጥር201100

ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ/ም

**ዳኞች** ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

**አመልካቾች**፡- 1ኛ. አቶ ዳንኤል ታደሰ

2ኛ. ወ/ሪት ኤልሳ ታደሰ — የቀረበ የለም

3ኛ. ወ/ሪት ለምለም ታደሰ

4ኛ. ወ/ሪት ዘይድ ኡፔላ

5ኛ. ወ/ሪት ዘውዲቱ ታደሰ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ ዘውዲ መንግስተአብ- ቀርበዋል

ለምርምራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍርድ**

አመልካቾች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 259177 ጥር 7 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት ያቀረቡትን ይግባኝ መሰረዙ እንዲሁም ሟች አቶ ታደሰ ወልደጊዮርጊስ ታህሳስ 20 ቀን 2005 ዓ/ም አደረጉት የተባለው ኑዛዜ እንዲሰረዝ ያቀረቡትን መቃወሚያ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመዝገብ ቁጥር 266705 መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል በማለት በሰበር ለማሳረም ጥር 12 ቀን 2013 ዓ/ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ያስቀርባል በመባሉ መዝገቡ ለችሎት ቀርቧል።

ጉዳዩ የሚች አቶ ታደሰ ወልደጊርጊስ ውርስ እንዲጣራ አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ የውረስ አጣሪ ተሹሞ ተጠሪ ሚች ታህሳስ 20 ቀን 2005 ዓ/ም ኑዛዜ አትርፈዋል በማለት ለውርስ አጣሪ ያቀረቡት ኑዛዜ ላይ የቀረበ መቃወሚያን የሚመለከት ሆኖ የክሱ ይዘትም፡- ሚች ለረጅም ጊዜ በእርጅና እንዲሁም የመርሳት የአእምሮ በሽታ ፣ ኮልስትሮል ፣ ስኳር ደምግፍት እና የሌሎች በሽታዎች መድኀንት ይወስዱ የነበረና ኑዛዜ አድርገዋል በተባለ ጊዜ የአእምሮ ሁኔታቸው ምርመራ እንዳይደረግ ተጠሪ ፓስፖርት በመከልከል የአእምሮ ጤንነት ሁኔታቸውን ለማድበስበስ የሞከሩ ሲሆን ኑዛዜውም በተናዛዡ እና አራት ምስክሮች ፊት መነበቡ በኑዛዜው ላይ ስላልተገፀ እና ኑዛዜውም ለተጠሪ ልጆች የሚያደላ አመልካቾችንም ከ1/4ኛ በላይ የሚጎዳ በመሆኑ ሊፈርስ ይገባዋል በማለት አመልክተዋል። ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ፍርድ ቤቱ በብይን ያለፈው ሲሆን በፍሬ ነገር መልሳቸውም ሚች ኑዛዜውን ባደረጉበት ወቅት የአእምሮ ህመም የነበራቸው ለመሆኑ የህክምና ማስረጃ አለመቅረቡ እና የተባሉት ህመሞች ሚች ኑዛዜ እንዳያደርጉ የማያግዱ በመሆኑና ሚች ኑዛዜውን በኮምፒዩተር አፅፈው በማምጣት ለምስክሮቹ አንብበው አይተው መፈረማቸው በኑዛዜው ላይ የሰፈረ በመሆኑ አጠራጣሪ ካለመሆኑም በላይ ኑዛዜው ከተጠሪ ለተወለዱት ልጆች የሚያደላ አይደለም እንጂ የሚያደላ እንኳን ቢሆን ከልካይ የሕግ ድንጋጌ ባለመኖሩ እና ሚች ተጠሪ ግማሽ ባለድርሻ የሆኑበትን ንብረት ያለተጠሪ ፈቃድ በኑዛዜ ለአመልካቾች ያስተላለፉ በመሆኑ ተጠሪ በኑዛዜው ተጎጂ እንጂ ተጠቃሚ አለመሆናቸውን በመግለፅ የአንድ ወራሽ ድርሻ ከ1/4ኛ በታች መሆንም የክፍፍል ደንብ እንጂ የኑዛዜ ማፍረሻ ምክንያት ባለመሆኑ ክሱ እንዲሰረዝ ጠይቀዋል።

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ኑዛዜ በሚች የተደረገ መሆን አለመሆኑ ፣ ሚች ኑዛዜውን አድርገዋል በተባለ ጊዜ የአእምሮ ሁኔታቸው እንዴት እንደነበረ እንድጣራ እንዲሁም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ኑዛዜ በሚች የተፈረመ መሆን አለመሆኑ እንዲጣራ እንዲሁም በኑዛዜው ላይ የተዘረዘሩት ምስክሮች ቀርበው የመስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ትዕዛዝ ሰጥቶ የአማኑል የአእምሮ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሚች ስም በኮምፒተራቸው ውስጥ የሌለ በመሆኑ ካርድ ካለ ከመዝገብ የሚፈልግ መሆኑን የገለፀ ሲሆን የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የፎረንስክ ምርመራ ዳይሬክቶሬትም ለምርምራው የሚረዱ ሚች የፈረሙባቸው የፊርማ ናሙናዎች እና ተመርማሪው ሰነድ እንዲቀርብለት ጠይቆ የአመልካቾች ጠበቃ የተጠቀሱ ሰነዶችን ለማቅረብ ደንበኞቻቸው በቅርበት እንደሌሉ በመግለፅ ለማቅረብ ጊዜ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ተደጋጋሚ ቀጠሮ ብሰጣቸውም ስላላቀረቡ መታለፉን እንዲሁም በኑዛዜው ላይ ስማቸው የተጠቀሱት ምስክሮችን አድራሻ አመልካቾች ስለማያውቁ በተጠሪ በኩል እዲቀርብላቸው ጠይቀው መታለፉን ግልፆ ፤ በኑዛዜው ላይ ምስክር ያልነበሩ የ1ኛ ፣ 5ኛ አመልካቾችን እና የሌላ ሶስተኛ ምስክር ቃል ሰምቶ መዝገቡ እንደመረመረው፡- በአእምሮ ጉድለት ምክንያት ኑዛዜን ለመሻር ሚቹ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር

863 መሰረት ተናዛዡ የታወቀ እብድ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን በአመልካቾች የቀረቡት የሕክምና ሰነዶች የሚያስረዱት ሟቹ ከልብ ህመም ጋር የተያያዘ የጤና ችግር የነበረባቸው መሆኑን እንጂ ሟች የአእምሮ መጉደል ወይም የታወቀ እብድ መሆቻውን የማያሳይ ከመሆኑም በላይ 1ኛ እና 5ኛ አመልካቾች ሟቹ በደም ግፍት ምክንያት ጤንነታቸው ተናግቶ የማስታውስ ችግር ገጥሟቸው እንደነበረ ያሳረዱ ቢሆንም ኑዛዜው ሲደረግ ስላልነበሩ ሟቹ ኑዛዜውን ስያደርጉ የጤንነት ሁኔታቸው ፈቃዳቸውን ለመስጠት የማያስችላቸው እንደነበረ ስላላስረዱ እና ኑዛዜው በተናዛዡ እና በአራት ምስክሮች ፊት ተነቦ መፈረሙን የሚገልፅ በመሆኑና ተጠሪ በማስረጃነት ካቀረቡት ከሰንሻይን ኮንስትራክሽን ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ/ም ከተፃፍ ሰነድ መረዳት እንደሚቻለው ሟች ከኑዛዜው አስቀድሞ ሌሎች ንብረቶችን ለአመልካቾች በስጦታ ያስተላለፉ መሆኑ ሲታይ ሟች ንብረቶቻቸውን ለተወላጆች ከፍፍል ደረጉ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በተደረገው ከፍፍልም አመልካቾች ከሩብ የበለጠ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ስለማያሳይ ኑዛዜው ለተጠሪ እና ለጆቻቸው ማድላቱን የማያመለክት በመሆኑ ታህሳስ 20 ቀን 2005 ዓ/ም የተደረገው ኑዛዜ ሊፈርስ አይገባም በማለት ወስኗል።

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመቃወም ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ በመሰረዙ አመልካቾች ቀጣዩን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል። ታህሳስ 20 ቀን 2005 ዓ/ም ተደረገ የተባለው ኑዛዜ ተጠሪ እንድያቀርቡ ማድረግ ሲገባው ይህንን አለማድረጉ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ከመሆኑም በላይ ፍትህን የሚጎዳ ሆኖእያለ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ወሳኝ የሆነውን ኑዛዜ እና በኑዛዜው ላይ የተቆጠሩ ምስክሮች ቀርበው ባለመሰማታቸው በኑዛዜው ላይ ያለው ፍርማ የሟች መሆኑ ፣ ኑዛዜው በሟች መደረጉ ፣ ኑዛዜው ሲደረግ ነበሩ የተባሉ ሰዎች በእርግጥም መኖራቸው ፣ ኑዛዜው ምስክሮች በተገኙበት የተነበበ መሆኑ ለውሳኔ አሰጣጥ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ፍሬ ነገሮች ሳይጣሩ እና ሟች የአእምሮ ህመም እንዳለባቸው ለማስረዳት የቀረበው በርካታ የሕክምና ማሰረጃ እና ተጠሪዋ ሟቹን አማኑኤል ሆስፒታል እንዳሳከሟቸው የተናገሩ ለመሆኑ የተነገረው የምስክርነት ቃል ተመርምሮ ተደርጓል የተባለው ኑዛዜ መደረጉ ፤ ተደርጓል ከተባለም በነፃ ፈቃድ እና በትክክለኛ አእምሮ መደረጉ ሳይጣራ ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ መሆኑ እንዲሁም ሟቹ በኑዛዜ ያስተላለፉት ጠቅላላ ንብረት ግምት ተጣርቶ የአመልካቾችን የውርስ ደርሻ ከሩብ የበለጠ መጉዳት አለመጉዳቱ ሳይረጋገጥ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት በሰበር ችሎቱ እንዲታረም ጠይቀዋል።

የአመልካቾችን የሰበር ቅሬታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ኑዛዜ በሟች የተፈረም ባለመሆኑ እንድመረመርላቸው ፣ በኑዛዜው ላይ የተመለከቱት ምስክሮች እንዲሰሙላቸው እንዲሁም ኑዛዜው ከ1/4ኛ በታች የውርስ ድርሻቸውን የሚጎዳ ነው በሚል አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር በአግባቡ ሳይጣራ የተወሰነበትን አግባብ ከመሰረታዊ የክርክር አመራር እና ማስረጃ ምዘና መርህ ጋር አገናዝቦ ለመመርምር መዝገቡ ያስቀርባ በማለቱ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- ሟች የአእምሮ በሽታ የነበረባቸው ለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ማስረጃ አለመቅረቡ ፣ አማኑኤል ሆስፒታልም ሟች ከሆስፒታሉ የህክምና ፋይል የሌላቸው መሆኑንና ስታከሙ እንዳልነበረ በፅሁፍ ገልፆ ፣ ሟችም በሆስፒታሉ ስታከሙ

እንዳልነበረ በአመልካቾች ምስክር ባለመመስከሩ በአጠቃላይ ሚች ኑዛዜውን ባደረጉበት ወቅት የጤና ጉድለት የነበረባቸው መሆኑ በማስረጃ ባለመረጋገጡ እና የፎረንስክ ምርመራ ውጤት እንድቀርብ በተደጋጋሚ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቢሰጥም አመልካቾች ለማቅረብ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ማስረጃ የማቅረብ መብታቸው እንዲሁም አመልካቾች ለምስክርነት የቆጠሩትን በኑዛዜው ላይ ያሉ ሰዎችን ለአራት የፍርድ ቤት ቀጠሮዎች ለማቅረብ ፈቃደኛ ስላልሆኑና ምስክሮቻቸውን የማቅረብ ግዴታቸውን ስላልተወጡ የታሰፈ ሆኖእያለ ተጠሪ ምስክሮቹ እንዳይቀርቡ እንዳገዷቸው ቅሬታ መቅረቡ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ኑዛዜውን ከነበረበት የሚች ብቻ ንሰሓ አባት ከሆኑት አባ ዘርአብሩክ እጅ የአመልካቾች ጠበቃ ጠይቀው ኮፒውን ወስዶ እንድሰረዝ ክስ ያቀረቡ ሲሆን ዋናውም ለውርስ አጣሪዋ ተሰጥቶ እያለ ተጠሪ ለማቅረብ ፈቃደኛ እንዳልሆኑ እና ኑዛዜው በሕጉ አግባብ በምስክሮች ፊት ተነቦ አለመፈረሙ በምሰክር ሳይረጋገጥ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን ታህሳስ 20 ቀን 2005 ዓ/ም ሚች ያደረጉት ኑዛዜ በአራቱም ምስክሮች ፊት ተነቦ የተፈረመ በሚች ነፃ ፈቃድ የተሰጠ ሆኖ አመልካቾች የህጉን ፍርማሊት ያላሟላ መሆኑን ስላላስረዱ ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ መሆኑ ተገቢ ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ሚች ታህሳስ 20 ቀን 2005 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜም ከሩብ በላይ ጉዳት መድረሱን የማሳይ ሲሆን ኑዛዜውም ሲታይ ተናዛዡ የውርስ ሃብቱን ለተወላጆቹ መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ ማድረግ ሲሆን ፣ የሰበር ሰሚ ችሎቱም በሰበር መዝገብ ቁጥር 50901 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሚች በኑዛዜ የንብረት ድልድል ማድረግ እንደሚችል እና በንብረት ድልድል አፈፃፀሙ ተወላጅ የሆነ ወራሽ መብቱ ከሩብ የበለጠ ጉዳት የደረሰበት ከሆነ ከውርስ ማጣራ በኋላ ጉዳቱ በገንዘብ ወይንም በዓይነት የማስተካከል የክፍፍል ደንብ እንጅ የኑዛዜ ማፍረሻ ምክንያት ባለመሆኑ ኑዛዜውን በተናዛዡ ሃሳብ እና ፈቃድ መሰረት ማስፈፀም እንደሚገባ የወሰነ ሲሆን ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ/ም በተፃፈ ሰነድ ሳንሻይን አፓርትመንት ላይ የሚገኝ መኖሪያ ቤት ለ1ኛ ፣ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ፤ ለ1ኛ አመልካችም በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍል ከተማ የሚገኝ ባለአንድ ወለል መኖሪያ ቤት ሰጥተው እና ከፍተኛ ወጪ በማውጣት በእንግሊዝ ሀገር ያስተማሩ ሲሆን 4ኛ እና 5ኛ አመልካቾችንም ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ሠርግ በመደገስ ድረው እያለ ኑዛዜው ከተጠሪ ለተወለዱ ልጆች አድልዕል በማለት የሚቀርበው አቤቱታ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ የአመልካቾች አቤቱታ የሕግ መሰረት የሌለው እና በማስረጃ ያልተደገፈ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና ግራቀኙ በዚህ ችሎት ያደረጉት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን ለሰበር ቅሬታው መነሻ የሆነው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑ መዝገቡ ያስቀርባል ሲባል የተያዘው ጭብጥ አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ አንፃር ችሎቱ እንደሚከተለው መርምሯታል፡፡ ተጠሪ ሚች ታህሳስ 20 ቀን 2005 ዓ/ም ኑዛዜ አትርፈዋል በማለት ለውርስ አጣሪዋ ያቀረቡትን ሰነድ አመልካቾች ሚች ለረጅም ጊዜ በእርጅና እንዲሁም የመርሳት የአእምሮ በሽታ ፣ ኮልስትሮል ፣ ስኳር ደምግፍት እና የሌሎች በሽታዎች መድኀንት ይወስዱ የነበረ በመሆኑ ፤ ኑዛዜ ለማድረግ ችሎታ የላቸውም በማለት ያቀረቡትን መቃወሚ ፣ ተጠሪ ሚች ኑዛዜውን ባደረጉበት ወቅት የአእምሮ ህመም የነበራቸው ለመሆኑ የህክምና ማስረጃ አለመቅረቡ እና የተባሉት ህመሞች ሚች ኑዛዜ እንዳያደርጉ የሚያግዱ አይደሉም በማለት

ተቃውመዋል። እንደማንኛውም የፀና ሕጋዊ ተግባር ኑዛዜ ማድረግም ችሎታን ይጠይቃል። በሕግ በሌላ አግባብ ካልተወሰነ በቀር ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ሕጋዊ ተግባር ለመፈፀም ችሎታ ያለው መሆኑን የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 192 ይደነግጋል። ግልጽ የታወቀ የአእምሮ ጉድለት ያለበት ሰው በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 341 እና 342 ሥር የተገለፁ ሁኔታዎችን የሚያሟላ ከሆነ መሆኑን ያስረዳል። ተናዛዡ ኑዛዜውን በሚያደርግበት ጊዜ የታወቀ እብድ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር የአእምሮ ጉድለት ነበረበት በማለት ብቻ ኑዛዜ ሊሻር የማይችል መሆኑን የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 863 ያስረዳል። አመልካቾች ተናዛዡ የመርሳት የአእምሮ በሽታ ፣ ኮልስትሮል ፣ ስኳር ደምግፍት እና የሌሎች በሽታዎች የነበሩባቸው መሆኑን ቢክራከሩም የተጠቃሾቹ በሽታዎች ተጠቂ ለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ የተባሉት በሽታዎች ተጠቂ እንደነበሩ ብረጋገጥ እንኳን በእነዚህ በሽታዎች መጠቃት የታወቀ እብድ የሚያሰኝ ባለመሆኑ ፤ የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡት የሕክምና ሰነዶች ሟች ከልብ ህመም ጋር የተያያዘ የጤና ችግር የነበረባቸው መሆኑን እንጂ የአእምሮ መጉደል ወይም የታወቀ እብድ መሆቻውን አያሳይም በማለት ከዚህ አንፃር አመልካቾች ያቀረቡትን መቃወሚያ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ በሕጉ አግባብ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም።

በኑዛዜ የሚከናወኑት ተግባሮች ስጦታ(legacy) ወንም የክፍያ ደንብ (Rule of partition) ሊሆኑ ይችላሉ። በመርህ ደረጃ አንድ ሰው ከውርስ ሀብቱ መካከል አንድን ንብረት ለወራሾቹ መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ የማያሰኘው ሲሆን ፣ ይልቁንም ይህ ዓይነቱን ኑዛዜ ሕጉ የሚቀበለው እንደ አንድ የክፍያ ደንብ በመሆኑ አንድ አውራሻ ለወራሹ አንድን ንብረት ቢናዘዝለት የኑዛዜ አፈፃፀም ስጦታ(legacy) አፈፃፀምን መከተል ሳይሆን የክፍያ ደንብ (Rule of partition) በመከተል የሚከናወን ይሆናል። ሆኖም በኑዛዜው ላይ የሚሰጠው የክፍያ መጠን በመገለፁ ብቻ ሁል ጊዜ የክፍያ ደንብ ሊባል የሚችል ሊሆን አይችልም። በመሆኑም የተሰጠው የንብረት መጠን ከሟቹ የውርስ ንብረት ጋር ታይቶ ውጤቱም በዚሁ ረገድ መታየት አለበት። በተያዘው ጉዳይ ኑዛዜው ከተጠሪ ለሚወለዱት ልጆች ሚያዳላ እና ከ1/4ኛ በላይ የሚጎዳቸው መሆኑን በመግለፅ ሊፈርስ ይገባዋል በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር ኑዛዜው ለተጠሪ ለተወለዱት ልጆች የሚያደላ አይደለም እንጂ የሚያደላ እንኳን ቢሆን ከልካይ ሕግ ባለመኖሩ እና ሟች ተጠሪ ግማሽ ባለድርሻ የሆኑበትን ንብረት ያለተጠሪ ፈቃድ በኑዛዜ ለአመልካቾች ያስተላለፉ በመሆኑ ተጠሪ በኑዛዜው ተጎጂ እንጂ ተጠቃሚ አለመሆናቸውን ፤ እንዲሁም የአንድ ወራሽ ድርሻ ከ1/4ኛ በታች መሆንም የክፍፍል ደንብ እንጂ የኑዛዜ ማፍረሻ ምክንያት ባለመሆኑ ኑዛዜው ሊሰረዝ አይገባም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ፤ ተጠሪ ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ኑዛዜ ከመደረጉ በፊት ለ1ኛ ፣ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ/ም ስጦታ ተደርጎላቸዋል በማትለት ያቀረቡት ክርክር በአመልካቾች ካለመስተባበሉም በላይ ፤ ሟች ለአመልካቾች በስጦታ ያስተላለፉት ንብረት መኖሩን ከሰንሻይን ኮንስትራክሽን ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ/ም የተፃፈ ሰነድ በተጠሪ በማስረጃነት መቅረቡን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል። ኑዛዜ ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ ላይ ከሩብ የበለጠ ጉዳት ማድረሱ ለኑዛዜው መፍረስ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የሰበር ሰሚ ችሎቱ ለፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1123 በሰበር መዝገብ ቁጥር 55648

የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለተያዘው ጉዳይም ተፈፃሚነት ያለው በመሆኑ ፤ ተጠሪ ኑዛዜው ከ1/4ኛ በላይ ጉዳት ማድረሱ ቢረጋገጥም ጉዳዩ የክፍያ ደንብ በመሆኑ ከልካይ ሕግ የለም በማለት ያቀረቡት ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ማግኘቱ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ኑዛዜው በአመልካቾች ላይ ከ1/4ኛ በላይ ጉዳት ማድረስ አለማድረሱ አስቀድሞ ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ/ም ለአመልካቾች የተላለፈው ንብረት እና ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ኑዛዜ ለግራቀኙ የደረሰው ንብረት ግምት መታወቅ አለበት፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ/ም ለአመልካቾች የተላለፈው ንብረት እና የንብረቱ ግምት እንዲሁም ለቅሬታው ምክንያት በሆነው ኑዛዜ ለአመልካቾች የደረሰው ንብረት ግምቱ ተለይቶ ሳይታወቅ ሚች ለተወላጆች ያደረጉት የንብረት ክፍፍል ከሩብ የበለጠ በአመልካቾች ላይ ጉዳት ማድረሱን አያሳይም ማለቱ ግልጽ የህግ ድንጋጌን የሚቃረን ነው፡፡

አመልካቾች ሚች ኑዛዜ አላተረፉም ፣ በሰነዱ ላይ ያለው ፊርማም የሚች አይደለም ፣ ኑዛዜውም አራት ምሰክሮች ባሉበት አልተነበበም በማለት ያቀረቡትን ክርክር ማስረዳት አልቻሉም በማለት የመታለፉ አግባብነት ሲታይ፡- የኑዛዜ መኖርን ማስረዳት ሸክም ያለበት የኑዛዜው ተጠቃሚ ነኝ የሚል ሰው መሆኑንና ማስረዳት የሚቻለውም የኑዛዜ ሰነዱ በማቅረብ መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 49831 እና 53279 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ ሲሆን የፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥር 896 እና 897 ድንጋጌም ይህንኑ የሚያስረዳ ነው፡፡ አመልካቾች የሚች ወላጅ አባታቸው አቶ ታደሰ ወልደጊርጊስ ውርስ እንዲጣራ ያቀረቡትን አቤቱታ ተጠሪ ሚች ታህሳስ 20 ቀን 2005 ዓ/ም ኑዛዜ አትርፈዋል በማለት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ሰነድ የሚች ውርስ እንዲጣራ አመልካቾች አቤቱታ ባቀረቡበት መዝገብ ላይ ያቀረቡ ሲሆን ፤ አመልካቾች ታህሳስ 20 ቀን 2005 ዓ/ም ተደርጓል በማለት ተጠሪ ያቀረቡትን የኑዛዜ ወራሽነት ሰነድ ላይ ያላቸውን መቃወሚያ በመዘርዘር ኑዛዜው ሊፈርስ ይገባም በማለት የመቃወሚያ አቤቱታ ለሰበር ቅሬታው መነሻ በሆነው መዝገብ ላይ አቅርበው ፤ ተጠሪም ኑዛዜው ሊፈርስ አይገባም የሚሉበትን ዝርዝር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም አከራካሪው ኑዛዜ በሚች የተደረገ መሆኑን አለመሆኑን ለማጣራት የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የፎረንሲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት ሚች አድርገዋል የተባለውን ኑዛዜ የሚች መሆን አለመሆኑን አጣርቶ እንዲያቀርብ እና በኑዛዜው ላይ የተዘረዘሩ እማኞችም ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ትእዛዝ ሰጥቶ ፤ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የፎረንሲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት የሚች ፊርማ ናሙና እና ተመርማሪው ሰነድ እድቀርብለት ጠይቆ በአመልካች ባለመቅረቡ እንዲሁም በኑዛዜው ላይ ስማቸው የተጠቀሱ እማኞች አመልካቾች አድራሻቸውን የማያውቁ በመሆኑ በተጠሪ በኩል እንድቀርቡላቸው ጠይቀዋል በማለት አልፎታል፡፡ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2007(2) ወራሾች የአውራሻቸው ጽሑፍ ፊርማ አለመሆኑን ብቻ መካድ በቂ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ጽሑፉ ወይንም ፊርማው በተካደ ጊዜ እንዲመረመር ዳኞች ሊያዙ እንደሚችሉ ከፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2008 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ጽሕፈቱንና ፍርማውን ለማስመርመር ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም ተመርማሪው ሰነድ በማን እጅ እንዳለ ሳይለይ እና የፊርማ ናሙናዎቹም የሚገኙበትን ቦታ ተለይቶ እንድቀርብ ግልፅ ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው ፤ አመልካቾች መኖሩን በውርስ ማጣራት ሂደት የሰሙትን ሰነድ ለምርመራ አላቀረቡ በማለት ፤ እንዲሁም

በኑዛዜው ላይ ያለው ፍርማ ስለተካደ ፊርማው የሟች መሆን አለመሆኑ ኑዛዜው ሲደረግ በነበሩ ምስክሮች ማረጋገጥ ሲገባው ፤ አመልካቾች በኑዛዜው ላይ ስማቸው የተጠቀሱ እማኞችን አድራሻ አናውቅም በማለታቸው ብቻ የእማኞቹን አድራሻ ማወቅ አለማወቃቸው ሳይጣራ በአመልካቾች ጉድለት ትዕዛዙ እዳልተፈፀመ ተወስዶ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 199(1) ታልፎ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ኑዛዜ በሟች የተደረገ መሆን አለመሆኑ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 255 ,257 እና 273 በማስረጃ ሳይጣራ ፤ እንዲሁም ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ ፍትሓዊነት ተገቢ ነው ብለው ሲያምኑ ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ አስቀርቦ መመርመር እንዳለባቸው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 29861 ላይ የሰጠው በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት ያለውን አስገዳጅ ውሳኔ በመተላለፍ ፤ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖአያለ በይግባኝ ሰሚው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አለመታረሙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 259177 ጥር 7 ቀን ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 266705 መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት **ተሽሯል**፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 266705 በማንቀሳቀስ በፍርድ ሀተታው ውስጥ በተገለፀው መሰረት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ኑዛዜ በሟች መደረግ አለመደረጉ ፣ ተደርጓል ከተባለ የፎርማሊት ችግር ያለበት መሆን አለመሆኑ ፣ በሕግ ፊት የፀና ኑዛዜ አለ ከተባለ በአመልካቾች ላይ ከሩብ በላይ ጉዳት ማድረስ አለማደረሱ ፤ ጉዳት አደርሶ ከሆነ ውጤቱ ምን መሆን እንዳለበት አጣርቶ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ላይ ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ውጪ እና ኪሳራ ግራቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

.

ማ/አ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

**የሰ/መ/ቁ.** 201128

ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች-** ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ- ጠበቃ ሰለሞን ረዳ

**ተጠሪ-** ወ/ሮ ቢቂልቱ በየነ- ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ የፍርድ ባለመብት በመሆን የፍርድ ባለዕዳ በሆኑት በአመልካች እና ሌሎች ሁለት ግለሰቦች ላይ ባቀረቡት አቤቱታ የቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 64593 ላይ በቀን 10/08/2009 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ውሳኔ መሠረት እንዲፈፀምላቸው የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

የአፈፃፀም አቤቱታዉ የቀረበለት ፍርድ ቤት አከራካሪው ይዞታ በገፈርሳ ቡራዩ ቀበሌ አስተዳደር አማካኝነት ተለክቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ ስፋቱ 842.8 ካ.ሜ እንደሆነ፤ ተጠሪ ደግሞ በክሳቸው ላይ የጠቀሱት የይዞታ መጠን 660 ካ.ሜ ስለመሆኑ መገንዘቡን ጠቅሶ የፍርድ ባለእዳዎች በዚሁ መጠን ለአመልካች እንዲያስረክቡ፣ ከዚህ ውጪ የሚተርፍ ይዞታ ካለና ባለመብት ካልተገኘ የከተማው አስተዳደር ወደ መሬት ባንክ እንዲያስገባ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ግራ ቀኙ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን የይግባኝ አቤቱታ በማጣመር ከመረመረ በኋላ ትርፍ ነው የተባለውን መሬት የቡራዩ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት ይዉሰድ መባሉ ስህተት ነው፤

ተጠሪ በአራቱም አቅጣጫ አዋሳኝ ጠቅሰው ያቀረቡትን ክስ መጠኑ በባለሞያ እንዲጣራ ከማዘዝ ውጪ ትክክለኛውን መጠን አልጠቀሱም ሊባል አይገባም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል። አመልካች በበኩላቸው በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች በቅደም ተከተል ቢያቀርቡም ተቀባይት አላገኘም። ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች በቀን 12/05/2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል። የአቤቱታቸው ይዘትም በአጭሩ ክርክር ያስነሳውና ተጠሪ እንዲረከቡት የተወሰነላቸው ይዞታ መጠን 660 ካ.ሜ ሆኖ እያለ ከዚህ መጠን በላይ አመልካች በውርስ ያገኘሁትን ይዞታ በማጠቃለል በአፈፃፀም እንዲረከቡ መወሰኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው።

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የአከራካሪው ይዞታ አፈፃፀም ፍርዱን የተከተለ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ከፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት ህግ አንፃር መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል። በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ በቀን 22/06/2013 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው የቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍርድ ለአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነውን ውሳኔ ሲሰጥ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ስፋት ያላጣራ ሲሆን በደፈናው የተጠሪ ይዞታ ላይ የተፈጠረው ሁከት ተወግዶ የፍርድ ባለእዳዎች የሰሩትን አጥር አፍርሰው ይዞታውን እንዲለቁ ወሰነ እንጂ የይዞታውን መጠን አልገለፀም፤ በስር ፍርድ ቤት ክስ ያቀረብኩበት ይዞታ መጠኑ 1300 ካ.ሜ የነበረ ሲሆን መንግስት በይዞታው ላይ መንገድ በማውጣቱ መጠኑ ቀንሷል፤ አመልካች በዚህ አካባቢ ምንም አይነት መሬት የላቸውም፤ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዋሳኙ የተጠቀሰውን መሬት በአፈፃፀም እንድረከብ ትዕዛዝ መስጠቱ ስህተት ስለሌለው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክራለች። አመልችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተው ተከራክረዋል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ከተያዘው ጭብጥ፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረዉም ለአፈፃፀሙ ምክንያት ለሆነዉ ዉሳኔ መነሻ የሆነዉን ክስ ተጠሪ ሲያቀርቡ አዋሳኞቹንም በአራት አቅጣጫ በመጥቀስ ሲሆን ለአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ ይዘትም አዋሳኙ ከተጠቀሰዉ ይዞታ ዉስጥ የሚገኘዉ ይዞታ የተጠሪ በመሆኑ አመልካችን ጨምሮ ሌሎች ተከሳሾች ሁከት አስወግዶ በቦታዉ ላይ ያጠሩትን አጥር ያፍርሱ የሚል ስለመሆኑ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሰጠዉ የፍርድ ሃተታ መገንዘብ ይቻላል። አመልካች ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ወይም ለአፈፃፀሙ መነሻ

የሆነዉ ፍርድ ካረፈበት ይዞታ አጠገብ አዋሳኝ ይዞታ ያላቸዉ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ ለፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔም ይሄዉ ነዉ፡፡

ፍርድ እንዲያስፈጽም አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት እንደ ፍርዱ፣ ማለትም በፍርዱ ላይ በተመለከተዉ ላይ ሳይጨምር ወይም ሳይቀንስ፣ የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት፡፡ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ዳኝነት ያላግባብ የተወሰደ ንብረት ወይም ሀብት እንዲመለስ ወይም ገንዘብ እንዲከፈል ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ በሚሰጥ ዉሳኔ የፍርድ ባለመብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለዉ በተሰጠ ፍርድ መሠረት የተፈጸመለት እንደሆነ ነዉ፡፡ እያንዳንዱ ጉዳይ የሚፈጀዉ ጊዜ እንደ የጉዳዩ ዓይነትና ባህርይ ሊለያይ የሚችል ቢሆንም፣ ክስ ከቀረበበት ጀምሮ እስከ ዉሳኔ ድረስ ያለዉ ሂደት የተወሰነ ጊዜ መዉሰዱ አይቀሬ ነዉ፡፡ በዚህም ሂደት የፍርድ ቤት ብሎም የተከራካሪ ወገኖች ጊዜ ይባክናል፤ ወጪና ድካም ይኖራል፡፡ ስለሆነም ፍርድን እንደ ፍርዱ ማስፈጸም ይህን ሂደት በማለፍ የተሰጠ ፍርድ ፍሬ አልባ እንዳይሆን የማድረግ ዉጤት ሊያስከትል የሚችል ከመሆኑም በላይ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ፍርድ ተፈፃሚነቱ ተገማች እንዲሆን ያስችላል፡፡ የፍት/ብ/ሥነ ሥርዓት ህጋችን ሰባተኛ መጽሐፍ ከአንቀጽ 371 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎቹ የፍርድ አፈፃፀም የሚመራበትን ሥነ-ሥርዓት ይደነግጋል፡፡ የፍርድ አፈፃፀም የቀረበለት ፍርድ ቤትም በዚህ የመጽሐፉ ክፍል የተዘረጋዉን ስርዓት በመከተል ድንጋጌዎቹን እንደየአግባብነታቸዉ ተግባራዊ በማድረግ አፈፃፀሙን በመምራት እንደ ፍርዱ የማስፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ለአፈፃፀሙ መነሻ ለሆነዉ ዉሳኔ ምክንያት በሆነዉ ክስ ተጠሪ የጠቀሱት የይዞታ መጠን 660 ካ/ሜትር የሚል ቢሆንም የተሰጠዉ ዉሳኔ በክሱ ላይ አዋሳኞቹ የተጠቀሰዉ ይዞታ የተጠሪ መሆኑን የሚያሳይ ከሆነ በአዋሳኙ የተመለከተዉ የይዞታ መጠን ከ660 ካ/ሜትር በላይ 842.8 ካ/ሜትር መሆኑ ቀሪዉ ይዞታ ማለትም 182 ካ/ሜትር ፍርድ ያላላረፈበት ነዉ ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የወረዳዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ማየት ሲገባዉ ይዞታዉ ተለክቶ በታወቀዉ መጠን እና በተጠሪ ክስ ላይ በተጠቀሰዉ መጠን መካከል ልዩነት በመፈጠሩ ብቻ 182 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ፍርድ አላረፈም በማለት መቀነሱ የፍርዱን ትክክለኛ ይዘት ያላገናዘበ ሲሆን፣ በአንፃሩ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ በማረም በፍርዱ ላይ አዋሳኙ የተጠቀሰዉ ይዞታ ለተጠሪ እንዲፈጸም በማለት ዉሳኔ መስጠቱ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ይህንኑ ዉሳኔ በማጽናት የሰጡት ትዕዛዝ የፍርድ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረታዊ መርህን ለአፈፃፀሙ ምክንያት ከሆነዉ ዉሳኔ ጋር በማገናዘብ የተሰጠ እና በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 39788 በቀን 16/04/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 325009 በቀን 27/04/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 334648 በቀን

03/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡

2. የሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 201128 በቀን 25/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**ሂ/መ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 201142

ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ/ም

***ዳኞች*** ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ ፀሐይ ድሪባ- ጠበቃ አቶ መርጋ ታከለ - ቀርቧል

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ፅጌ ድሪባ- አቶ ተስፋዬ ድርባ ተወካይ ቀርቧል

2ኛ. ቢፍቱ የወተት አምራቾች ማህበር- ተወካይ አቶ ጎሾ ዋቅቶላ ቀርቧል

ለምርምራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ***ፍርድ***

አመልካች የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 27389 ህዳር 3 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 77957 ሰኔ 17 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ያቀረቡትን ይግባኝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 331767 የካቲት 5 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት መሰረዙ እንዲሁም የሰበር አጣሪ ችሎቱም በመዝገብ ቁጥር 336213 ህዳር 1 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ማለቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል በማለት በሰበር ለማሳረም ህዳር 15 ቀን 2013 ዓ/ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ያስቀርባል በመባሉ መዝገቡ ለችሎት ቀርቧል።

***ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም***

ጉዳዩ የገጠር መሬት ይዞታ የውርስ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ ፤አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ። 1ኛ ተጠሪ በሥር ክሳቸው ወላጅ አበታቸው አቶ ድሪባ ጎበና በ1998 ዓ/ም ፣ ወላጅ እናታቸው ወ/ሮ በሬዱ ሆርዶፋ በ2006 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን ገልፀው ከወላጅ አባታቸው ሞት በኋላ መገኛው ፣ አዋሳኞቹ እና መጠኑ በክሱ ላይ የተገለፀው ሚች እናታቸው በፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኙትን የመሬት ይዞታ የሥር ተከሳሾች ይዘው ስለሚገኙ እንዲለቁላቸው ጠይቀዋል።

አመልካችም በመልሳቸው አከራካሪውን ይዞታ ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ በእጃቸው ገብቶ ሲጠቀሙበት የቆዩ በመሆኑ ክሱ በ10 ዓመት ይርጋ ውድቅ እንዲሆንና በፍሬ ነገር ክርክራቸውም ለክርክሩ መነሻ የሆነው መሬት የ1ኛ ተጠሪ እናት የባለይዞታነት መብት የሌላቸው አመልካች የግል ይዞታቸው መሆኑን ሲከራከሩ 2ኛ ተጠሪም በመልሳቸው ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት ያገኘ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን በማስቀደም በእጃቸው ይገኛል የተባለው የመሬት ይዞታ የ1ኛ ተጠሪ ወላጅ እናት ከዚህ ዓለም በሞት ከመለየታቸው በፊት መሬቱ በሌላ ሰው ያልተያዘ መሆኑ ተረጋግጦ በማህበር ተደራጅቶ በሀገር ሽማግሌዎች እና በኮሚቴ ተሰጥቷቸው የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ካርታ ወስደው ለ8(ስምንት) ዓመት የተጠቀሙበት በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም በማለት አማራጭ ክርክር አቅርበዋል። ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ የግራቀኙን ክርክር እና ማሰረጃ ሰምቶ አመልካች በእጇ አለ የተባለውን የመሬት ይዞታ በ1998 ዓ/ም ይዛ የምትጠቀምበት እና በሰሚ ተመዝግቦ መኖሩ ቢረጋገጥም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ይርጋ በደንብ ቁጥር 151/2005 ቁጥር 32 ላይ የተመለከተው 12 ዓመት በመሆኑ በክሱ በ1ኛ ተራቁጥር ሥር የተመለከተው የመሬት ይዞታ በይርጋ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ብይን ሰጥቷል። የፍሬ ነገር ክርክሩ 2ኛ ተጠሪ በሌለበት የቀጠለ ሲሆን የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪን ክርክር ሰምቶ በክሱ በ2ኛ, 3ኛ እና 4ኛ ተራቁጥር የተጠቀሱ የመሬት ይዞታዎችን በተመለከተ ሊጣራ ይገባል ያለውን ጭብጥ ይዞ ማስረጃ ሰምቶ ፣ ኮሚቴዎችን አዋቅሮ ጉዳዩን በማጣራት ባደረገው ምርመራ በክሱ በ2ኛ እና 3ኛ ተራቁጥር የተጠቀሱት የመሬት ይዞታዎች ለ1ኛ ተጠሪ እናት ተወስኖ ትታው የሞተች የውርስ ይዞታ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች እንደ ክርክሯ ስላላስረዳች በክሱ በ2ኛ እና 3ኛ ተራቁጥር የተጠቀሱትን የመሬት ይዞታዎች ለ1ኛ ተጠሪ እንድትለቅ የወሰነ ሲሆን በክሱ በ4ኛ ተራቁጥር ሥር የተጠቀሰው መሬት ለ2ኛ ተጠሪ የተሰጠ መሆኑ መረጋገጡን ገልፆ ከተሰጠው ይዞታ ውጪ 0.75 ሄክታር ድንበር አልፎ የያዘውን የአመልካች ይዞታ እንዲለቅ አስቀድሞ የተሰጠ ውሳኔ ያለ በመሆኑ እና 1ኛ ተጠሪም ይዞታው የራሷ መሆኑን አላስረዳችም በማለት ወስኗል።

አመልካች የወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመቃወም የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔ፡- በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ እናት መካከል ክፍፍል የተደረገው በ1999 ዓ.ም ሲሆን 1ኛተጠሪ በ2011 ዓ/ም የጠየቀችው በ2006 ዓ/ም የሞተችውን እናቷን ውርስ በመሆኑ ፣ እናቷ በሕይወት እያለች ድርሻዋን ይዛ መገኘቷን የሚያረጋግጥ ማሰረጃ ያልቀረበ ቢሆንም ይርጋው የሚቆጠረው የ1ኛ ተጠሪ እናት ከሞተችበት ከ2006 ዓ/ም

ጀምሮ በመሆኑ እና ክርክሩም ወራሽ እና ወራሽ ባልሆኑ ተከራካሪዎች መካከል የተደረገ የውርስ ክርክር በመሆኑ አግባብነት ያለው ይርጋ በውርስ ሕጉ የተመለከተው 10 ዓመት ስለሆነ 1ኛ ተጠሪ እናቷ ከሞተች በአምስት ዓመት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ የሚታገድ ባለመሆኑ አከራካሪው ይዞታ በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ እናት መካከል በተደረግ ክፍፍል የ1ኛ ተጠሪ እናት የሚስትነት ድርሻ ስለሆነ አመልካች የ1ኛ ተጠሪ እናት የሚስትነት ድርሻ የሆነውን ይዞታ የያዘችበት ሁኔታ ህጋዊ መሆኑንና በአከራካሪው ይዞታ ላይ ከ1ኛ ተጠሪ እናት የተሻለ መብት ያላት መሆኑን አላረጋገጠችም በማለት የወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን ያፀና ሲሆን አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበችው የይግባኝ እና ሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል በማለት በሰበር ለማሳረም ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት፡- የወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የ12 ዓመት ይርጋ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ እንዲሁም ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት በፌንፌኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አግባብነት ያለው ይርጋ 10 ዓመት ነው ማለቱ አግባብ ቢሆንም ይርጋው መቆጠር የነበረበት አከራካሪው መሬት በአመልካች ከተያዘበት ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ መሆን ሲገባው 1ኛ ተጠሪ እንዳለችው መሬቱ በ1999 ዓ/ም ተይዟል ቢባል እንኳን 12 ዓመት ሞልቶት እያለ በወረዳ ፍርድ ቤት ያላከራከረ እና በተከራካሪዎች ያልተነሳን መከራከሪያን መሰረት በማድረግ ይርጋው ሊቆጠር የሚገባው ከ2006 ዓ/ም ጀምሮ ነው በማለት የአመልካችን የይርጋ ክርክር ውድቅ ማድረጉ ፤ የ1ኛ ተጠሪ እናት አከራካሪውን ይዞታ ሳትጠቀም እና በአመልካች ላይ ጥያቄ ሳታቀርብ በ2006 ዓ/ም እንደሞተች የተረጋገጠ በመሆኑ በመሬቱ ላይ መብት ቢኖራት እንኳን መብቷን አጥታ የሞተች በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች እናቷ አጥታ የሞተችው መብት ለ1ኛ ተጠሪ ይተላለፋል ማለታቸው እንዲሁም አመልካች 2ኛ ተጠሪን በተመለከተ ያቀረበችው መከራከሪያን ውድቅ በማድረግ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎቱ የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ መቃወሚያን ያለፉበትን አግባብነት ከፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1677(1) እና 1845 እንዲሁም ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ አንፃር ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ይቅረብ በማለት አሟል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በመልሳቸው አከራካሪው መሬት በሟች የ1ኛ ተጠሪ እናት ስም ተመዝግቦ እስከ 2006 ዓ/ም ድረስ ግብር እየተከፈለበት በቁጥጥሯ ሥር አድርጋ ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለየችበት ጊዜ ድረስ ስትጠቀምበት የቆየች በመሆኑ አመልካች መሬቱን በ1999 ዓ/ም ነው የያዝኩት በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ሀሰት ስለሆነ የሥር ፍርድ ቤት ወ/ሮ በራዱ ሆርዶፋ ህዳር 28 ቀን 2006 ዓ/ም መሞቷን አረጋግጦ በክልሉ የመሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 151/2005 መሰረት ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም በወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ከአመልካች ጋር ተከሳሾች ሆኖእያለ በሁለቱ መካከል ክርክር ሳይኖር እንዲሁም ግራቀኙ የተከራከሩበት ይዞታ ለአመልካች ተወስኖ እያለ በ2ኛ ተጠሪ እጅ ያለ በማስመሰል በአመልካች የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት

የለውም በማለት ውድቅ እንዲሆንላቸው ጠይቀዋል። አመልካችም ዋናውን አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል።

የግራቀኙ ክርክር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባ ሲባል የተያዘውን ጭብጥ አግባብነት ካለው የሕጉ ድንጋጌ አንፃር እንደሚከተለው ተመርምሯል። 1ኛ ተጠሪ በ2006 ዓ/ም የሞተችው ወላጅ እናቷ ወ/ሮ በራዱ ሆርዶፋ በ1998 ዓ/ም በክፍፍል ያገኘችው የሚስትነት ድርሻዋ የሆነውን የመሬት ይዞታ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ይዘው ስለሚገኙ አንዲለቁላት በ2011 ዓ/ም ላቀረበችው ክስ አመልካች በሰጠችው መልስ ፤ አከራካሪው ይዞታ ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ በእጃዋ ገብቶ ስትጠቀምበት የቆየች በመሆኑ ክሱ በ10 ዓመት ይርጋ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርባለች። የወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች አከራካሪውን የመሬት ይዞታ በ1998 ዓ/ም ይዛ የምትጠቀምበት መሆኑን ቢያረጋግጥም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ይርጋ በደንብ ቁጥር 151/2005 ቁጥር 32 ላይ የተመለከተው 12 ዓመት ነው በማለት የይርጋ መቃወሚያውን ውድቅ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ ያየው በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፤ በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ እናት መካከል የመሬት ክፍፍል የተደረገው በ1999 ዓ/ም ሲሆን ሟች ወ/ሮ በራዱ ሆርዶፋ ድርሻዋን ይዛ መገኘቷን የሚያረጋግጥ ማሰረጃ ባይቀርብም የስር ከሳሽ የሆነችው 1ኛተጠሪ ክስ ያቀረበችው በ2006 ዓ/ም የሞተችውን እናቷን ውርስ ለመጠየቅ በመሆኑ አግባብነት ያለው ይርጋ በውርስ ሕጉ የተመለከተው 10 ዓመት ስለሆነ ፤ 1ኛ ተጠሪ እናቷ ከሞተች አምስት ዓመት በኋላ ያቀረበችው ክስ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል። ክርክሩ የውርስ ይዞታን የሚመለከት በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 1000(2) ስር የተመለከተው 10 ዓመት ነው መባሉ በአግባቡ ነው። 1ኛ ተጠሪ ሟች እናቷ አከራካሪውን መሬት ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለየችበት ጊዜ ድረስ ስትጠቀምበት የቆየች በመሆኑ አመልካች መሬቱን በ1999 ዓ/ም ነው የያዝኩት በማለት የምታቀርበው ክርክር ሀሰት ነው በማለት የምትከራከር ቢሆንም ክፍፍል ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ አከራካሪው መሬት በሟች የ1ኛ ተጠሪ እናት እጅ ያልገባ እና በአመልካች ተይዞ መቆየቱን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል።

አከራካሪውን መሬት በክፍፍል ለ1ኛ አመልካች እናት የደረሰ ቢሆንም ከአመልካች እጅ አለመውጣቱ ከተረጋገጠ ይርጋው መቆጠር የነበረበት አከራካሪው መሬት በአመልካች ከተያዘበት ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ ነው ወይስ የ1ኛ ተጠሪ እናት ከሞተችበት ከ2006 ዓ/ም ጀምሮ ነው የሚለው ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ማግኘት አለበት። 1ኛ ተጠሪ የምትጠይቀው መብት ከሟች እናቷ በፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 826(2) የሚተላለፍላትን መብት እና ግዴታ ነው። ጥያቄው የሚቀርበው የውርስ ንብረቶቹ መያዛቸው ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አስር ዓመት ድረስ መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 1000 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ መስራት ከሚቻልበት ጊዜ አንስቶ መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 1846 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል። በተያዘው ጉዳይ የ1ኛ ተጠሪ እናት በክፍፍሉ የደረሳት መሬት ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ አመልካች እንድትለቅላት የመጠየቅ መብት ያላት ቢሆንም ይህንን መብቷን ሳትጠቀምበት ሞታለች። ምንም እንኳን 1ኛ ተጠሪ እናቷ በሕይወት እያለች አመልካች አከራካሪውን የመሬት

ይዞታ እንድትለቅላት ለመጠየቅ መብት የሌላት ቢሆንም ፤ የምትጠይቀው ሚች እናቷ በሕይወት እያለች የነበራት መብት በእናቷ እግር ተተክታ በመሆኑ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ እናት ላይ ልታነሳ የሚትችለውን መከራከሪያ በ1ኛ ተጠሪ ላይም የማንሳት መብት ያላት በመሆኑ ፤ የይርጋ ጊዜው መቆጠር የሚገባው አመልካች አከራካሪውን መሬት ከያዘችበት 1999 ዓ/ም መሆን ሲገባው የ1ኛ ተጠሪ እናት ከሞተችበት ከ2006 ዓ/ም ጀምሮ ነው በማለት አመልካች ያቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ሆኖ አመልካች ከ10 ዓመት በላይ በእጇ የቆየውን አከራካሪውን የመሬት ይዞታ ለተጠሪ አንድትለቅ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

## ***ውሳኔ***

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 336213 ህዳር 3 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ፣ ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 321767 የካቲት 5 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 27389 ህዳር 3 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ***ተሻሽሏል***፡፡
2. በክሱ በተራቁጥር 1 ሥር የተመለከተውን የመሬት ይዞታ አስመልክቶ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ***ፀንቷል***፡፡
3. 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ስለሆነ በክሱ በ2ኛ እና 3ኛ ተራቁጥር ሥር የተመለከቱትን የመሬት ይዞታዎች አመልካች ለተጠሪ ሊለቁ አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡
4. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

***ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም***

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት — ሰ/መ/ቁጥር 201201
ሀምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የደነባ ከተማ መሪ ማዘጋጃ ቤት

ተጠሪ ፡- አቶ ጥላሁን ይስማ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርምራ ሲሆን በዚህ አግባብም ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

# ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የከተማ ይዞታን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የሲ.ያ/ዋዩ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ለአከራካሪው ቤትና ይዞታ በተጠሪ ስም የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰርቶ ሊሰጠው ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች መፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አመልካች ስላመለከተ ነው፡፡አመልካች በሲ.ያ/ዋዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡

ተጠሪ ህዳር 23 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስም አቶ ማናዜ መኮንን እና ወ/ሮ እትሞላሽ ደመቀ የነበራቸውን ጋብቻ በፍርድ ቤት አፍርሰው የጋራ ንብረታቸው የሆነውን በደነባ 01

ቀበሌ ሐ ዞን የሚገኘውን ቤትና ቦታቸውን ከተካፈሉ በኋላ ለአቶ ማናዜ የደረሳቸውን 187 ካሜ ቤትና ቦታ በ27/10/2006 ዓም በተደረገ ውል ገዝቼ አመልካችም ውል አዋውሎን፤ውሉን አፅድቆ በስሜ በማዞር የግንባታ ፈቃድ ሰጥቶኝ የነበረውን ቤት አፍርሼ ቤት የሰራሁበት ሲሆን ለይዞታዬ ካርታ እንዲሰጠኝ ስጠይቀው የቀበሌ ቤት አብሮ ስለተሸጠልህ አልሰጥህም ያለ ሲሆን ያሉትን አስተዳደራዊ መንገዶች ሁሉ ተጠቅሜ ጥያቄን ባቀርብም ምላሽ ያላገኘሁ በመሆኑ ለቤትና ለቦታው የባለቤትነት ማስረጃ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጡ በታዘዘው መሰረት አመልካች በሰጠው መልስም የንብረቱ ክፍፍል ሲፈፀም ያላካፈልኩ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ባልና ሚስቱ የያዙት ቦታ 542.58 ካሜ ሆኖ በሰነድ አልባ አጣሪ0 ኮሚቴ ተጣርቶ ህጋዊ ይዞታቸው 432 ካሜ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ቀሪው 110 ካሬ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ የተወሰነ ሲሆን ባልና ሚስቱ ሲካፈል ለተጠሪ ሻጭ 216 ካሜ ይደርሳቸው የነበረ ቢሆንም የሻጭ የቀድሞ ሚስት 364.5 ካሜ የያዙ በመሆኑ በፕላን 64.18 ካሜ ተነስቶ 300.32 ካሜ የያዙ ሲሆን በሰነድ አልባ አጣሪ ኮሚቴው ተጣርቶ ተጠሪ ከያዘው 187 ካሜ ቦታ 110.58 ካሜ የቀበሌ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በቀበሌ ቦታ ላይ ለሰራው ቤት የይዞታ ማረጋገጫ ሊሰጠው አይገባም ተብሎ ይወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች ባቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስም ተጠሪ የያዘውን የቀበሌ ቦታ የሆነውን 110.58 ካሜ ይዞታ የሰራውን ቤት አፍርሶ እንዲያስረክብ ይወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ ለቀረበባቸው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስም ቦታው የቀበሌው ቦታ ስላልሆነና ስለመሆኑም ያልተረጋገጠ ስለሆነ፤ቦታውን በሽያጭ ውል አግኝቼው በስሜ የምገብርበት በመሆኑና ሽያጩ ህጋዊ መሆኑን አመልካች አረጋግጠልኝ የያዝኩት በመሆኑ አመልካች ክሱን ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ ስርዝ ድልዝ ያለው በመሆኑና በሰነድ አልባ ኮሚቴ ተጣርቶ የቀረበው ማስረጃም ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ የቀረበው 42.58 ካሜ ሆኖ እያለ በአመልካች 110.58 ካሜ መጠየቁ አግባብ ባለመሆኑ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔም አከራካሪው ቤትና ቦታ ለተጠሪ በሽያጭ ሲተላለፍ በባለሙያ ተለክቶና ታይቶ ውሉ በማዘጋጃ ቤቱ ተደርጎ የፀደቀ መሆኑን፤ቤትና ቦታው በተጠሪ ስም ተመዝግቦ ግብር የሚገብሩበት ፤ግንባታ በተጠሪ ሲፈፀምም በአመልካች ተፈቅዶለት መሆኑን የቀረቡት ማስረጃዎች የሚያሳዩ መሆኑን፤አመልካች የቀበሌው ይዞታ ምን ያህል እንደሆነ ምን ያህሉ በተጠሪ ተቀንሶ እንደተያዘ ይዞታውም በቀበሌው መመዝገቡን የሚያሳይ ማስረጃ በአመልካች አለመቅረቡ አመልካች በደፈናው 110.58 ካሜ ተጠሪ ወደ ቀበሌው ገብቶ ያዘ በማለት መጠየቃቸውን የሚያሳይ መሆኑን ፤የሰነድ አልባ መሬት አጣሪ ኮሚቴ ሪፖርት ከምስክሮቹ ቃል ጋር የማይጣጣም ስርዝ ድልዝ ያለበት እምነት የማይጣልበት መሆኑን በመጥቀስ የአመልካችን

የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውድቅ አድርጎ አመልካች ለአከራካሪው ቤትና ቦታ ለተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይገባል በማለት ወስኗል ፡፡ይህ ውሳኔ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ፀንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ጥር 04 ቀን 2013 ዓም በተፃፈ ባቀረበው የሰበር አቤቱታም ተጠሪ ቤትና ቦታውን ከአቶ ማናዜ መኮንን የገዛው መሆኑና አመልካችም የሽያጭ ውሉን መዝግቦ የግንባታ ፈቃድ የሰጠው ቢሆንም ይህንን ቤትና ቦታ ለተጠሪ የሸጠለት ግለሰብ ቦታው ነባር ይዞታ በመሆኑ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ የሌለውና የተሟላ ሰነድ የሌለው መሆኑን ሻጩ በስር ፍርድ ቤት ምስክር ሆኖ ያስረዳ በመሆኑ የክልሉ እንዱስትሪ እና ከተማ ልማት ቢሮ ባወጣው የከተማ ቤትና ስመ ንብረት ዝውውር አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 4/2006 አንቀፅ 5(1) መሰረት የባለቤትነት ማስረጃ የሌለው ይዞታ እና ቤት ስመ ንብረት ዝውውር ሊፈፀምበት እንደማይገባ የሚደነግግ ሆኖ እያለ በወቅቱ የነበረው የማዘጋጃ ቤቱ ባለሙያ መመሪያውን በግልፅ በመተላለፍ ህጋዊ ሰነድ የሌለውን ይዞታና ቤት ሽያጭ ውል መመዝገቡና ለተጠሪ የግንባታ ፈቃድ መስጠቱ ተገቢነት የሌለው ህገወጥ ተግባር በመሆኑ ፣

ለይዞታው ካርታ ተሰጥቶ ቢሆን እንኳ የአስተዳደር አካሉ ካርታውን ለማምከን የሚችል መሆኑ በሰ/መ/ቁ.57044 አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቶ እያለ የሽያጭ ውሉ ስለተመዘገበና የግንባታ ፍቃድ ስለተሰጠው ብቻ ፣የሰነድ አልባ አጣሪ ኮሚቴው አቶ መኮንን ለተጠሪ በሽያጭ 110.58 ካሜ የሆነ የቀበሌውን ይዞታ በማጠቃለል ያስተላለፉ መሆኑን አረጋግጦ እያለ ተጠሪ ይህ ይዞታ የቀበሌው አለመሆኑን ባላስረዱበት በየይዞታ ማረጋገጫ ለተጠሪ እንዲሰጥ መወሰኑ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች መፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ አመልካች ለተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርቶ ሊሰጥ አይገባም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ህጋዊ ይዞታው 432 ካሜ ሆኖ ተጠሪ የገዛው ሲጣራ 542 ካሜ በመሆኑ የመንግስት ይዞታ 110 ካሜ ስለያዘ የባለቤትነት ማረጋገጫ ልሰጥ አይገባም በማለት አመልካች እየተከራከረ የባለቤትነት ማረጋገጫ ለተጠሪ እንዲሰጥ የተወሰነበትን አግባብ ለማጣራት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ግንቦት 23 ቀን 2013 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ ተጠሪ የገዛሁት 187 ካሜ ብቻ ሆኖ እያለ አመልካችም ተጠሪ የገዛው 542 ካሜ ነው ብሎ ባልተከራከረበት የማስቀረቢያ ጭብጥ በማድረግ 542 ካሜ እንደገዛው ተደርጎ ጭብጥ መያዙ አግባብ አይደለም፤ተጠሪ ለአቶ ማናዜ የደረሳቸውን 187 ካሜ ቤትና ቦታ በ27/10/2006 ዓም በተደረገ ውል ገዝቼ አመልካችም ውል አዋውሎኝ፤ውሉን አፅድቆ በስሜ በማዞር የግንባታ ፈቃድ ሰጥቶኝ የነበረውን ቤት አፍርሼ ቤት የሰራሁበት ለአመታትም በስሜ ግብር የገበርኩበት በመሆኑ፤የአቶ ማናዜ መኮንን እና ወ/ሮ እትሞላሽ ደመቀ ጋብቻ ፈርሶ ንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ያደረጉት ስምምነት በፍርድ ቤት ፀድቆ አመልካች በፀደቀው የግልግል ውል መሰረት ቦታውን ለክቶ አካፍሎ ድርሻቸውን በየስማቸው መዝግቦ ግብር በድርሻቸው ልክ እንዲገብሩ ያደረገ

መሆኑን በስር ፍርድ ቤት ተገቢውን ማስረጃ በማቅረብ ያስረዳው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ከሰበር ቅሬታው አኳያ እና ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ይዘት አንፃር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል፡፡በመሰረቱ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ ለተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰርቶ ሊሰጥ ይገባል በማለት ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት የሰጠው ማስረጃን የመስማት፤የመመርመርና የመመዘን ስልጣኑን ተጠቅሞ በደረሰው መደምደሚያ በአመልካች የሰበር አቤቱታው ላይ ጭምር ከታመነው ተጠሪ ቤትና ቦታውን ከአቶ ማናዜ መኮንን ሲገዙ አመልካችም የሽያጭ ውሉን መዝግቦ የግንባታ ፈቃድ ከመስጠቱ በተጨማሪ ቤትና ቦታው በተጠሪ ስም ተመዝግቦ ግብር የሚገብሩበት መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባትና በዋነኝነትም አመልካች የቀበሌው ይዞታ ምን ያህል እንደሆነ ምን ያህሉ በተጠሪ ተቀንሶ እንደተያዘ በግልፅ በክሱና ማስረጃው አለማሳየቱን ይዞታውም በቀበሌው መመዝገቡን የሚያሳይ ማስረጃ በአመልካች አለመቅረቡን እንዲሁም ይዞታውን በተመለከተ የቀረበው የሰነድ አልባ ይዞታ አጣሪ ኮሚቴ ሪፖርት ከምስክሮቹ ቃል ጋር የማይጣጣም እና ስርዝ ድልዝ ያለበት በዚህም ምክንያት እምነት የማይጣልበት መሆኑን በመጥቀስ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ያሳያል፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን የመስማት፤የመመዘንና የመመርመር ስልጣናቸውን በመጠቀም በፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ የሚደርሱበት መደምደሚያ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10(1) እና በህገ መንግስታችን አንቀፅ 80(3)(ሀ) መሰረት በስር ፍርድ ቤቶች የተፈፀመን መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን ብቻ በተሰጠው በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚታረሙ ሆነው ስላልተገኙ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1.የሲ/ዋዩ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0114877 የካቲት 26 ቀን 2012 ዓም የሰጠው ፍርድ እና ይህንን ፍርድ በማፅናት የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0133422 መስከረም 27 ቀን 2013 ዓም እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.03-11887 ህዳር 17 ቀን 2013 ዓም የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንተዋል፡፡

2.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

**ክርክሩ ተገቢውን እልባት ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ሠ/ኃ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ 201235

ህዳር 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አብዲ አሚን አሊሾ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ መሳ ኡስማን ዑመር

2ኛ. ወ/ሮ ደሃቦ አብደላ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 06/05/2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 75621 በቀን 14/12/2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 16162 በቀን 08/04/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ የጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት አቤቱታ ነው።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች በቀን 03/11/2011 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ በድሬዳዋ አስተዳደር ጆሎ በሊና ገጠር ቀበሌ ልዩ ስፍራው ኢጃነኒ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኝ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰ 1000 ካ/ሜ በግምብ አጥር የታጠረ ይዞታና ግምቱ 50,000.00 ብር የሆነ መኖሪያ ቤት ያለኝ ሲሆን ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በእውነት በእጄ አድርጌ እያዘዝኩበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እገኛለሁ። ይሁን እንጂ ተከሳሾች ምንም አይነት መብት ሳይኖራቸው ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ በይዞታው ላይ በሃይል የተደገፈ ሁከት እየፈጠሩብኝ ይገኛሉ። በተደጋጋሚ ሁከቱን እንዲያቆሙ በግልም ይሁን በሽማግሌ ባስጠይቃቸውም ሁከቱን ሊያቆሙ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው የፈጠሩትን ሁከት እንዲወገድ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

ተጠሪዎች በሰጡት መልስ ክርክር የተነሳበት ይዞታ ተከሳሾችና ቤተሰቦቻችን ለ17 አመት የምንገለገልበት የግል ይዞታችን እንጂ የከሳሽ ይዞታ አይደለም። አከራካሪው ይዞታ በእኛ እጅ የሚገኝ ራሳችን የምናስተዳድረው ነው፤ ከሳሽ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1140 መሰረት ይዞታውን በእጁ አድርጎ የማያስተዳድረው በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1149 መሰረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊያቀርብ አይችልም። ከሳሽ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን በቀርሳ ወረዳ ወተር ከተማ ነዋሪ ሆኖ አከራካሪው ይዞታ የሚገኝበት በድሬዳዋ አስተዳደር ጀሎ በሊና በቀበሌ ያለውን ይዞታ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በእጁ አድርጎ የሚይዝበት ምክንያት የለም። ከሳሽ ከህግም ይሁን ከውል የመነጨ መብት የለውም። በመሆኑም የከሳሽ ክስ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ከቀረቡት የከሳሽና ተከሳሾች ምስክሮች እንዲሁም ከጀሎ በሊና ገጠር ቀበሌ የመጣው የሰነድ ማስረጃ አንጻር ሲመዘን የእርሻ መሬቱ አመጣጥ የ1ኛ ተከሳሽ የነበረ መሆኑ በኋላ ላይ ግን 1ኛ ተከሳሽ ለከሳሽ በብር 100,000.00 ባዶ መሬት የሸጠለት መሆኑ፤ በዚህም መነሻነት ከሳሽ በግምት 1000 ካ/ሜ የሚሆነውን ከ1ኛ ተከሳሽ የገዛውን ባዶ መሬት በግንብ ያጠረው መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል። ከሳሽ ይህን ከ1ኛ ተከሳሽ የገዛውን ባዶ መሬት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በግንብ አጥሮ በይዞታው ስር አድርጎ የሚጠቀምበት መሆኑም ተረጋግጧል። ከሳሽ አከራካሪውን ይዞታ በሽያጭ ውል ከ1ኛ ተከሳሽ ያገኘው መሆኑን ከከሳሽ ምስክሮች የተረጋገጠ በመሆኑ የከሳሽ ይዞታ መብት ከውል የመነጨ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዷል። ከሳሽ ከ1ኛ ተከሳሽ የገዛው መሬት ባዶ መሬት በመሆኑ ህገ መንግስቱን አንቀጽ 40(3) እና የፍ/ብ/ህ/ቁ 1678(ለ) የጣሰ ነው፤ በመሆኑም ውሉ እንዲፈርስ ከተዋዋዮች አንዱ ወይም ማንኛውም ጥቅም ያለው ሰው መጠየቅ እንደሚችል የፍ/ብ/ህ/ቁ 1808(2) አስቀምጧል። በመሆኑም ውሉ ፈራሽ ነው። ከሳሽ አከራካሪውን ይዞታ ያገኘው ህገወጥ ውል መሰረት በማድረግ ስለሆነ ውሉ ከመጀመሪያውኑ እንዳልተደረገ የሚቆጠር ነው። ህገወጥ በሆነ ውል አማካኝነት የተቀባበሉትን በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815(1) መሰረት ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባል። ከሳሽ በውሉ አማካኝነት ለ1ኛ ተከሳሽ የከፈለው ገንዘብ ብር 100,000.00 ከ1ኛ ተከሳሽ ሊመለስለት ይገባል፣ በምላሽ የተረከበውን መሬት በነበረበት ሁኔታ ለ1ኛ ተከሳሽ ሊመልስ ይገባል። ስለሆነም

ተከሳሾች በህገ ወጥ ውል ወይም በፈራሽ ውል ያስተላለፉትን መሬት መልሰው መያዛቸው የሁከት ተግባር አይደለም። ሊወገድ የሚገባው ሁከት የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ከሳሽ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ለክርክር መነሻ የሆነውን ይዞታ በተመለከተ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1140 መሰረት በእውነት የሚያዝበት የይ/ባይ ይዞታ ነው? ይ/ባይ በዚህ ይዞታ ላይ የህውከት ይወገድልኝ አቤቱታ ሊያቀርብበት የሚችል ነው? የስር ፍርድ ቤት ግራቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ በማለት የሰጠው ውሳኔ ከቀረበው ክስ እና ከግራቀኙ ክርክር አንፃር ተገቢ ነው? የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ ውሳኔ ሰጥቷል። በሰጠው ውሳኔ ቀበሌው በጉዳዩ ላይ በጻፈው ማስረጃ ይ/ባይ እና 1ኛ መ/ሰጪ በነበራቸው የሽያጭ ውል መሰረት ይ/ባይ ይህን ይዞታ የያዘው መሆኑን ከመግለፅ ውጪ አከራካሪው ይዞታ የይ/ባይ መሆኑን አላረጋገጡም፤ ይ/ባይም በምን አግባብ ይህን ይዞታ የያዘ ስለመሆኑ አላረጋገጠም፤ ቦታው የገጠር መሬት እንደመሆኑም የገጠር መሬት ሊገኝባቸው በሚገኝባቸው መንገዶች ስለመገኘቱም የቀረበ ማስረጃ የለም፤ ቦታው ወደ ከተማ የተከለለ ነው የሚባል ከሆነም አሁንም ይህንኑ ሊያረጋግጥ የሚችል ምንም አይነት ማስረጃ አላቀረበም። የስር ፍርድ ቤት ይዞታው በሽያጭ የተገኘ ስለመሆኑ ቢገልፅም ህጋዊ የቤት ሽያጭ ውል ስለመኖሩ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አልቀረበም። በአጠቃላይ ይ/ባይ በእውነት ሊያዝበት የሚችል የራሱ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባለመቅረቡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1140 እና 1149 መሰረት ሁከት ይወገድልኝ በማለት አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችልበት የህግ መሰረት የለም። በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም። ግራቀኙ ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት የሰጠውን ውሳኔ በተመለከተ ይ/ባይ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ሁከት ይወገድልኝ የሚል ሲሆን በመ/ሰጪ በኩልም የቤት ሽያጭ ውል ወይንም የመሬት ሽያጭ ውልን በተመለከተ የቀረበ ክርክር የለም። በመሆኑም በሁለቱም በኩል ውልን በተመለከተ የቀረበ ክርክር ባለመኖሩና በፍ/ብ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 182(2) አንጻር ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው ከተጠየቀው ዳኝነት አንጻር በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ይህን በማለፍ ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም። በሌላም በኩል የህገወጥ መሬት ሽያጭ ውል ስለመኖሩ በአግባቡ በጭብጥነት ተይዞ በማስረጃ አጣርቶ ክርክር ሳይደረግበት ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት የተሰጠው ውሳኔና የተደረሰበት ድምዳሜ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182(2) ያላገናዘበ ነው። በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሻሽሏል፤ ይ/ባይ ህውከት ፈጠሩብኝ በማለት ያቀረቡት የህውከት ይወገድልኝ አቤቱታ ውድቅ ተደርጓል፤ የስር ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት የሰጠው ውሳኔ አቤቱታ ባልቀረበበት ጉዳይ እና የክርክሩ ጭብጥ ባልሆነበት ጉዳይ የተሰጠ በመሆኑ ተሽሯል በማለት ወስኗል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች በቀን 06/05/2013 ዓ/ም ባቀረቡት ማመልከቻ ተፈፀመ የሚሉትን ስህተት ዘርዝረው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ተጠሪዎች እየፈጠሩ ያለውን ሁከት ያቁሙ ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል። ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጎ ግራቀኙ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር መልስና የመልስ መልስ ተለዋውጠዋል።

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ሁለቱም ወገኖች ያቀረቡትን ክርክር፤ ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የስር ፍርድ ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል።

ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ባቀረቡት ክስ ተጠሪዎች ምንም አይነት መብት ሳይኖራቸው ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ በይዞታየ ላይ በሃይል የተደገፈ ሁከት እየፈጠሩብኝ ስለሆነ የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው አከራካሪው ይዞታ በእኛ እጅ የሚገኝ ራሳችን የምናስተዳድረው ነው፤ አመልካች ይዞታውን በእጁ አድርጎ የሚያስተዳድረው አይደለም፤ በይዞታው ላይ ከህግም ይሁን ከውል የመነጨ መብት የለውም በማለት ተከራክረዋል።

የስር ፍርድ ቤት ከፍ ሲል እንደተገለፀው አመልካች ይዞታውን በሽያጭ ውል ከ1ኛ ተጠሪ ያገኙ መሆኑ በአመልካች ምስክሮች ተረጋግጧል፤ ውሉም ህገወጥ በመሆኑ ፈራሽ ነው፤ ህገወጥ በሆነ ውል አማካኝነት የተቀባበሉትን በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815(1) መሰረት በመመላለስ ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ ሊመለሱ ይገባል፤ ተጠሪዎች በህገ ወጥ ውል ያስተላለፉትን መሬት መያዛቸው የሁከት ተግባር አይደለም በማለት ወስኗል። ይግባኝ ሰሚው ችሎት በበኩሉ ውሳኔውን አሻሽሎ አመልካች በእውነት ሊያዝበት የሚችል የራሱ ይዞታ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባለመቅረቡ ሁከት ይወገድልኝ በማለት አቤቱታውን ሊያቀርቡ አይችልም፤ ህውከት ፈጠሩብኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ ነገር ግን የስር ፍ/ቤት ባልተጠየቀ ዳኝነትና ከክርክሩ ውጪ የውሉን ጉዳይ ተመልክቶ ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት ይመለሱ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል በማለት ወስኗል።

በመሰረቱ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊቀርብ የሚችለው በይዞታው በእውን በሚያዘው ሰው ሰላማዊ የይዞታ አጠቃቀም ላይ ችግር ወይም መሰናክል ሲፈጠር ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1140 እና 1149 ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል። በዚህ መልኩ ለቀረበው ክስ የሚሰጠው ዳኝነትም የተነሳው ህውከት እንዲወገድ እንዲሁም ስለደረሰ ጉዳት ኪሳራ እንዲከፈል ሊሆን ይችላል። በተለይ ተከሳሽ አድራጎቱን የሚፈቅድ መብት እንዳለው በፍጥነትና በማይታበል

ዓይነት ካላስረዳ በቀር ህውከቱ እንዲወገድ እንደሚታዘዝ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1149(3) ሥር ተመልክቷል፡፡ በአንፃሩም ሁከቱን ፈጠረ ከተባለው ሰው ጋር የተደረገ በውል ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ካለ ግንኙነቱ የሚገዛበት የውልና የህግ አግባብ ተለይቶ ራሱን ችሎ ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአከራካሪው ይዞታ አመልካች በእውነት ሊያዝበት የሚችል የራሱ ይዞታ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያልቀረበ ስለመሆኑ ፍሬ ነገርን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህግ ስልጣን በተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ህውከት ይወገድልኝ ተብሎ የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲሆን መወሰኑ ከፍ ሲል የተመለከተውን የህጉን ይዘትና መንፈስ የተከተለ በመሆኑ የህውከት ይወገድልኝ ክሱን ውድቅ በማድረግ ረገድ የተላለፈው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘንውም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር አድርገውታል የተባለው የሽያጭም ሆነ ሌላ ውል ህጋዊነት እንዲሁም ውል ፈርሶ ግራቀኙ ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን ከህውከት ክሱ ጋር ተያይዞ ዳኝነት እንዲሰጥበት የቀረበ አቤቱታ ባለመኖሩና በውል ላይ የተመሰረተው ግንኙነት ይኸው በሚገዛበት የውልና የህግ አግባብ እራሱን ችሎ ሲጠየቅ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ከተጠየቀው ዳኝነት በማለፍ ያሳለፈው ውሳኔ ክርክሩ የሚመራበትን ስርዓት እና ከላይ የተጠቀሱትን የህጉን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የተከተለ ባለመሆኑ ውሳኔው በዚህ ረገድ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መታረሙ በአግባቡ ነው፡፡

በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 16162 በቀን 08/04/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

2. አመልካች ህውከት ይወገድ በሚል ያቀረቡት ክስ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው፡፡

3. በአንዣሩ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ አደረጉ የተባለውን ውል በተመለከተ አቤቱታ ሲቀርብ የውል ግንኙነቱ ከሚገዛበት የውልና የህግ አግባብ አንፃር ታይቶ ዳኝነት ሊሰጥበት ከሚገባ በቀር አመልካች ካቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ የዳኝነት ጥያቄ ጋር ተያይዞ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰጠቱ የተጠየቀውን ዳኝነት እና ህጉን የተከተለ አይደለም ብለናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁጥር 201235
ቀን 28/3/2014 ዓ/ም

**ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የምገኘው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን እንደምከተለው አስቀምጫለሁ**

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጡት ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ሲሆን በስር ፍ/ቤት በነበረው ክርክር የአሁን አመልካች በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ የአሁን ተጠሪ በመሬት ይዞታዬ ላይ ሁከት ስለፈጠረብኝ ሁከት ያቁምልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ የአሁን ተጠሪም የፈጠርኩት ሁከት የለም ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም አከራክሮ የአሁን አመልካች ክስ ያቀረበበት የመሬት ይዞታ ከተጠሪ በሽያጭ ውል አግኝቻለሁ የሚል በመሆኑ የአሁን አመልካች በህገ መንግስቱ የተከለከለውን የመሬት የሽያጭ ውል መሰረት አድርጎ አግኝቻለሁ በሚለው የመሬት ይዞታ ላይ ሁከት ተፈጥሮብኛል ሲል የሁከት ክስ ሊያቀርብበት የማይችል ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 36645 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት በህገ ወጥ መንገድ ያዝኩ በሚለው መሬት የሁከት ክስ ሊያቀርብበት አትችልም፡፡ እንዲሁም ህገ ወጥ ውል በክርክርነት የቀረበ እንደሆነ ሌላ ክስ ማቅረብ ሳያስፈልግ በተያዘው የሁከት ክስ መዝገብ ላይ ተቀባይነት እንደሌለው መወሰን እንደሚቻል የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 79394 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የአሁን አመልካች በሽያጭ ውል ይጥለሁ ሲል ያቀረበው የሁከት ክስ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔን እንደተገነዘብኩት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምን መሰረት በማድረግ የአሁን አመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ክፍል ተገቢ ሆኖ፣ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ሲል የሰጠው ውሳኔ ክፍል ግን ሊታረም የሚገባው ጉዳይ ነው እላለሁ፡፡ ምክንያቱም የመሬት ሽያጭ ውል በህገ መንግሰቱ የተከለከለ ህገ ወጥ ውል ነው፡፡ የመሬት ሽያጭ ውል ከመጀመሪያውኑ እንደውል የማይቆጠር ፈራሽ ውል በመሆኑ በቀረበው የሁከት ክስ ክርክር ውሉ ተቀባይነት እንደሌለው ውሳኔ ሲሰጥ በህገ ወጥ ውሉ ካለ አግባብ ብልጽጎል የሚል ወገን ካለ በዚሁ አግባብ ከመጠየቅ በቀር ህገ ወጥ የመሬት ሽያጭ ውል በፍርድ ቤት ውሳኔ ፈራሽ እንደተደረገ ተወስዶ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ በሚል ውሳኔ መስጠቱ ህጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ ሌላው የአሁን አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም አከራክሮ በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች ላቀረበው የሁከት ክስ ይዞታው በእጁ የነበረ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባልተጠየቀ ዳኝነት ስለ ውል ጉዳይ አንስቶ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባል ብሎ በውጤት ደረጃ የፌደራል የመጀሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማስረጃ የመስማትና የመመዘን በተሰጠው ሥልጣን አንጻር የአሁን አመልካች ክስ ያቀረበበት የመሬት ይዞታ በእጁ ያልነበረ መሆኑን አረጋግጦ ሁከት የለም ብሎ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ክስ ያቀረበበትን የመሬት ይዞታ ከአሁን ተጠሪ ላይ በሽያጭ ውል የገዛው ስለመሆኑ በማስረጃ ያረጋገጠ በመሆኑና የመሬት ሽያጭ ውል በህገ መንግስቱ የተከለከ ስለሆነ ከመጀመሪያውኑ ፈራሽ በመሆኑ የውል ይፍረስልኝ ክስ ማቅረብ ሳያስፈልግ በተያዘው መዝገብ ላይ ሕገ ወጥ ውሉን ውድቅ ማድረግ እንደሚቻል የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 79394 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት የአሁን አመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ እያለ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የህገ ወጥ የመሬት ሽያጭ ውል ክርክራቸው ውጪ ነው ሲል የሰጠው እርማት ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም መጀመሪያውኑ የአሁን አመልካች ክስ ማቅረብ መቻል የሚገባውና ይህን ባላሟላበት ይዞታው በማን እጅ ነበር ወደ ሚለው ጉዳይ ማለፍ አስፈላጊም ስለማይሆን ነው፡፡ ይህም ሆኖ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ከላይ በተገለጸው መሰረት እርማት በማድረግ በውጤት ደረጃ ክሱ ውድቅ መደረጉን ማጽናት ሲገባ የመሬት ሽያጭ ውል መጀመሪያ በፍርድ ቤት ውሳኔ ፈራሽ መደረግ ነበረበት

**የሚል ምክንያታዊ እርማት ውሳኔ መስጠቱ እንደ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ህገ ወጥ የመሬት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ ክስ ሊቀርብ ይገባል ብሎ ውሳኔ መስጠት የመሬት ሽያጭ ውል ከመጀመሪያውኑ ፈረሽ መሆኑ እየታወቀ ካለአግባብ እንደገና ግራ ቀኙን ለሌላ ያልተገባ ክርክር የሚጋብዝ፣ ላልተገባ ወጪ እና ተጨማሪ ጊዜ ብክነት የሚዳረግ፣ ህገ ወጥ የመሬት ሽያጭ ውልን እውቅና የሚሰጥ፣ የራሱን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 79394 ላይ የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም የሚጻረር፣ የውል መሰረታዊ መርሆን የሚጻረር እና የፌደራል ህገ መንግስትን የሚጻረር ውሳኔ ስለሚሆን ተገቢነት ያለው ውሳኔ አይደለም እላለሁ፡፡**

**የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት**

**ማ/አ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 201252
መስከረም 28 ቀን 2014ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ
ፀሐይ መንክር
ኑረዲን አድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ፮ አለቃ ሰቦቃ መገርሳ - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እቴነሽ ወንድሙ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 333318 ሕዳር 1ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ እንዲታረምላቸው ስለጠየቁ ነው።

ክርክሩ በተጀመረበት የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፊንፊኔ ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች አሻሽለው ባቀረቡት ክስ ሆሎታ ከተማ ጎሮ ቁረንሳ ቀበሌ አዋሣኙ በክሱ ላይ የተዘረዘረውንና በ250 ካሬ ቦታ ላይ በእንጨት እና በጭቃ የተሰራውን 3 ክፍል የግል ቤታቸውን ተጠሪ የወንድማቸው ሚስት ስለሆኑ የራሳቸውን ቤት እስከሚሰሩ ድረስ በነፃ እንዲኖሩበት ሰጥተዋቸው ሲኖሩበት ቆይተው እንዲለቁላቸው ከ2003 ዓ/ም ጀምሮ ሲጠየቁ ፍቃደኛ ስላልሆኑ በፍርድ ሀይል እንዲለቁ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል።

ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች በዚህ ጉዳይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 214887 ክስ አቅርቦባቸው የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ስለሆነ በድጋሚ ክስ ሊቀርብበት የማይገባ መሆኑንና የቤቱ ግምትም በባለሙያ የተገመተ አለመሆኑን በመጀመሪያ መቃወሚያነትና ይዞታዉ በአመልካች ስም የተመዘገበ ቢሆንም አመልካች የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰራዊት አባል ስለነበሩ ሰራዊቱ ሲበተን ሰራ በማጣታቸው በ1984 ዓ.ም የሰራ መፈለጊያ እንዲሆናቸው መሬቱን ለተጠሪና ለባለቤታቸው መሬቱን ትተው ገንዘብ ተቀብለው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ድሬዳዋ መሐዳቸውን በዚህ መሰረት በመጀመሪያ በ6 ቆርቆሮ ቤት ሰርተው ቆይተው ይህን ቤት በ1991ዓ.ም አፍርሰው ሌላ ሁለት 2 ክፍል ቤት ሰርተው ለ22ዓመታት ያለ ተቃውሞ እየኖሩበት ሣለ በ1994 ዓ.ም ባለቤታቸው ስለሞቱ አመልካች ለለቀሶ ሲመጣ የቤቱን ካርታ ላስተካክለው በሚል ከልጃቸው አታለው ከተቀበሉ በኋላ በስማቸው ግብር መክፈል ጀመሩ እንጅ ለ22 ዓመታት ስጠቀምበት ቆየሁ የሚለው የአመልካች ክስ እውነት አይደለም ሲሉ ተከራክረዋል። የስር ፍርድ ቤት የተጠሪን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት አመልካች ሰርቶ በነፃ እንዲኖሩበት ሰጥቷቸው አለቅም ብለዋል ወይስ ተጠሪ ራሳው ሰርተው የሚኖሩበት ቤት ነዉ? በማን መቼ ተሰራ? የሚለዉን የክርክር ጭብጥ ይዞ የግራ ቀኝ ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጀዎች መርምሯል።

በቀረበዉ የሰነድ ማስረጃ የቤቱ ካርታ በአመልካች የተሰጠና ግብርም በአመልካች ስም የሚከፈል መሆኑ ቢረጋገጥም አመልካች ለክርክሩ ምንስዔ የሆነውን ቤት ራሱ እንደሰራ ቢከራከርም በቀረቡት የግራ ቀኙ ምስክሮች ቤቱን ተጠሪ ሰርተው እየኖሩበት ስለመሆኑ በመረጋጡና አመልካች ተጠሪ ቤቱን ሲሰሩ እንደተቃወመ ያልተከራከረ በመሆኑ በፍትሐ ሕግ ቁጥር 1179/1/ ድንጋጌ መሰረት የቤቱ ባለቤት ተጠሪ ናቸው ሲል የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጓል። በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኙት አመልካች የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታቸውን በየደረጃው ለሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች አቅርበው ተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ከተከራካሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤቱ ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚለው አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል።

አመልካች ጥር 13 ቀን 2013 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40(7) የተደነገገውን የባለይዞታ መብት በሚፃረር መልኩ የስር ፍርድ ቤቶች የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1179ን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ መወሰናቸው፣ ተጠሪም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነበራቸው ክርክር እና በዚህ መዝገብ ላይ የተለያየ ክርክር እያቀረቡ መሆኑ ቤቱንም በሕገወጥ መንገድ ስለመያዟ በተረጋገጠበት ቀደም ሲል ተጠሪ በሌለችበት በተደረገ ክርክር ለክርክሩ መንስዔ የሆነው ቤት የአመልካች ስለመሆኑ በተረጋገጠበትና በአመልካች በኩል የተለየ ማስረጃ ሣይቀርብ ክሱ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በአመልካች የተሰራና በስማቸውም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ በቀረቡት የሰነድ ማስረጃ እና በሰው ማስረጃ አስረድተው ባለበት የተጠሪ ተጨማሪ ክፍል ቤት ሰርተዋል በማለት አመልካች የቤቱ ባላቤት አይደሉም በሚል የተወሰነበት አግባብነት ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1195 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አንፃር ተጣርቶ እንዲወሰን ተጠሪም የመልስ ክርክር እንዲያቀርቡ ታዞ የፅኑፍ ክርክሩ ተጠናቋል።

ተጠሪ በበኩላቸው የካቲት 17 ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ መልሣቸው አመልካቹ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበውን የክርክር ይዘት ሆነ ብሎ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ መደበቁን፣ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች በ1983 ዓ/ም ባደ መሬት ትቶ ከተጠሪና ባለቤታቸው ገንዘብ ተቀብሎ ወደ ድሬዳዋ ከሄደ በኋላ ተጠሪና

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ባለቤታቸው ቤቱን ሰርተው መኖራቸውን አከራካሪውን ቤት አመልካች አለመስራቱንና ቤቱ ለአንድ ቀንም በአመልካች እጅ ገብቶ የማያውቅ መሆኑ በምስክሮች ስለተረጋገጠ ካርታ መያዙ ብቻውን የቤቱ ባለቤት ነው የሚያሰኘው ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈፅመዋል የሚያሰኛቸው ባለመሆኑ ውሣኔው እንዲፃና ተከራክረዋል። አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር ተጠናቋል።

ክፍ ሲል የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና የግራ ቀኙን ክርክር ሲሆን አከራካሪው ቤት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1179 በሚደነግገው መሰረት የተጠሪ ነው ተብሎ በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በተመለከተ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተው ተምርምሯል። እንደተመረመረው አመልካች ባቀረቡት ክስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የግል ቤታቸው መሆኑን ከ1996ዓ/ም ጀምሮ ተጠሪ የራሣቸውን ቤት እስከሚሰሩ ድረስ በነፃ እንዲኖሩ ፈቅደውላቸው በ2003ዓ/ም ጀምሮ ግን እንዲለቁላቸው ሲጠይቁ ፈቃደኛ ስላልሆኑ በፍርድ ሐይል ተገደው እንዲለቁላቸው እንዲወሰንባቸው ጠይቀዋል። ተጠሪ በበኩላቸው ቤቱ የተሰራበት ይዞታ በአመልካች ስም የእርሣቸው ባለቤት በ1983ዓ/ም ተመርተው አመልካች ከስራ ሲፈናቀሉ በተጠሪዎች ሲረዱ ቆይተው በ1984ዓ/ም ለስራ መፈለጊያ ከተጠሪና ከባለቤታቸው ገንዘብ ተቀብለው ወደ ድሬዳዋ ከሄዱ በኋላ ተጠሪና ባለቤታቸው በይዞታው ላይ በስድስት ቆርቆሮ ቤት ሰርተውበት ከቆዩ በኋላ ይህን ቤት በ1991 ዓ/ም አፍርሰው ሁለት ክፍል ቤት በአዲስ መልክ ሰርተው በመኖር ላይ ሣሉ በ1994ዓ/ም ባለቤታቸው ሲሞቱ አመልካች ለለቅሶ መጥቶ ከዚህ በኋላ ግብር መክፈል አትችሉም በሚል ማስረጃውን ከልጃቸው መቀበላቸውን በአሀኑ ጊዜ በ54 ቆርቆሮ ዋና ቤት በ21ቆርቆሮ ሰርቪስ ቤት ሰርተው ለ22ዓመታት ያለ ተቃውሞ የኖሩበት ቤታቸውን ይዞታው በአመልካች ስም በመመዝገቡ ብቻ እንዲለቁ መጠየቁ ተገቢነት የለውም ሲሉ ይከራከራሉ።። በቃል ክርክር ወቅት አመልካች ሶስቱን ክፍል ቤት በ1983ዓ/ም ራሣቸው የሰሩ መሆኑን ሌላውን ቤት ተጠሪ የሰሩ ቢሆን እንኳ የግምቱን አንድ አራተኛ ከሚጠይቁ በስተቀር ቤቱን አንዳትለቅ የሚያበቃ ህጋዊ ምክንያት አይደለም ሲሉ ተከራክረዋል።

በስር ፍርድ ቤት ቀርበው የተደመጡት የአመልካች 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች በጥቅሉ አመልካች በ1983ዓ/ም ሁለት ክፍል ቤት ሰርቷል ሲሉ የመሰክሩ ቢሆንም ቀሪ ምስክሮች አመልካች በይዞታው ላይ ቤት ስለመስራታቸው አልመሰከሩም። በሌላ በኩል ሁሉም የአመልካች ምስክሮች አመልካች እንደሚያቀርቡት ክርክር በአከራካሪው ቤት ውስጥ ገብተው መኖር የጀመሩት ባለቤታቸው(የአመልካቹ ወንድም) ከሞቱ በኋላ ከ1996ዓ/ም ጀምሮ የራሣቸውን ቤት እስኪሰሩ ድረስ በአመልካች መልካም ፈቃድ ስለመሆኑ አላረጋገጡም። ይልቁንም የአመልካች ምስክሮች አከራካሪው ቤት ውስጥ ተጠሪ መኖር የጀመሩት ባለቤታቸው ከሞሞታቸው በፊት መሆኑን፣ የአመልካች ወንድም ከመሞታቸው በፊትም በይዞታው ላይ በራሳቸው ወጪ ተጨማሪ ቤት ሰርተው እየኖሩ እያለ እዚሁ ቤት ውስጥ መሞታቸውን መስክረዋል። በአንፃሩ በተጠሪ በኩል የቀረቡት ሁሉም ምስክሮች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት እንዲሁም አጥር አመልካች ሣይቃወሙ ተጠሪና ባለቤታቸው ሰርተው ከ1991ዓ/ም ሲኖሩበት እንደነበርና አመልካች ቤቱ የኔነው ማለት የጀመሩት የተጠሪ

ልጅ አረብ ሐገር ሄዳ ሰርታ ባገኘችው ገንዘብ ለእናቷ (ተጠሪ) ሌላ ቤት ከሰራችላቸው በኋላ መሆኑን አረጋግጠዋል።

አንድ ሰው በተለያዩ መንገድ የግል ሀብት ሊያገኝ እንደሚችል የፍትሐ ብሔር ሕጋችን ሶስተኛ መፅሐፍ አንቀፅ ሰባት የሚደነግግ በመሆኑ ከእነዚህ መንገዶች መካከል ደግሞ በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ባለይዞታው ሣይቃወመው ህንፃ የሰራ እንደሆነ የሕንፃው ባለቤት ሕንፃውን የሰራው ሰው እንደሆነ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1179(1) ይደነግጋል። ባለይዞታው ወይም ባለርስቱ ሣይቃወም በይዞታው ላይ በሌላ ሰው ሕንፃ የተሰራ እንደሆነ የሕንፃው ባለቤት ህንፃውን የሰራው ሰው ነው ቢባልም እንኳ ግምቱን በመክፈል ሕንፃውን የማስለቀቅ የባለይዞታው መብት መሆኑን ወይም ባለሕንፃው ክፈለን ሕንፃውን በራሱ ወጪ አፍርሶ መሬቱን ለባለይዞታው መልቀቅ አማራጩ ለባለሕንፃው የተሰጠው መሆኑን የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1179(2) ወይም 1180 ይደነግጋሉ። ይህ ድንጋጌ የተደነገገው መሬት የባለይዞታው ወይም የባለርስቱ የግል ሀብት በነበረበት የመሬት ስርዓትን ታሣቢ በማድረግና በባለይዞታው ሣይቃወም በመሬቱ ላይ የተሰራው ህንፃ የመሬቱ ተቀጥላ ወይም ተጨማሪ ነገር ሆኖ ይቆጠር በነበረበት የሕግ ፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል። ሆኖም አሁን በስራ ላይ ባለው የመሬት ስሪት ስርዓት የገጠርም ይሁን የከተማ መሬት ባለሃብቶች ህዝብና መንግስት እንጅ ግለሰቦች አይደሉም። በመሆኑም ይህ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 105125 እንደሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1178፣ 1197(2)ና 1180 ድንጋጌዎች በአሁኑ ጊዜ ሲተረጉሙም ይሁን በተግባር ሲውሉ አሁን ያለውን የመሬት ስሪት ስርዓት ወይም መሬት የሕዝብና የመንግስተ መሆኑን ተሣቢ በማድረግ ሊሆን ይገባል።

ከዚህ በመነሣት አመልካች በቃል ክርክር ወቅት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ራሱ እንደሰራው የተከራከረና ካቀረባቸው ምስክሮች መካከል ሁለቱ ብቻ ከ1983ዓ/ም በፊት አመልካች ሁለት ክፍል ቤት የሰራ መሆኑን የመሰከሩ ቢሆንም ይዞታው በአመልካች ስም ከተመራበት ጊዜ ጀምሮ በይዞታው ላይ ተስርቶ የነበረውንም ይሁን በአዲስ መልክ የተሰራውን ዋና ቤት ኩሽናና ሳጥር ተጠሪና ባለቤተቻው ሰርተው ከ1991ዓ/ም ጀምሮ እንደሚኖሩበት በተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክሮች በተሻለ አስረድተዋል የሚል መደምደሚያ መደረሱ ተገቢነት ያለው ምዘና ነው ብለናል። ይህ ከሆነ አመልካች ቤቱን ሰርተው ተጠሪ ቤት እስከሚሰሩ ድረስ እንዲኖሩበት ስለመስጠታቸው ብቻ እንጅ ቤቱ በይዞታቸው ላይ የተሰራው እየተቃወሙ መሆኑን ወይም መቃወም በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው መሆኑን በመዘርዘር ህጉን መሰረት ያደረገ ግልፅ ክርክር ባላቀረበቡት የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1179(1) በሚደነግገው መሰረት የቤቱ ባለቤት ተጠሪ ናቸው ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ ነው የሚያሰኝ ምክንያት ባለማግኘታችን ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል።

## ውሣኔ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

1) የአሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 333318 ሕዳር 1ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ በጉዳዩ ላይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በማፅናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል።

2) ይህ የሰበር ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።

## ትዕዛዝ

1) ይህ ችሎት ጥር 25ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል።

2) መዝገቡ እልባት ያገኘ በመሆኑ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ.201365

ቀን፡-27/01/2013ዓ/ም

**ዳኞች፡ እትመት አሰፋ**

**ፀሐይ መንክር**

**ኑረዲን ከድር**

**መላኩ ካሳዬ**

**እስቲበል አንዱዓለም**

**አመልካች፡** **የአማራ ክልል ገቢዎች ቢሮ ዐቃቤ ህግ ዓ/ህግ- አቶ ማዘንጊያ ደምሴ**

**ተጠሪ፡** **ደሳለኝ ቸኮል**

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ ያለደረሰኝ እና የጭያሽ መመዝገቢያ ማሽን ግብይት መፈፀም ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው አመልካች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪን ጨምሮ በሁለት ሰዎች ላይ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ በቀረበው ክስ ላይ ተጠሪ ሁለተኛ ተከሳሽ ነበር፡፡ የቀረበው ክስ ጭብጥም ተከሳሾቹ የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120(1) እና 128 ድንጋጌን በመተላለፍ የስር 1ኛ ተከሳሽ የድርጅቱ ባለቤት ሆኖ የአሁን ተጠሪ ደግሞ በድርጅቱ ውስጥ የመስተንግዶ ሰራተኛ ሆኖ እየሰራ እያለ ታህሳስ 16/2012 ዓ.ም ከቀኑ 6፡50 ሰዓት አካባቢ ሁለቱ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች እያንዳንዳቸው ለተጠቀሙት ሁለት ሁለት ቢራ ደረሰኝ ሳይሰጣቸው የአሁን ተጠሪ ሂሳብ የተቀበላቸው በመሆኑ ያለደረሰኝ ግብይት ፈፅመዋል፣ በዚህም ውስጥም የአሁን ተጠሪ አስተናጋጅ ሆኖ ዳረሰኝ ሳይሰጥ ሂሳብ በመቀበል ወንጀሉ እንዲፈፀም የስር 1ኛ ተከሳሽን ረድቷል የሚል ነው፡፡

ተጠሪ እና የስር 1ኛ ተከሳሽ ቀርበው ድርጊቱን እና ጥፋተኝነቱን ክደው ተከራክረዋል፡፡ በዚሁ ምክንያት ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የዐቃቤ ህግን ምስክሮችን አስቀርቦ ከሰማ በኋላ የስር 1ኛ ተከሳሽ ክሱን እንዲከላከል ሲያዝ የአሁን ተጠሪን በተመለከተ በድርጅቱ ውስጥ በአስተናጋጅነት

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

መስራቱ እንጂ በቀረበው ክስ አግባብ 1ኛ ተከሳሽ ስለመርዳቱ አልተረጋገጠም በሚል ክሱን መከላከል ሳያስፈልገው በነፃ አሰናብቷል፡፡ በዚሁ ብይን ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(1) መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ጥር 07/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ብይንና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ የክርክር መነሻ የሆነው ደረሰኝ እና የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ሳይጠቀሙ ግብይት በመፈፀም ሂደት ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው ስለመሆኑ በተገለፀበት በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል በነጻ እንዲሰናበት የተወሰነበት አግባብነት ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመደረጉ ተጠሪ የፅሁፍ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡ ሆኖም ተጠሪ በተደረገለት የጋዜጣ ጥሪ ቀርቦ መልስ ያልሰጠ በመሆኑ ክርክሩ በሌለበት እንዲታይ ታዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የአመልክችን የሰበር ቅሬታ ለአቤቱታው መሰረት ከሆነው የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይዘት ጋር በማገናዘብ በሰር ፍርድ ቤቶች ብያኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ መርምሯል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ካቀረበው የክስ ይዘት መረዳት እንደሚቻለው የአሁን ተጠሪ የወንጀል ተሳትፎ ተብሎ የተጠቀሰው በወንጀሉ አፈጻፀም ሂደት የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረውን ረድቷል በሚል ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱ ተካፋይ ስለመሆኑ እና በዚያው ውስጥም የነበረው የተሳትፎ መጠን አግባብነት ባለው ማስረጃ መረጋገጥ ያለበት የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ የአመልካችን ማስረጃ የመረመረው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በወንጀል ህግ ቁጥር 37 አግባብ የስር 1ኛ ተከሳሽን በወንጀል ድርጊቱ የረዳው ስለመሆኑ በዐቃቤ ህግ ማስረጃ አልተረጋገጠም ብሏል፡፡ እንግዲህ የቀረበው ማስረጃ የክሱ ፍሬ ነገር አረጋግጧል ወይስ አላረጋገጠም የሚለው የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10 መሰረት ለዚህ ሰበር ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔው ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ካለ ማረም እንጂ ማስረጃን የመመርመር እና የመመዘን አይደለም፡፡ ከዚህ አኳያ ማስረጃን የመመርማር እና የመመዘን የዳኝነት ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ በሰበር ሰሚ ችሎት ሊነቀፍ የሚችለው ፍርድ ቤቶቹ ማስረጃን ከመመዘን አኳያ የተላለፉት መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ ሲኖር አልያም የተወሰደው አቋም በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያላደረገ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ማስረጃ በድጋሚ የሚመረመርበትም ሆነ የሚመዘንበት ህጋዊ መሰረት የለም፡፡

ከዚህ አንፃር አመልካች ያቀረበው የሰበር ቅሬታም ሆነ በአጣሪ ችሎቱ የተያዘው ማስቀረቢያ ነጥብ በስር ፍርድ ቤት ቀርበው የተሰሙት የአመልካች ማስረጃዎች በድጋሚ እንዲመረመሩ እና እንዲመዘኑ የሚጋብዝ እንጂ በማስረጃ ምዘና ሂደት የተጣሰ መርህ መኖሩን የሚያሳይ አይደለም፡፡ ይህ ከሌላ ደግሞ የአመልካች ማስረጃ በዚህ ችሎት በድጋሚ የሚመዘንበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች ብይን እና ትዕዛዝ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ምክንያት ባለመኖሩ የአመልካች የሰበር ቅሬታ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/02-23435 ላይ ታህሳስ 01/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ሀ)) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ሄ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-201746

ቀን፡-28/03/2014ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ደሴ ከተማ ሆጤ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት -ዓ/ህግ ማዘንጊያ ደምሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አዋድ ኢብራሂም - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 12 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 03-29655 ሕዳር 06 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት የቀረበን የመቃወም አቤቱታን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች የመቃወም አመልካች፤ የአሁን ተጠሪ እና በዚህ የሰበር ክርክር የሌለ ሆጤ ክፍለከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት ደግሞ የመቃወም ተጠሪዎች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው የመቃወም አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡- የአከራካሪው የንግድ እና መኖሪያ ቤት ካርታ በቅይጥ የተሰራ ቢሆንም ሽያጭ በተከናወነበት ጊዜ የንግድ እንቅስቃሴው ያልቆመ እና የንግድ ፈቃዱም ያልተመለሰ በመሆኑ የሽያጭ ውሉን መሠረት በማድረግ በመኖሪያ ቤት ስም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንዲዛወርላቸው የተሰጠው ውሳኔ የመንግስትን መብት እና ጥቅም የሚጎዳ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል የሚል ነው።

የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው በብይን ውድቅ ተደርጓል፤ በፍሬነገሩ ላይ ደግሞ አመልካች ክርክሩን ከዚህ በፊት አያውቅም ተብሎ አይገመትም፤ አመልካች አስቀድሞ ሲደረግ የነበረውን ክርክር እያወቀ ውጤቱን ጠብቆ ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፤ የሆጤ ክፍለከተማ አስተዳደር ኮንስትራክሽን ልማት ጽ/ቤት የመኖሪያ ቤት ግብር እንዲከፈልበት አሳውቋል፤ የካፒታል ዕድገት ታክስ ተጠሪን አይመለከትም፤ ለስመ ንብረት ዝውውር ሲባል በንግድ ድርጅት ግብር ልንከፍል አይገባም፤ የስመ ንብረት ዝውውር በጠየቅንበት ወቅት ንብረቱ ሲሰጥ የነበረው አገልግሎት ቅይጥ አገልግሎት ነው፤ የስም ዝውውርን በሚመለከት ተፈጻሚነት ያለው ሕግ መመሪያ ቁጥር 4/2006 ብቻ ነው፤ ስለሆነም አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ምስክሮችን ከሰማ በኋላ አመልካች አስቀድሞ የነበረውን ክርክር ያውቅ ነበር የሚያስብል የሚያስብል ማስረጃ አልቀረበም፤ የሽያጭ ውሉ የተደረገው ለመኖሪያ እና ለንግድ ቅይጥ አገልግሎት በሚል ነው፤ በቅይጥ አገልግሎት ግብር የተገበረ ቢሆንም በመመሪያ ቁጥር 4/2006 አንቀጽ 14/6 ላይ ለቅይጥ አገልግሎት የተሰጠ ቦታ ይዞታው እየሰጠ ባለው አገልግሎት መሠረት ተገቢውን የስመ ንብረት ዝውውር ክፍያ እንደሚፈጸም የሚደነግግ በመሆኑ በዚሁ አግባብ የስመ ንብረት ዝውውር ክፍያው ሊፈጸም ይገባል በማለት አስቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ ሰርዟል።

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ ክርክር ሲደረግበት ያውቅ እንደነበር መገንዘብ ተችሏል፤ የስር ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል የቀረበውን መቃወምያ ተቀብሎ እንደ አዲስ አከራክሮ እና ማስረጃዎች ሰምቶ ውሳኔ መስጠት ሲገባው የቀደመ ውሳኔውን በቀጥታ መሻሩ አግባብ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሯል።

አመልካች በበኩሉ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቧል። አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች የመቃወም አቤቱታ ያቀረበው የሽያጭ ውል የተፈጸመበት ቤት የእኔ ነው በሚል ሳይሆን አመልካችን ሳያሳውቁ በመኖሪያ አገልግሎት ስመ ንብረቱ ቢዛወር በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚከፈለው ክፍያ ስለሚቀንስ የመንግስት ጥቅም ይነካል በሚል ነው፤ አመልካች ስመንብረት እንዲዛወር በተጠየቀው ዳኝነት ላይ በቀጥታ ስለማይመለከተው ከጅምሩ የክርክሩ ተካፋይ ሊሆን የሚገባው አልነበረም፤ ሆኖም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ስመ ንብረቱ በመኖሪያነት ተዛውሮ ሽያጩ ሊፈጸም ይገባል በማለት የወሰነ በመሆኑ በውጤት ደረጃ ተቀብለነዋል በማለት ወስኗል።

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ጥር 12 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው የስመ ንብረት ዝውውር ውሳኔ መብት እና ጥቅማችንን የሚነካ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት ውሳኔውን ለሰጠው ለስር ፍርድ ቤት አቅርበን ማስወሰናችን ተገቢ ሆኖ ሳለ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔውን መሻራቸው አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት ጣልቃ ለመግባት ያቀረበውን አቤቱታ ያልተቀበለበትን አግባብነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 37502 ከሰጠው የሕግ ትርጉም እና ከክልሉ አዋጅ ቁጥር 168/2002 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪዎች የካቲት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች አስቀድሞ ሲካሄድ የነበረውን ክርክር ያውቅ ነበር፤ አመልካች ይህን እያወቀ ከውሳኔ በኋላ ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በስር ይግባኝ ሰሚ ፍርደ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው በአሁን ተጠሪ እና በስር ተከሳሽ መካከል የተደረገው ክርክር የስም ሐብት ዝውውርን የሚመለከት መሆኑን፤ አመልካች በበኩሉ በተጠሪ እና በስር ተከሳሹ መካከል በተደረገው ክርክር የሽያጭ ውሉን መሠረት በማድረግ የአከራካሪው ቤት ስመ ሐብት በመኖሪያ ቤት ስም እንዲተላለፍ በማለት የተሰጠው ውሳኔ የመንግስትን ገቢ የሚጎዳ መሆኑን በመግለጽ የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን የተሰጠው ውሳኔ እንዲሰረዝለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ያቀረበ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ችሎት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ከመነሻውም ቢሆን አመልካች የቤቱ ስመ ሐብት በመኖሪያ ቤት ሊተላለፍ አይገባም በማለት የሚያቀርበው ጥያቄ ሊስተናገድ የሚገባው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት በሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ መነሻነት ነው? ወይስ ራሱን ችሎ በሚቀርብ ክስ ነው? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለዉ በክርክሩ ዉስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባዉ ወይም በክርክሩ ዉስጥ ለመግባት የሚችልና ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠዉ ፍርድ መብቱን የሚነካበት ሰዉ ነዉ፡፡ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው መቃወሚያ የሚያቀርበው ሰው በሙግቱ በቀጥታ ጥቅም ያለው እውነተኛ ወገን ሊሆን እንደሚገባ፤ በተሰጠው ፍርድ በእርግጥም

ጥቅሙ የተነካበት እና በሌላ አግባብ መብቱን ለማስከበር የማይችል ሰው ስለመሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ የሚገባ መሆኑን ነው።

በያዝነው ጉዳይ በአሁን ተጠሪ እና የስር ተከሳሽ በነበረው የሆጤ ክፍለከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት መካከል በተደረገው ክርክር የአከራካሪው ቤት ስም ሐብት በመኖሪያ ቤት እንዲተላለፍ በሚል ውሳኔ ተሰጥቶበታል። አመልካች ይህ ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት አቤቱታ ያቀረበው ደግሞ ተካፋይ ባልሆንኩበት ክርክር የተሰጠው ውሳኔ የመንግስትን ገቢ ይጎዳል በሚል ነው። ስለሆነም አመልካች በሕጉ በተቀመጠው ሥርዓት መሠረት ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት ላይ አዲስ ክስ በማቅረብ መብቱን ከሚያስከብር በቀር የአከራካሪው ቤት ስመ ሐብት በመኖሪያ ቤት እንዲተላለፍ በማለት የተሰጠው ውሳኔ መብቴን ይጎዳል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት ያቀረበው መቃወሚያ ተገቢነት የለውም። በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

## ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 03-29655 ሕዳር 06 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል።
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።
3. ጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

??/? /??? 201771
?? 28/3/2014 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - 1. ወ/ሮ ማስተዋል ዓለሙ 2. ህጻን ታጫውት አለማየሁ 3. ህጻን እያለ አለማየሁ - የቀረበ የለም

ተጠሪ - አቶ ደሳለው ታደሰ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ጥር 21 ቀን 2013 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 92061 ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 52061 ነሐሴ 2 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 0174616 ግንቦት 6 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ቅሬታቸውን በማቅረባቸው ነው፡፡ ቅሬታቸውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካቾች የሚቃወሙባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልን ይገባል የሚሉትን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤት መሬቱ የኔ የ1ኛ አመልካችና የባለቤቴ ሲሆን 2ኛ እና 3ኛ ከሳሾች የአባታቸው ወራሾች ናቸው፡፡ የአሁን ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች ጋር የተስማማነው 12 ክፍል ቤት ሰርቶ ሊያካፍለኝ ሲሆን 12 ክፍል ቤት ሰርቶ ለግሉ ይዞታል፡፡ 3

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ክፍል ቤት ደግሞ በ2ኛ እና 3ኛ ከሳሾች የመሬት ድርሻ ላይ የሰራ በመሆኑ ሊያነሳላቸው የሚገባ ሲሆን የወረዳ ፍ/ቤት አጣርቶ የሰጠውን ውሳኔ የከፍተኛውና የሰበር ሰሚው ችሎት መሻራቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑ ይታረምልን የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከአዲስ ዓለም ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት ክስ 1ኛ ከሳሽና ተከሳሽ በ24/4/2008 ዓ/ም በቃል ባደረግነው ስምምነት በገጠር መሬት ላይ ተከሳሽ 12 ክፍል ቤት ሰርቶ ሊያከፍለኝ ተዋውለን በውሉ መሰረት 12 ክፍል ቤት ሰርቶ ያላካፈለኝ በመሆኑ፣ 2ኛ እና 3ኛ ከሳሾች በውርስ ባገኙት መሬት ላይ ካለፈቃዳቸው ሶስት ክፍል ቤት የሰራበት በመሆኑ እንዲለቅላቸው ለ1ኛ ከሳሽ ደግሞ 12 ክፍል ቤት እንዲያካፍለኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ ተከሳሽም የአሁን ተጠሪ 1ኛ ከሳሽና እኔ ተከሳሽ በተስማማነው መሰረት 3 ክፍል ቤት ሰርቼ ሰጥቻታለሁ፡፡ እኔ ደግሞ 12 ክፍል ቤት ሰርቻለሁ፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ከሳሾች መሬቱ የነሱ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ ቤቱን ስሰራ ያልተቃወሙኝ በመሆኑ ክሳቸው ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የአዲስ ዓለም ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 015883 መጋቢት 17 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ በተዋዋዮች መሀከል የሚደረግ ውል በመሀላቸው እንደ ህግ የሚቆጠር ነው፡፡ አንድ ውል በተለየ ፎርም እንዲደረግ ካልተደነገገ በቀር በፈለጉት መንገድ ሊዋዋሉ ይችላሉ፡፡ 1ኛ ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር ያደረጉት ስምምነት 12 ክፍል ቤት በተከሳሽ ተሰርቶ ሊካፈሉት ሲሆን የተሰሙት ምስክሮችም በማረጋገጣቸው ተከሳሽ 12 ክፍል ቤቱን ግማሹን ለ1ኛ ከሳሽ ያካፍላት፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ከሳሾች የአባታቸው ወራሾች ቢሆኑም፣ ይዞታው ተመዝግቦ ያለው በ1ኛ ከሳሽ ስም በመሆኑ፣ እና ተከሳሽ የ1ኛ ከሳሽ መሬት ነው በሚል አምኖ የተስማማ በመሆኑ፣ 2ኛ እና 3ኛ ከሳሾች የሚከራከሩትም በ1ኛ ከሳሽ በኩል ሲሆን፣ ቤቱ ውስጥም ለ8 ወራት የኖሩበት በመሆኑ 3 ክፍል ቤቱ በሚገባ ተጠናቆ ተከሳሽ ለከሳሾች ያስረክብ ሲል ወስኗል፡፡ ተከሳሽ ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 0174616 ግንቦት 6 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ክርክሩ የሚያስረዳው ስምምነቱ ተከሳሽ ለ1ኛ ከሳሽ 3 ክፍል ቤት ሰርቶላት ለራሱ ደግሞ 12 ክፍል ቤት ለመስራት ሲሆን ጉዳዩን በእርቅ ያዩት ሽማግሌዎችም ከሳሽ ያቀረበችው ቅሬታ ለራሱ በደንብ ሰርቶ ለኛ ያላለቀ ቤት ነው የሰጠን የሚል መሆኑን የመሰከሩ በመሆኑ 12 ክፍል ቤት የተሰራው ለተከሳሽ ነው ሲል የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡ ከሳሾች ለአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው በመ/ቁጥር 52061 ነሐሴ 2 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኛቸውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከሳሾች ለአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው አከራክሮ በመ/ቁጥር 92061 ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትእዛዝና የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካቾችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አከራካሪው ይዞታ የ2ኛ እና 3ኛ የሰበር አመልካቾች አባት ሟምር መሆኑ ከመረጋገጡ አንጻር 1ኛ የሰበር አመልካች አድርገዋለች ለተባለው ውል መነሻነት 2ኛ እና 3ኛ የአሁን አመልካቾች መብት ጨምሮ የውሉ አካል ነበር ማለት ይቻላል ወይ? የምለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ ተጠሪ መልስ ባለማቅረቡ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት ክስ የአሁን 1ኛ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገችው የቃል ስምምነት በአሁን አመልካች የገጠር መሬት ላይ

ተጠሪ 12 ክፍል ቤት ሰርቶ እኩል አንዲያካፍላት የተስማሙና የአሁን ተጠሪ 12 ክፍል ቤት ሰርቶ ያላካፈላት መሆኑን እንዲሁም 3 ክፍል ቤት የሰራው በአሁን 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የመሬት ይዞታ ላይ በመሆኑ ያንሳልን የሚል ሲሆን የአሁን ተጠሪም በሰጠው መልስ ለአሁን 1ኛ አመልካች 3 ክፍል ቤት ሰርቶ ያስረከባትና ለራሱ ደግሞ 12 ክፍል ቤት የሰራ መሆኑን፣ በውላቸውም መሰረት የተፈጸመ መሆኑን ተከራክሯል፡፡ በዚሁ መሰረት በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ይዞታው የአሁን 1ኛ አመልካችና የባለቤቷ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች አባት የሚች አቶ አለማየሁ የጋራ ንብረት አንደሆነ፣ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾችም የአባታቸው የሚች አቶ አለማየሁ ወራሽ መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን ቤት የተሰራበት የመሬት ይዞታ የአሁን 1ኛ አመልካችና የአሁን 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የጋራ ይዞታ መሆኑም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በግራ ቀኙ ከቀረበው ክርክር የምንረዳው ቤት ተሰርቶ ለመከፋፈል የተስማሙት የአሁን 1ኛ አመልካችና የአሁን ተጠሪ ብቻ ስለመሆናቸው ግራ ቀኙ የሚስማሙበት ጉዳይ ሲሆን የቀረበው ክስና መልስ ይህንኑ የሚያስረዳ ነው፡፡ በመሆኑም የግራ ቀኙ ስምምነት የአሁን 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾችን የመሬት ይዞታ ድርሻ የሚመለከት አይደለም፡፡ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾችን መብት የሚነካ የቤት ግንባታ ስምምነትም ከፍቃዳቸው ውጪ ስለሚሆን ተፈጻሚነት የሚኖረው አይደለም፡፡ በገጠር መሬት ላይ የሚደረጉ ውሎች ህጋዊነት በተመለከተ በአሁን 1ኛ አመልካችና ተጠሪ መካከል በገጠር መሬት ላይ ቤት ሰርቶ ለመካፈል የተደረገው ስምምነት ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ አንጻር ህጋዊነት ያለው አይሆንም፡፡ ይሁንና የአሁን 1ኛ አመልካች ውሉን መሰረት አድርጋ ላቀረበችው ክስ የአዲስ ዓለም ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች የይግባኝ ቅሬታ ያላቀረበችበትና ይግባኝ ባልተባለበት ጉዳይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አንስቶ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የስነ ሥረዓት ህጉ የማይፈቅድ ሆኖ በመገኘቱ ሊታለፍ ችሏል፡፡ በአሁን 1ኛ አመልካችና በአሁን ተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ግንባታ ስምምነትን በተመለከተ የአሁን 1ኛ አመልካች ክርክር ተጠሪ 12 ክፍል ቤት ገንብቶ ግማሹን ሊያካፍለኝ በቃል ተስማምተናል የሚል ሲሆን የአሁን ተጠሪ ደግሞ ስምምነቱ ከአሁን 1ኛ አመልካች ጋር ብቻ የተደረገ መሆኑን ተቀብሎ ለአመልካች 3 ክፍል ቤት ሰርቶላት ለራሱ 12 ክፍል ቤት ለመስራት የተስማማ መሆኑን ተከራክሯል፡፡ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ማጣራት ደግሞ 12 ክፍል ቤት በአንድ ቦታ ሶስት ክፍል ቤት በአንድ ቦታ የተሰራ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን የአሁን 1ኛ አመልካች ግራ ቀኙ ያደረጉት የቃል ስምምነት 12 ክፍል ቤት ተሰርቶ ለመካፈል የተስማሙ መሆኑን ያረጋገጡ ሲሆን የአሁን ተጠሪ ምስክሮች ደግሞ ጉዳዩን በሽምግልና ያዩትና በሽምግልና ጊዜ የሰሙትን የሰጡት ቃል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የአዲስ ዓለም ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤት የቀረበውን ክርክር በማስረጃ አጣርቶ አሁን ተጠሪ በአሁን 1ኛ አመልካች የመሬት ይዞታ ላይ 12 ክፍል ቤት ሰርቶ ለመካፈል የተስማሙ መሆኑን የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ ሆኖ እያለ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ካለ በቂ ምክንያት የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔን ማሻሻሉ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 38844 ላይ በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በአግባቡ ሳይመረምሩ እና ለውሳኔያቸው በቂ ምክንያት ሳይሰጡ መሻር የማይችሉ ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ በመሆኑም የአዲስ ዓለም ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤት በማስረጃ አጣርቶ በህጉ መሰረት የሰጠውን ውሳኔ ካለበቂ ምክንያት የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በማሻሻል የሰጠው ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት ሳያርሙት ማለፋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል፡፡

## ውሳኔ

1. የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 92061 ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 52061 ነሐሴ 2 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የምዕራብ ጎጃም ዞን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር -174616 ግንቦት 6 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡ የአዲስ ዓለም ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 015883 መጋቢት 17 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

3. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-201929

ቀን፡-30/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡አቶ ሆርዶፋ ዬቲ

ተጠሪዎች ፡1ኛ/ ወ/ሮ ፀሐይ ሽፈራው

2ኛ/ አዋሽ ባንክ አ.ማ

3ኛ/ ዳሸን ባንክ አ.ማ

ይህ መዝገብ ከመ/ቁ/ 201929 ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀም ክስ መነሻ ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን 1ኛ ተጠሪ የአፈጻጸም ከሳሽ፤የአሁኑ አመልካች በአፈጻጸም ተከሳሽ፤የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ከተወሰነ በኋላ 200 ሄክታር የቡና ልማት የኢንቨስትመንት ይዞታ የጋራ ንብረት ነዉ ተብሎ እኩል እንዲካፈሉ ተወስኖ የፌዴራል ፍ/ቤቶች የአፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ንብረቱ ያለበት የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በውክልና ውሳኔውን እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ መስጠቱን ተከትሎ የአፈፃፀም መዝገብ ቁ/42899 ተከፍቶ በሂደት ላይ እያለ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በየበኩላቸዉ ባልና ሚስቱ ከባንኩ ተበድረዉ ያልከፈሉት እዳ መኖሩን በተለያየ መዝገብ ያሰጡትን ፍርድ በማቅረብ ንብረቱ በባልና ሚስት መካከል ክፍፍል ከመደረጉ በፊት እዳዉ እንዲከፈላቸዉ አቤቱታ በማቅረብ የክርክሩ ተካፋይ መሆናቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸዉ በሰጡት መልስ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ከዚህ ቀደም

የአፈጻጸም ክስ አቅርቦ የ2010ዓ.ም እና 2011 ዓ.ም የምርት ዘመን የቡናዉን ፍሬ አስለቅሞ እዳዉን እንዲሰበስብ ትእዛዝ የተሰጠለት መሆኑን ጠቅሰዉ በባልና ሚስት መካከል በሚደረግዉ የአፈጻጸም ክርክር ላይ አቤቱታ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ እና ከሚመለከተዉ አካል አጣርቶ ለባንኩ እንደፍርዱ አለመፈጸሙን እና ንብረቱም ከፍርድ ባለእዳ እጅ አለመዉጣቱን አረጋግጦ ክርክራቸዉን ዉድቅ በማድረግ ንብረቱ በሃራጅ እንዲሸጥ እና ለባልና ሚስቱ ከመከፋፈሉ በፊት የባንኩቹ እዳ እንዲከፈል በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 224389 ላይ ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ/337 መሰረት ሰርዟል፡፡1ኛ ተጠሪ በበኩሏ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/224547 ላይ ያቀረበችዉ ይግባኝ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት በቀን 17/05/2013ዓ.ም ጽፎ ያቀረበዉ አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሲታይ፤2ኛ ተጠሪ(አዋሽ ባንክ) በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.428(2) መሰረት የሁለት ዓመት የቡና ምርት በብር 14,150,360.00 ግምት እንዲረከብ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.214298 በቀን 30/09/2010ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀርቦ ጸድቋል፤ነገር ግን ባንኩ ይህንን ትዕዛዝ አልቀበልም በማለት ለሁለት አመት የቡና ምርት እንድበሰብስ በማድረግ ያደረሰውን ጉዳት ወደ ጎን በመተው በዚህ አፈፃፀም መዝገብ እንደገና ጣልቃ ገብቶ ከኢንቨስትመነት መብታችን ጋር እንዲከፈል ያቀረበው አቤቱታ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.418(1) መሰረት ተቀብሎ ባለመብት ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ እንዲታረም፤ግምቱን በተመለከተ የቀረበው ግምት ፍትሃዊ እንዳልሆነ ግልፅ ሆኖ እያለ ፍ/ቤቱ እንደ ትክክለኛ ውሳኔ በመውሰድ የሰጠው ብይን ስህተት ነው፡፡ለኢንቨስትመንት ከወሰድኩት መሬት ስፋት 200 ሄክታር ውስጥ የቡና ተክል 78 ሄክታር ብቻ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የስር ፍ/ቤት 122 ሄክታር ባዶ መሬት ጨምሮ እንዲሸጥ መወሰኑ ሰርቼ የመኖር መብቴን የሚነካ በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እዳ መጠን በተመለከተ ተሸጦ ገቢ የተደረገውን እና ቀሪውን ሂሳቡ በባለሙያ እና በማስረጃ እንዲጣራ የሰጠውን ትእዛዝ የስር ፍ/ቤት ሳያጣራ ማለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የተሰጠው ብይን እንዲሻር በማለት አመልክተዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በበኩሏ ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ አቤቱታ ያቀረበች ሲሆን ዝርዝር ይዘቱን ከሰበር መዝገብ ቁ.201929 የሚቻል ሆኖ ባጭሩ ሲታይ፤2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጉዳያቸው በሌላ መዝገብ እልባት አግኝቶ ተፈጽሞ እያለ በድጋሚ በባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል መዝገብ ላይ ጣልቃ ገብቶ በድጋሚ ንብረቱ በሀራጅ እንዲሸጥ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ በሚል የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲታረም ጠይቃለች፡፡

የአመልካቹ አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ቀደም ሲል ከአመልካች ጋር በነበረው የአፈጻጸም ክርክር በጨረታ ገዥ ስላጣ ምርቱን እንዲረከብ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.214298 በ30/09/2010 ዓ.ም ውሳኔ ተሰጥቶ በፌዴራል ሰበር ችሎት የፀና ሲሆን በባልና ሚስት ክርክር ላይ ባንኩ ጣልቃ እንዲገባ አድርጎ በጨረታ ተሸጦ ቅድሚያ ለባንኩ ይከፈል በማለት የሥር ፍርድ ቤት የወሰነበት አግባብነት ለማጣራት በሚል እንዲሁም የ1ኛ ተጠሪ አቤቱታም

ተመሳሳይና አንድ በመሆኑ ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምረው እንዲታይ በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የተጠሪዎች መልስ ይዘት በቅደም ተከተል ስንመለከት 1ኛ ተጠሪ የአመልካች አቤቱታ በሚያጠናክር መልኩ መልስ አቅርባለች፡፡2ኛ ተጠሪ ባቀረበው መልስ አንድ ፍርድ በውሳኔው መሰረት ተፈጽሟል ሊባል የሚቻለው ፍርዱ ያረፈበት ገንዘብ ሲከፈል ወይም የተቻቻለ ነገር ያለ ሲሆን ነው፡፡ነገር ግን አመልካች ክፍያ የፈፀመበትን ደረሰኝ ወይም ለሽያጭ የተዘጋጀ ምርት በሌለበት የቡና እርሻን ለመረከብ አልገደድም እንጂ መረከበን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይቀርብ እና የ2010 ምርት ይረከብ በተባለ ጊዜም በአካል የሌለና የ2011 ዓ.ም በይግባኝ ላይ ቆይተን ጥር 15 ቀን 2011 ዓ.ም የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ አመልካች ምርቱን ሰብስቦ የጨረሰ ሲሆን ሊፈፀም ወይም ተግባራዊ የማይሆን ውሳኔ መሰረት በማድረግ አመልካች የ2ኛ ተጠሪ እዳ ተከፍሏል በማለት ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም፤የ2ኛ ተጠሪ እዳ በውሳኔው መሰረት ሳይፈፀም አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የባልና ሚስት ንብረት ነው በማለት የ2ኛ ተጠሪ መያዣ ንብረት ለመከፋፈል በአፈፃፀም መዝገብ ክርክር እያደረጉ ስለሆነ 2ኛ ተጠሪ ቀዳሚ መብት ያለው በመሆኑ ጣልቃ ገብ ሆኖ አቤቱታ ማቅረቡ በአግባቡ ነው፤የጅማ ዞን ከፍተኛ የ2010 ዓ.ም እና የ2011 ዓ.ም ምርት ተጠሪ መረከብ አለመረከቡን ለማረጋገጥ ፍ/ቤቱ በመ/ቁ 42899 ላይ መስከረም 19 ቀን 2013 ዓ.ም ለሚመለከተው አካል በሰጠው ትእዛዝ መሰረት በመስከረም 30 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ አከራካሪው የቡና እርሻ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በአመልካች እጅ የሚገኝ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ርክክብ ያልተደረገና ተረከብ የተባለ የቡና ምርት የሌለ በመሆኑ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ከመከፋፈላቸዉ በፊት የ2ኛ ተጠሪ እዳ ይከፈል ማለቱ ትክክል በመሆኑ ቅሬታው ተቀባይነት የለውም፡፡ግምቱን በተመለከተ ምርቱ ከማሳ ተሰብስቦ ለገበያ እስኪቀርብ ድረስ ያሉት ወጪዎች እና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ብክነቶች ታሳቢ ያደረገ ሲሆን የባለሙያ ግምት የሚነቀፍ አይደለም፤ስለዚህ የቀረበው ቅሬታ ውድቅ ሆኖ ወጪና ኪሳራ የማቅረብ መብት እንዲጠበቅልን በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

3ኛ ተጠሪ በበኩሉ በአመልካች ላይ ያለው ብድር እዳ ብር 1,521,349.81 እንዲከፍል የተሰጠዉ ውሳኔ እልባት ሳያገኝ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ክፍፍል ለማድረግ የአፈፃፀም መዝገብ ስለከፈቱ የቡና ማሳ ሳይሸጥ በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ችለናል፡፡አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ይህንን ገንዘብ ሳይከፍሉ የቡናውን እርሻ ሊካፈሉ የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡ስለዚህ የስር ፍ/ቤት የባልና ሚስት ንብረት ሳይከፋፈል ንብረቱ በሀራጅ ተሸጦ ፍርድ ያረፈበት እዳ እንዲከፈለን የሰጠው ብይን የሚነቀፍበት የህግ ምክንያት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡የ1ኛ ተጠሪን አቤቱታ በተመለከተም ከላይ ከተገለጸዉ ጋር ተመሳሳይ የሆነ መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ለአፈጻጸም ክርክር መነሻ የሆነዉ ፍርድ በአንድ በኩል የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል የሚመለከት ሲሆን በሌላ በኩል የአበዳሪ ባንኮችን ማለትም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እዳ በሚመለከት የተሰጠ ዉሳኔ ነዉ፡፡ፍርዱ በተለያየ ጊዜ በተለያዩ መዝገቦች የተሰጠ ሲሆን ለአሁኑ አቤቱታ ምክንያት የሆነዉ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነዉ የተባለዉ በጅማ ዞን የሚገኝ የቡና ኢንቨስትመንት ይዞታ

በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ ክፍፍል እንዲደረግ ባቀረቡት የአፈጻጸም መዝገብ ላይ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እዳ በቅድሚያ እንዲከፈል ትእዛዝ እንዲሰጥላቸዉ ያቀረቡትን አቤቱታ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ትእዛዝ መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ አሁንም አጥብቀዉ የሚከራከሩት ከተጠሪዎች እዳ አከፋፈል ጋር በተያያዘ በተለይም 2ኛ ተጠሪ አዋሽ ባንክ አስቀድሞ የቡና ፍሬ ለቅሞ እዳዉን እንዲሰበስብ የተሰጠዉን ትእዛዝ ሳያስፈጽም ቆይቶ አሁን እንደአዲስ አቤቱታ ማቅረቡና ፍርድ ቤቱም መቀበሉ ስህተት ነዉ በማለት ነዉ፡፡የዚህ ሰበር ችሎት ምለሽ የሚሻዉ አቢይ ነጥብ የስር ፍርድ ቤት የባለእዳዎቹን ክርክር ዉድቅ በማድረግ የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እዳ በቅድሚያ እንዲከፈል በሰጠዉ የአፈጻጸም ትእዛዝ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን የሚመለከት ነዉ፡፡

በመሠረቱ ፍርድ ማስፈጸም ማለት ፍርድ ቤቶች ወይም ሌላ የዳኝነት ስልጣን በህግ የተሰጣቸዉ አካላት የሚሰጡትን ፍርድ ወደ ተግባር እንዲለወጥ ወይም ዉጤት እንዲያገኝ የሚደረግበበት ሥርዓት ሲሆን ሂደቱ የሚመራዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ ሰባተኛ መጽሓፍ ስለፍርድ አፈጻጸም በስነስርዓት ህጉ አንቀጽ 371 እና ተከታዮቹ ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ፍርዱን የማስፈጽም ስልጣን ፍርዱን የሰጠዉ ፍርድ ቤት ወይም እንደ ፍርዱ እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ የተሰጠዉ ፍርድ ቤት ስለመሆኑም በህጉ አንቀጽ 371(1) ላይ የተደነገገ ሲሆን፣ ፍርዱን የሰጠዉ ወይም እንደ ፍርዱ እንዲያስፈጽም የታዘዘዉ ፍርድ ቤትም ፍርዱ ወደ ተግባር እንዲለወጥ ወይም በፍርዱ መሠረት ለማስፈጸም ባለበት ኃላፊነት መሠረት የተለያዩ እርምጃዎችን መዉሰድ እንደሚችል የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 386 እና 392 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ፍርድ እንዲያስፈጽም አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት አስቀድሞ እንዲመረምር የሚጠበቅበት መሰረታዊ ጉዳይ የሚፈጸም ፍርድ ስለመኖሩ፤የሚፈጸመዉ ነገር ምንነት፤ፍርዱን እንዲፈጽም የሚገደደዉ ሰዉ ማነዉ? የሚሉ እና መሰል ጉዳዮች ሲሆኑ ይህንኑ ፍርዱንና ተከራካሪ ወገኖችን በመመርምር ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡የአፈጻጸም ክርክሩን የሚመራዉ ፍርድ ቤት የፍርድ ባለእዳዉን ጠርቶ ከመረመረ በኋላ እንደፍርዱ የማይፈጸምበት ምክንያት ያለመኖሩን ሲያረጋግጥ ለአፈጻጸሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርዱ እንዲፈጸም ትእዛዝ እንደሚሰጥ ተደንግጓል፡፡የፍ/ብ/ስ/ስ/ህጉ አንቀጽ 386 እና 392/1/ይመለከታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ወደ አፈጻጸም ክርክር የገቡት በየበኩላቸዉ በአመልካች ላይ ክስ አቅርበዉ በፍርድ ያገኙትን መብት ለማስፈጸም ነዉ፡፡ለአፈጻጸም ክርክር መነሻ የሆነዉ አመልካቹ ከ2ኛ ተጠሪ ተበድሮ ያልከፈለዉ ቀሪ እዳ ለማስከፈል ባቀረበዉ ክስ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ተደርጎ በሰበር መ/ቁ/ 98218 ላይ መስከረም 30 ቀን 2009ዓ.ም የተሰጠ ፍርድ መሆኑን፤ 3ኛ ተጠሪን በተመለከተ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 175214 ላይ በጥቅምት 9 ቀን 2011ዓ.ም የተሰጠ ፍርድ እንዲሁም በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የንብረት የባልና ሚስት ክፍፍል ላይ በመ/ቁ/ 33998 ላይ የተሰጠ ፍርድ ስለመሆኑ ከክርክሩ መገንዘብ ተችሏል፡፡ይህ ፍርድ በስምምነት ወይም በሌላ አግባብ ስለመፈጸሙ በአመልካች በኩል የቀረበ መከራከሪያ የለም፡፡

የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ ዋነኛ መከራከሪያ ነጥብ 2ኛ ተጠሪ አስቀድሞ ባስከፈተዉ የአፈጻጸም መ/ቁ/31745 ላይ በተሰጠዉ ትእዛዝ መሰረት የፍርድ ባለእዳ ንብረት የሆነዉን ቡና ተረክቦ የ2010

እና 2011ዓ.ም ምርት ፍሬዉን በመልቀም ማስፈጸም ሲገባዉ አሁን 1ኛ ተጠሪ ባስከፈተችዉ የአፈጻጸም መዝገብ በጣልቃ ገብነት አቤቱታ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በወቅቱ በተሰጠዉ ትእዛዝ ባለመስማማት ለበላይ ፍርድ ቤቶች አቤቱታ መቅረቡንና በሂደቱም ጊዜዉ ማለፉን እንዲሁም ለመረከብ የማይገደድ ስለመሆኑና መረከቡንም የሚያስረዳ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ እንደፍርድ አለመፈጸሙን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ከክርክሩ እንደተገነዘብነዉ በአመልካች እና 2ኛ ተጠሪ መካከል በአፈጻጸም መ/ቁ/ 31745 መዝገብ ላይ ክርክር ተደርጎ ለፍርዱ ማስፈጸሚያ የለማዉ ቡና ላይ ፍርዱ እንዲፈጸም ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡ይሁንና በግምቱ ላይ አለመግባባት ተፈጥሮ ከአንድም ሁለት ጊዜ በተለያዩ ባለሙያዎች እንዲገመት ተደርጎ በመጨረሻም ሁለት ጊዜ ጨረታ ወጥቶ ገዥ ባለመገኘቱ 2ኛ ተጠሪ ተረክቦ የ2010 እና የ2011ዓ.ም ምርት የቡናዉን ፍሬ ለቅሞ በመሸጥ እዳዉን እንዲሰበስ የሚል ትእዛዝ የተሰጠ ቢሆንም ተጠሪ እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ሰበር ችሎት በመ/ቁ/167078 ላይ በቀን 15/05/2011 ዓ.ም የሥር ፍርድ ቤት ማጽናቱን መዝገቡ ያሣያል፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለዉ ጉዳዩ በክርክር ሂደት ላይ እያለ የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሳይፈጸም የምርት ዘመኑ ያለፈ መሆኑን ነዉ፡፡ ከዚህም ሌላ ለስር ፍርድ ቤት በቀን 29/01/3013ዓ.ም የቀረበዉ ሪፖርት ይህንኑ የሚያስረዳ ከመሆኑም በተጨማሪ አመልካች ለባንኩ በተለያዩ ጊዜያት የጻፋቸዉ አቤቱታዎች ይህንኑ የሚያረጋግጡ ናቸዉ፡፡በዚህ ረገድ አመልካቹ ለባንኩ አስተዳደር አካላት በቀን 12/03/2011ዓ.ም ባቀረበዉ አቤቱታ ባንኩ ቡናዉን እንድረከበዉና የቡናዉ ፍሬ ሳይበላሽ እንድለቅም መጠየቁ ንብረቱ ከእጁ አለመዉጣቱን የሚያሣይ ነዉ፡፡በተጨማሪም በመ/ቁ/31745 ላይ የተሰጠዉ ትእዛዝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር መ/ቁ/167078 ላይ በ15/05/2011ዓ.ም አያስቀርብም ተብሎ እስከተዘጋበት ጊዜ ድረስም ሆነ ከዚያም በኋላ 2ኛ ተጠሪ ንብረቱንም ሳይረከብ እንደፍርዱም ሳይፈጸም መዝገቡ በእንጥልጥል ላይ የቆየ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡2ኛ ተጠሪም አጥብቆ የሚከራከረዉ ንብረቱ ከመገመቱ ዉጪ በወቅቱ አለመረከቡን እንዲሁም ለመረከብ የሚያስገድደዉ ህግ አለመኖሩን ነዉ፡፡በዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባዉ ጉዳይ በሁለተኛ ጨረታ ገዥ ያልቀረበ እንደሆነ የፍርድ ባለገንዘቡ ንብረቱን እንዲረከብ ሊታዘዝ ይችላል የሚለዉ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 428/2/ ድንጋጌ በራሱ ሲታይ ፈቃጅ እንጂ አስገዳጅ አይደለም፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ ሰበር ችሎቱ በሰጠዉ ዉሳኔ እንዳመለካተዉ ንብረቱን ለመረከብ የባለገንዘቡ ፈቃደኛ መሆን አስፈላጊ እንደሆነ ያሣያል፡፡መ/ቁ 128776 ቅጽ 21 መመልከት ይቻላል፡፡ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ በአፈጻጸም መ/ቁ/ በመ/ቁ/31745 ላይ ንብረቱን መረከቡ ወይም እንደፍርዱ የተፈጸመለት መሆኑ ካልተረጋገጠ ወይም መብቱ በይርጋ ቀሪ ነዉ ካልተባለ በስተቀር በማናቸዉም ጊዜ አቤቱታ በማቅረብ የአፈጻጸም መዝገቡን በማንቀሳቀስ እንደፍርዱ እንደፈጸምለት መጠይቅ የሚከለክለዉ የህግ ምክንያት የለም፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ ባልና ሚስቱ ንብረታቸዉን ለመከፋፈል ባስከፈቱት የአፈጻጸም መዝገብ ላይ 2ኛ ተጠሪ ያቀረበዉ አቤቱታ የተስተናገደበት አግባብ ማየቱ ተገቢ ነዉ፡፡ከአንድ የፍርድ ባለእዳ ላይ መብት የሚጠይቁ ብዙ የፍርድ ባለመብቶች ሲቀርቡ ፍርድ ቤቱ በፍርዱ መሰረት ያለመፈጸሙን ካረጋገጠ በኋላ ተገቢዉን ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 403 ድንጋጌ ይዘት ያመላክታል፡፡ከዚህ አኳያ ተጠሪዎች በየፊናቸዉ የአፈጻጸም መዝገብ ያስከፈቱ ሲሆን ፍርዱ ማስፈጸምያ እንዲሆን የተባለዉ ንብረት አንድ የቡና ኢንቨስትመንት ይዞታ ነዉ፡፡ፍርድ ቤቱም በሌላ አግባብ ለባለመብቶቹ እንደፍርድ አለመፈጸሙን ካረጋገጠ በኋላ የፍርድ ባለመብቶች አቤቱታ ተቀብሎ አፈጻጸም ክርክሩን በአንድ መዝገብ መምራቱ ከስነስርዓት ዉጪ ነዉ የሚባልበት ምክንያት

የለም፡፡ምክንያቱም የፍርድ ባለእዳ ንብረት ሳይከፋፈል ወይም በሌላ ማናቸውም ሁኔታ ለሶስተኛ ወገን ከመተላለፉ በፊት የሁሉንም የፍርድ ባለገንዘብ እዳ መክፈል የሚያስችል ሁኔታ በስነስርዓት ህጉ የተዘረጋውን ስርዓት ተከትሎ ማስፈጸም የፍርድ ቤቱም ሃላፊነት ነዉና፡፡በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ በመብቱ ሳይሰራ የቀረዉ እና ምርቱ ሳይሰበሰብ ለብክንት የተዳረገዉ በባንኩ ችግር ነዉ በማለት አመልካቹ ያቀረበዉን ክርክር እና ህጋዊ ዉጤቱ ምንድነዉ የሚለዉን ስንመለከት በእርግጥም ፍሬዉ ሳይለቀም የቀረዉ በማን ጥፋት ነዉ የሚለዉን መመርመር ያስፈልጋል፡፡በዚህ ረገድ አመልካች የሚከራከረዉ በወቅቱ 2ኛ ተጠሪ እንዲረከብ የተሰጠዉ ትእዛዝ ሳይፈጸም የቀረዉ በተጠሪ ጥፋት ነዉ ቢልም 29/01/2013ዓ.ም የቀረበዉ ሪፖርት የሚያሣየዉ በአንድ በኩል የቡና ልማቱ ከአመልካች እጅ አለመዉጣቱን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ 2010 እና 2011ዓ.ም ምርት ወድቆ መጥፋቱን ያሣያል፡፡ሆኖም ግን 2ኛ ተጠሪ ተረክቦ ነበር የሚል ማረጋጫ ካለመቅረቡም በላይ ፍሬዉ ሳይለቀም የጠፋዉ በእርግጥም በ2ኛ ተጠሪ ጥፋት ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ተጨማሪ ማጣራት የሚፈልግ ጉዳይ ነዉ፡፡ይህ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካቹ የሚኖረዉ መብት ቀደም ሲል ለባንኩ ሃላፊዎች በጻፈዉ ማሳሰቢያ ላይ እንደገለጸዉ ለጉዳቱ ኪሳራ የመጠየቅ መብት ከሚሰጠዉ በስተቀር እንደፍርዱ ተፈጽሟል ወይም ባለእዳዉ ግዴታዉን ተወጥቷል ብሎ ለመደምደም የ2ኛ ተጠሪን አፈጻጸም ጥያቄ ላለመቀበል የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት ሆኖ አላገኘንም፡፡

3ኛ ተጠሪን በተመለከተ ከመዝገቡ እንደተረዳነዉ ለአፈጻጸሙ መሰረት የሆነዉ ፍርድ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/175214 ላይ በ09/02/2011ዓ.ም የተሰጠ ፍርድ ስለመሆኑ ግራቀኙን አላከራከረም፡፡በዚሁ ፍርድ መሰረት እንዲያስፈጽምለት ባንኩ በመ/ቁ/224096 ላይ የአፈጻጸም አቤቱታ ለፌዴራል ከፍተኛ ካቀረበ በኋላ የፍርድ ባለእዳ ንብረት ላይ እንዲፈጸም መጠየቁን ተከትሎ ንብረቱ የሚገኝበት የጅማ ዞን ፍርድ ቤት በዉክልና እንዲያስፈጽም ትእዛዝ በመሰጠቱ የመ/ቁ/51721 ተከፍቶ 1ኛ ተጠሪ ካስከፈተችዉ የአፈጻጸም መዝገብ ቁጥር 42899 ጋር ተጣምሮ ትእዛዝ የተሰጠበት መሆኑን የክርክሩ አመጣጥ ያሣያል፡፡በዚህ ላይ የአመልካች ቅሬታ ነጥብ በጨረታ መሸጥ የሚገባዉ ለኢንቨስትመንት የወሰደዉ 200 ሄክታር በሙሉ ሳይሆን የለማ ቡና ያለበት 78 ሄክታር ብቻ ተለይቶ መሆን አለበት በማለት ነዉ፡፡ሆኖም በዚህ ረገድ ለስር ፍርድ ቤት የቀረበ ክርክር ዉድቅ የተደረገዉ የኢንቨስትመንት ይዞታዉ በባልና ሚስቱ መካከል ከመከፋፈሉ በፊት የሌሎቹ ባለገንዘቦች እዳ እንዲከፈል በሚል ምክንያት በመሆኑና በኢንቨስትመንት የተያዘዉ ይዞታ ተከፋፍሎ ወይም ተሸንሽኖ የሚሸጥበት አግባብ ባለመኖሩ ክርክሩ ተቀባይነት አለማግኘቱ ስህተት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለል ለፍርድ ባለገንዘቦች እንደፍርዱ አለመፈጸሙን በማረጋገጥ የፍርድ ባለእዳ ንብረት በሃራጅ ተሸጦ ለፍርድ ባለገንዘቦች እንዲከፋፈል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ትእዛዝ ስለፍርድ አፈጻጸም በፍ/ብ/ስ/ስ/ ህጉ የተዘረጋዉን ስርዓት ይዘት ዓላማ ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

1ኛ/በዚህ ጉዳይ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 42899 ላይ የሰጠውን ትእዛዝ በማጽናት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 224389 እና በመ/ቁ/224547 ላይ የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ችሎት በዚህ መዝገብ ላይ በ28/05/2013ዓ.ም እና በመ/ቁ/201929 ላይ በ28/05/2013ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትእዛዝ ተስቷል፡፡ይጻፍ፡፡

3ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ግራቀኙ የየራሳቸዉን ወጪ ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ በአዳሪ ተሰርቶ በቀን 15/03/2014ዓ.ም በችሎት ተነቧል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሠ/መ/ቁጥር 201974

ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም

**ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ**

**ተሾመ ሽፈራዉ**

**ሀብታሙ እርቅይሁን**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ነጻነት ተገኝ**

**አመልካች ፡- አቶ ታደሰ ንጉሴ**

**ተጠሪ ፡- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ሻሸመኔ ቅርንጫፍ**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ከተጠሪ ጋር በ1989 ዓ/ም በፈፀሙት የስራ ውል በባላንስ ሠራተኛነት የስራ መደብ ላይ በወር 13,034.00 እየተከፈላቸዉ እንዲሰሩ ተቀጥረዉ ሲሰሩ መቆየታቸዉን፤ነገር ግን ያለምንም ምክንያት በቀን 07/09/2011ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የትራንዛክሽን ሥራ በመስራት በማሳለፍ ብድር በመዝጋት ባንኩ ማግኘት ያለበትን በማሳጣት ጥፋት ፈጽመሀል በማለት ሥራዬ ትራንዛክሽን ማሳለፍ ባለመሆኑ የሰራሁት ጥፋት ሳይኖር ከሕግ-ዉጭ ከሥራ አሰናብቶኛል፡፡ስለሆነም ወደ ሥራ እንዲመልሰኝ እንዲወሰንልኝ፡፡ይህ የሚታለፍ ከሆነ የስንብት ክፍያ ብር 95,582.67 ፤የ15 ቀን ደመወዝ ብር 6,517.00 ፤ክፍያ ለዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ ብር 39,102.00 ፤ካሳ የ6 ወር ደመወዝ ብር 78,204.00፤የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ብር 63,550.29፤ተጠሪ ባንክ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ከ20 ዓመት በላይ ላገለገለ ሰራተኛ 21 ካራት ወርቅ ስለሚሰጥ የዚህ ዋጋ የአንድ ካራት ዋጋ ብር 1,700.00 ብር 35,700.00፤የቦነስ ክፍያ የ2011 ዓ/ም ብር 39,102.00፤ከ2009-2011ዓ/ም ድረስ ያልተጠቀምኩበትን የሶስት ዓመት የአመት እረፍት ወደገንዘብ ቀይሮ እንዲከፍለኝ በአቃላይ ብር 370,991.29 (ሶስት መቶ ሰባ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሃያ ዘጠኝ ሳንቲም) እንዲከፈላቸዉ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠዉ መልስ አመልካች በተጠሪ መስሪያ ቤት በካሼርነት የስራ መደብ ተቀጥረዉ በሚሰሩበት ወቅት የባንኩ ደንበኛ የሆኑት መሀመድ ተካ ብድር ወስደው የነበረውን ገንዘብ መመለስ ስላልቻሉ በዋስትና የተያዘውን ንብረት ለመሸጥ የወጣው የጨረታ ማስታወቂያ አንድ ቀን ሲቀር በቀን 18/07/2018 እ.አ.አ ከቅርንጫፉ ስራ አስኪያጅ ጋር በመሆን ባለእዳው በቼክ 700,000.00(ሰባት መቶ ሺህ ብር) ገቢ እንዳደረጉ አስመስለዉ የሀሰት ሂሳብ አሳልፈዉ ለጨረታው እንቅፋት ፈጥረዋል፡፡ በአመልካች ድርጊት ተጠሪ ብር 4,794.52 አጥቷል፡፡ አመልካች በቀን 11/11/2010 ዓ/ም በሀሰት ገቢ የሆነውን ብር ቆጥሬ ተቀብያለሁ በማለት አፈሰር ይህንን ገንዘብ ገቢ እንዲያደርግ አድርገዋል፡፡ነገር ግን ገንዘቡ ገቢ የሆነበት ቀን ሲታይ ብር 350,000.00 በቀን 23/11/2011ዓ/ም ገቢ የሆነ ሲሆን ሌላዉ ብር 350,000.00 ገቢ የሆነዉ በቀን 350,000.00 ነዉ፡፡አመልካች ገንዘቡ ገቢ የሆነባቸዉን ኦርጅናል ሰነዶች እንዲጠፉ አድርገዋል፡፡አመልካች የፈጸሟቸዉ ድርጊቶች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27(1/ሐ) እና በባንኩ የሠራተኞች የሥራ ሂደት ፖሊሲ ቁጥር 1/ለ አንቀጽ 1/1 መሰረት በከባድ ማታለል ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያስናበት ጥፋት በመሆኑ አመልካችን በማሰናበት የተወሰደዉ እርምጃ ሕጋዊ ነዉ፡፡ስለሆነም አመልካች ወደሥራ ሊመለስ አይገባም እንዲሁም ሕገ-ወጥ ስንብት ተፈጽሟል በሚል የጠየቋቸዉ ክፍያዎችም ሊከፈላቸዉ አይገባም፡፡በባንኩ አሰራር መሰረት ደመወዝ የሚከፈለዉ በአዉሮፓ አቆጣጠር ወር በገባ በ20ኛ ቀን ላይ ጀምሮ በመሆኑ እስከ ቀን 20/06/2011ዓ/ም ድረስ ያለዉ የግንቦት ወር ደመወዝ ስለተከፈላቸዉ ያልተከፈለ ደመወዝ የለም፡፡ያልተከፈለ ደመወዝ መኖሩን በመግልጽ ለተጠሪ ያመለከቱት ነገር ባለመኖሩ ክፍያ ዘግይቷል በሚል የጠየቁት ሊከፈላቸዉ የሚገባ አይደለም፡፡ዉሉ የተቋረጠዉ የቦነስ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በቀን 07/09/2011ዓ/ም ስለሆነ ቦነስ ሊከፈላቸዉ አይገባም፡፡ አመልካች ብድር ስላለባቸዉና በብድር ዉሉ መሰረት ሠራተኛዉ ስራ ሲለቁ ከማንኛዉም ተከፋይ ክፍያ(ከፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ) ላይ ጭምር ተቀንሶ እንደሚከፈል ስለተመለከተ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያቸዉ ለእዳቸዉ ገቢ ሆኗል፡፡አመልካች የ60.5 ቀን የአመት እረፍት እንዳላቸዉ ባይካድም ሊከፈላቸዉ የሚገባዉ የባንኩን አሰራር በመከተል ያለባቸዉን እዳ ብር 294,429.66 ከፍለዉ ክሊራንስ ሲያቀርቡ ነዉ፡፡ያቀረቡት የወርቅ ሽልማት ጥያቄ የሕግ መሰረት የለዉም በማለት መልሳቸዉን በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 09416 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማትና ማስረጃዎችን በመመርመር በቀን 06/05/2012 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገዉ የሥራ ዉል ለማቋረጥ ምክንያት የሆነዉ የባንኩ ባለዕዳ እዳዉን መክፈል ባለመቻሉ ባንኩ በመያዣነት የተያዘዉን ንብረት ለመሸጥ ጨረታ አዉጥቶ እያለ አመልካች ባለዕዳዉ ብር 700,000.00 ገቢ እንዳደረገ በማስመሰል ትራንዛክሽን በማስተላለፍ ባንኩ የወጣዉ ጨረታ ሂደት እንዲቋረጥ በማድረግ ጥፋት መፈጸሙ በአዲት ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የትራንዛክሽን መደብ ሠራተኛ ሳይሆኑ ገንዘብ ያዥ እንደሆኑ ተጠሪም አልካደም፡፡ ስለዚህ አመልካች ይህን ሂሳብ መዝጋታቸዉን የሚያሳይ ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች ሲሰሩ በነበሩበት የሥራ መደብ ላይ የፈፀሙት ጥፋት የለም፡፡ የገንዘብ ማስተላለፍም ሆነ ጨረታን መዝጋት ሥራ የአመልካች ድርሻ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ለሥራ ውል መቋረጥ ምክንያት የሆነው ገንዘብ ለተጠሪ መስሪያ

ቤት ገቢ መሆኑንም ተጠሪ አምኗል። በመሆኑም የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕገ-ወጥ መንገድ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43 መሰረት ተጠሪ አመልካችን ወደ መደበኛ ሥራቸዉ እንዲመልሳቸዉና ከሐምሌ እስከ ጥር 2012 ዓ/ም ድረስ ያለዉን ደመወዛቸዉን እንዲከፍላቸው ወስኗል።

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 41159 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 26/08/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ውሳኔ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል።

በመቀጠል ተጠሪ የሰበር አቤቱታውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው ችሎቱም በመ/ቁጥር 336132 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 15/03/2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠዉ ውሳኔ በስር የቀረበው የኦዲት ውጤት ማስረጃ ተጠሪ የስራ ድርሻዬ የእዳ ገንዘብ ማስከፈል አይደለም ይበሉ እንጂ ደረቅ ቼክ በመውሰድ ባለእዳው እዳውን እንደከፈለ በማስመሰል ጨረታው እንዲሰረዝ ማድረጋቸውንና ደንበኛው ያለበትን እዳ ካዘጋ በኋላ ደንበኛው ያለበትን ብድር 2ኛ ዙር ክፍያ እዳ መክፈሉን የኦዲት ሪፖርቱ ያረጋግጣል።ዋናው እዳ ቢከፈልም ተጠሪ ሊያገኝ የሚገባውን በማጣቱ የኢኮኖሚ ጉዳት ደርሶበታል።የሥር ፍርድ ቤት ጨረታው እንዲሻር ያደረገዉ የባንኩ ሥራ አስኪያጅ መሆኑን እንጂ አመልካች ጥፋት መፈጸሙን የኦዲት ሪፖርቱ አያሳይም ያለ ቢሆንም ከተጠሪዉ ቅርንጫፍ ሥራ አሲኪያጅ ጋር በመሆን ደረቅ ቼክ በመቀበል እዳ ካዘጋ በኋላ ደንበኛዉ ያለበትን ብድር የ2ኛ ዙር ክፍያ መክፈሉ ቢረጋገጥም አመልካች በተጠሪ ላይ የብር 4,794.52 የኢኮኖሚ ጉዳት እንዲደርስበት አድርገዋል።ስለሆነም አመልካች በተጠሪ ላይ የኢኮኖም ጉዳት በማድረሳቸዉ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 27(1/ሸ) መሰረት ያለማስጠንቀቂያ የሚያሰናብታቸዉን ጥፋት ፈጽመዋል።በተጨማሪም አመልካች ደረቅ ቼክ በመቀበል በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1/ሐ) መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብታቸዉን የማታለል ድርጊት ፈመዋል።ስለሆነም ተጠሪ አመልካችን ያሰናበተዉ በሕግ አግባብ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል። አመልካች በቀን 27/05/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ መልኩ በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ።

አመልካች የተቀጠርኩበት የሥራ መደብ የካሼር የሥራ መደብ ሲሆን የሥራ ድርሻዬ ደግሞ ገንዘብ በካዝና ቆጥሮ ማስቀመጥ፣ካሽ ከሲስተም ጋር በማገናዘብ ወጪና ገቢ ሚዛናዊ(ባላንስ) መሆኑን ማረጋገጥ መሆኑን የሥራ ዉሌ የሚያሳይ ሲሆን ተጠሪም ከሥር ጀምሮ ይህንን አልካደም።አመልካች ገንዘብ ትራንዛክት የማድረግም ሆነ ብድር የመዝጋት ሥልጣን የለኝም።በጨረታዉ ላይም አልተሳተፍኩም።ተጠሪ ያሰናበተኝ ትራንዛክሽን በማሳለፍ እና ብድር በመዝጋት ባንኩ ማግኘት የሚገባዉን ብር 4794.52 አሳጥቷል በማለት ቢሆንም ያሰናበተኝ የሥራ ድርሻዬን ወደ ጎን በመተዉ በመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 92466 ላይ የተሰጠዉት የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ስንብቱ ከሕግ ዉጭ ነዉ።ገንዘብ ትራንዛክሽን የሚደረገዉ የሚስጥር ቁጥር ባለዉ የትራንዛክሽን ሠራተኛ ሲሆን ብድር የሚዘጉትም ይህ የሥራ መደብ የሚመለከታቸዉን

ኃላፊዎች እንደሆነ የተረጋገጠ ሲሆን በማንኛውም የባንኪንግ አገልግሎት የሚሰራበት አሰራር ነዉ፡፡ቼኩንና የተለያዩ ሰነዶችን ደብቋል የተባልኩትም በማስረጃ ካለመረጋገጡም በላይ የሥራ ድርሻዬን የሚመለከት አይደለም፡፡የሻሸመነ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ከተበዳሪዉ የተከፈለዉን ብር 700,000.00 በራሳቸዉ ፊርማ ገቢ አድርገዋል፡፡ተጠሪ ከሥራ ያሰናበተኝ ድርጊቱ ተፈጸመ ከተባለ ከአንድ አመት በኋላ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/3 ስር በተደነገገዉ መሰረት በ30 ቀን በኋላ የተወሰደ እርምጃ በመሆኑ በይርጋ የታገደ ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ስንብቱ በሕግ አግባብ የተፈጸመ ነዉ በማለት የስራ መደቤንና የሥራ ድርሻዬን ወደ ጎን በመተዉ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ጥፋት አጥፍቷል የተባለበት የስራ መደብና እሳቸው የሚሰሩት የስራ መደብ ቦታ ተዛማጅነት ያለው መሆን አለመሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ የሥራ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ ተብሎ የተወሰነበትን አግባብነት ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 15/08/2013ዓ/ም የተጻፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

አንድ የባንኩ ተበዳሪ እዳዉን ባለመክፈሉ ምክንያት ባንኩ በመያዣነት የያዘዉን ንብረት በጨረታ ለመሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ አዉጥቶ ጨረታ ሊደረግ አንድ ቀን ቀርቶ እያለ አመልካች ከተበዳሪዉ ለምን ደረቅ ቼክ ተቀብለን ብድሩን አንከፍልለትም በማለት በወቅቱ የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ለነበሩት የማጭበርበር ሀሳብ በማቅረብና በመስማማት በተበዳሪዉ ሂሳብ ዉስጥ ገንዘብ ሳይኖር ደረቅ ቼክ በመቀበል ለዚህ ሀሰተኛ ትራንዛክሽን እንዲመች ወደሂሳቡ ጥሬ ገንዘብ ገቢ ማድረጊያ ቅጽ በመሙላት ብር 700,000.00 ከተበዳሪዉ ሂሳብ ገቢ እንደሆነ በማስመሰል የደንበኞች ኦፊሰር አስፈርመዉ ትራንዛክሽኑ ፖስት እንዲደረግ ማድረጋቸዉ ተረጋግጧል፡፡አመልካች አሁን ላይ የሲስተም መጠቀሚያ ፓስወርድ የለኝም የሚሉት ካጠፉት ጥፋት ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡ስንቅ የሌለዉ ቼክ እንዲጸፍ ሀሳብ ከማቅረብ ጀምሮ ስለተሳተፉ የሲስተም ፓስወርድ እንዲጠቀሙ የሚያስገድዳቸዉ ሁኔታ ባለመኖሩና በእለቱ የእለት ቲኬቶች ጠቅለለዉ ሲይዙ የነበሩትም አመልካች ስለነበሩ ጉዳዩ ከእሳቸዉ ሥራ ጋር እንደማይገናኝ በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡የአመልካች ስራ ካሽ በካዝና ቆጥሮ ማስቀመጥና ከኮምፒዉተር ሲስተም ጋር ማገናዘብ እና ሚዛናዊ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሆነ ቢገልጹም በካዝና ዉስጥ ያለ ገንዘብ አረጋግጦ ማስቀመት ቀርቶ ገቢ ያልሆነን ገንዘብ ደረቅ ቼክ በመቀበል ገቢ እንደሆነ በማስመሰል የማይጠበቅባቸዉን ተግባር ፈጽመዋል፡፡የእለቱ ሂሳብም ባላንስ አለመሆኑን ለስር ፍርድ ቤት አስረድተናል፡፡ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ከዚህ አንጻር ተመርምሮ ጥፋቱ የአሁን አመልካች መሆኑ ተረጋግጦ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡አመልካች ይርጋን አስመልክቶ ያነሱት መከራከሪያ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ሰ/ሕግ ቁጥር 329/1 መሰረት ተቀባይነት ሊኖረዉ አይገባም፡፡አመልካችም በቀን 26/08/2013ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የየዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች ተቀጥረዉ ሲሰሩ የነበረዉ የሥራ መደብ የካሼር መደብ(የገንዘብ ያዥነት የሥራ መደብ) እንደሆነ ተጠሪ አልካደም፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን የተመለከተዉ ፍርድ ቤት እና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምረዉና መዝነዉ አመልካች ገንዘብ ያዥ(ካሼር) እንጂ የትራንዛክሽን መደብ ሠራተኛ እንዳልሆኑ፤ የገንዘብ ማስተላለፍም ሆነ ጨረታን መዝጋት ሥራ የአመልካች ድርሻ አለመሆኑንና ከዚህ ጋር በተያያዘ ተጠሪ አመልካችን ሲያሰናብት አመልካች የፈጸሙት ጥፋት ነዉ የተባለዉን ድርጊት አመልካች የፈጸሙ ስለመሆኑ ተጠሪ ባቀረቡት ማስረጃ አላስረዱም በሚል ተጠሪ አመልካችን ከሕግ-ዉጭ አሰናብቷል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ተጠሪ ዉዝፍ ደመወዝ በመክፈል አመልካችን ወደ ሥራ ገበታቸዉ እንዲመልስ ወስነዋል፡፡

ዋናዉን ክርክር ከመመርመራችን በፊት አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/3 ስር የተደነገገዉን ይርጋ አስመልክቶ ያነሱትን ክርክር ተመልክተናል፡፡በዚህ ድንጋጌ ላይ አንድ አሠሪ ዉሉን ለማቋረጥ የሚያስችል በአዋጁ አንቀጽ 27/1 ስር የተመለከተ ምክንያት መከሰቱት ካወቀብ ቀን ጀምሮ ባለዉ 30 ቀን ዉስጥ ዉል የማቋረጥ እርምጃ ካልወሰደ መብቱ በይርጋ እንደሚታገድ ተደንግጓል፡፡ይህ ይርጋ የተጠሪን ዉል የማቋረጥ መብት የሚያሳጣ በመሆኑ አመልካች ምክንያቱ የተከሰተበትን ቀን እና ተጠሪ ምክንያቱ የተከሰተበትን ቀን መቼ እንዳወቀ በማሳየት ለስር ፍርድ ቤት በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ በግለጽ ክርክር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ሆኖም በዚህ መልኩ ለስር ፍርድ ቤት ክርክር ማቅረባቸዉን የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ አያሳይም፡፡ይህንን መከራከሪያ ለስር ፍርድ ቤት አቅርቤያለሁ በማለት በመልስ መልሳቸዉ ላይ ያነሱ መከራከሪያም የለም፡፡በመሆኑም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ መሰረታዊ ሕግ ላይ ያለን የይርጋ መቃወሚያ በማንሳት ለመከራከር ስለማይቻል ከዚህ አኳያ ያቀረቡትን አቤቱታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 329/1 መሰረት አልተቀበልንም፡፡

በሌላ በኩል እንደሚታወቀዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 እና በተሻሻለዉ የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 64(2/ሐ) ስር እንደተመለከተዉ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ሆነ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ሥልጣን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ዉሳኔ እንዲያርሙ ነዉ፡፡ ሰበር ችሎት የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትንና ተቀባይነትን (Production,relevancy and admissibility of evidence)እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን (weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች ተጥሶ በግልጽ ተጥሶ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ መኖሩን አረጋግጦ ስህተቱ እንዲታረም ሊወስኑ ከሚችሉ በስተቀር

ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ ለመቀበል፣ለመስማትና ለመመዘን ሥልጣን ለተሰጣቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች አቅርበዉ ተመርምረዉ የተመዘኑትን ማስረጃዎች በድጋሚ የመመዘን ተግባር ዉስጥ በመግባት ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አከራካሪ የሆነዉ ፍሬ ነገር መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥልጣን የላቸዉም፡፡በመሆኑም ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃዎችን የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን የተሰጣቸዉ የሥር ፍርድ ቤቶች የቀረቡላቸዉን ማስረጃዎች መርምረዉና መዝነዉ ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር ወደ ጎን በመተዉ ማስረጃ በመመርምርና በመመዘን በፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ በመድረስ የሚሰጠዉ ዉሳኔ በሕግ ከተሰጠዉ ሥልጣን ዉጭ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን የተመለከተዉ የወረዳ ፍርድ ቤት እና ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመርመርና በመመዘን የአመልካች የሥራ መደብ ገንዘብ ያኘኑት እንደሆነ፣አመልካች ገንዘብ የማስተላለፍ (የትራንዛክሽን) የሥራ መደብ ሠራተኛ እንዳልሆኑና ገንዘብ የማስተላለፍ ተግባር የሥራ ድርሻቸዉ እንዳልሆነ፣ከብድር ገንዘብ አከፋፈልም ሆነ የተበዳሪዉን ንብረት በጨረታ ለመሸጥ የወጣ ጨረታ እንዲቋረጥ ከማድረግ ጋር በተያያዘ አመልካች የሥራ ድርሻቸዉ ስላልሆነ ሚና እንዳልነበራቸዉና ፈጸሙ የተባለዉን ጥፋት ስለመፈጸማቸዉ ተጠሪ ባቀረባቸዉ ማስረጃዎች አለማስረዳቱን በማረጋገጥ ተጠሪ አመልካችን በሕገ-ወጥ መንገድ አሰናብቷል በማለት የሰጡት ዉሳኔ ከማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር አንጻር ጉድለት አለበት ሊባል የሚችል አይደለም፡፡በሌላ በኩል የክልሉ ሰበር ችሎት በተጠቀሰዉ መሰረት በሕግ ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን የተሰጣቸዉ የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር ወደ ጎን በመተዉ በራሱ ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አመልካች በተጠሪ የኢኮኖሚ ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረሳቸዉና የማታለል ድርጊት መፈጸማቸዉ ተረጋግጧል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ተጠሪ አመልካችን ያሰናበተዉ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1/ሐ እና ሸ) መሰረት በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ከማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር አንጻር በስር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመ ስህተት መኖሩን የማያሳይና በሕግ ከተሰጠዉ ሥልጣን ዉጭ ማስረጃ የመመዘን ተግባር ዉስጥ በመግባት የሰጠዉ ዉሳኔ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የሻሸመኔ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09416 ላይ በቀን 06/05/2012 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እና የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 41159 ላይ በቀን 26/08/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንተዋል፡፡

2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 336132 ላይ በቀን 15/03/2013 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ትእዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

በመሆኑም በስር ፍ/ቤቶች ውሉ ሊፈርስ አይገባም መባሉ ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ መሰረታዊ ሕግ ስህተት የለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁጥር 242750 ህዳር 30 ቀን 2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይ/መ/ቁጥር 201347 ጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጠው ትዕዛዝ በፍ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**ሄ/መ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 201980

ቀን ፡- ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ መሠለ ማሚቶ - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ እሸቱ መኮንን - ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች በአጭር ሥነ-ሥርዓት ያቀረቡት ክስ ተጠሪ ላጋጠመው ችግር እንዲያውለው ለሠጠኋቸው ገንዘብ የቼክ ቁጥሩ 01960861 የሆነ ብር 120,000.00 የተጻፈበት ቼክ ፈርመው ሠጥተው ባንክ ለክፍያ ስሄድ ሂሳቡ በቂ ስንቅ የለውም ተብሎ የተመለሰ በመሆኑ ገንዘቡ እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ የመከላከያ ማስፈቀጃ ምክንያታቸው ተቀባይነት በማግኘቱ ያቀረቡት መልስ ለአመልካች የምመለሰው ገንዘብ የለም፣ ለአመልካችም የሰጠሁት ቼክ የለም፡፡ በክሱ የቀረበው ቼክ አመልካች ቤት ለሚጣለው ዕቁብ እኔ አባል በመሆኔ እጣ ወጥቶልኝ ብር

450,000.00 ገንዘብ ስወስድ ቀንና የገንዘብ መጠን የሌለው ቼክ ለእቁቡ ዳኛና ፀሀፊ በዋስትና የሰጠሁ ሲሆን አመልካች ራሱ ቼኩ ላይ ጽፎ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ላይ በቼኩ ምክንያት የወንጀል ክስ ቀርቦበት ቼኩን ለአመልካች አለመስጠቱንና ለዕቁብ ለዋስትና የተሰጠ ቼክ መሆኑ ተረጋግጦ ከክሱ በነጻ ተሰናብቷል፡፡ ቼኩ ለዕቁብ ዋስትና እንጂ ለአመልካች ያልተሰጠ መሆኑ ስለተረጋገጠ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራቀኙን አከራክሮ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ለቀረበው ክስ ቼኩና የባንክ ማረጋገጫ ቀርቧል፡፡ ለጉዳዩ የሰው ማስረጃ ሊሰማ አይገባም፡፡ የሰው ማስረጃ ከተሰማም የአመልካች ማስረጃም ሊሰማ ሲገባ በተጠሪ ምስክሮች ብቻ መወሰኑ ስህተት ያለበት ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ቼክን መሠረት ያደረገው ክስ ውድቅ መደረጉ ከንግድ ሕግ አንቀጽ 717 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አንጻር ለማየት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ አመልካች የሠው ማስረጃ ባለመዘርዘሩ አልተሰማለትም፡፡ ቼኩ ለዕቁብ ዋስትና የተሰጠ ነው፡፡ ለቼክ ክርክር የሠው ማስረጃ እንዳይቀርብ የሚከልክል ሕግ የለም፡፡ ተረጋግጦ የተወሰነ ነው ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ የሠበር አጣሪ ችሎት የያዘው ጭብጥን በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች በአጭር ሥነ-ሥርዓት ያቀረቡት ክስ ተጠሪ ላጋጠመው ችግር እንዲያውለው ለሠጠኋቸው ገንዘብ የቼክ ቁጥሩ 01960861 የሆነ ብር 120,000.00 የተጻፈበት ቼክ ፈርመው ሠጥተው ባንክ ለክፍያ ስሄድ ሂሳቡ በቂ ስንቅ የለውም ተብሎ የተመለሰ በመሆኑ ገንዘቡ እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪ የመከላከያ ማስፈቀጃ ምክንያታቸው ተቀባይነት በማግኘቱ ያቀረቡት መልስ ለአመልካች የምመለሰው ገንዘብ የለም፣ ለአመልካችም የሰጠሁት ቼክ የለም፡፡ በክሱ የቀረበው ቼክ አመልካች ቤት ለሚጣለው ዕቁብ እኔ አባል በመሆኔ እጣ ወጥቶልኝ ብር 450,000.00 ገንዘብ ስወስድ ቀንና የገንዘብ መጠን የሌለው ቼክ ለእቁቡ ዳኛና ፀሀፊ በዋስትና የሰጠሁ ሲሆን አመልካች ራሱ ቼኩ ላይ ጽፎ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመሠረቱ ቼክ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሀተታ የሌለበት ትዕዛዝ የያዘና ቼኩም እንደቀረበ የሚከፈል መሆኑ በንግድ ሕግ ቁጥር 827/ሀ/ እና 854 ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ቼኩ የታዘዘለት ሰው ቼኩን ይዞ እንደቀረበ ቼኩ ሊከፈል ይገባዋል፡፡ ቼክ አውጪውም ሆነ የጀርባ ፈራሚዎቹ ለቼኩ አከፋፈል በንግድ ሕግ ቁጥር 840 እና 868(ሐ) መሠረት ኃላፊዎች በመሆናቸው ቼክ ባልተከፈለ ጊዜ ተጠያቂዎች ይሆናሉ፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በአጭር ሥነ-ሥርዓት ክሱን ያቀረቡ ቢሆንም ተጠሪ ክሱን ለመከላከል

እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ፍ/ቤቱ የተቀበለው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 291 አግባብ ክርክሩ በመደበኛው ሥርዓት የሚመራ ነው፡፡

ተጠሪ ቼኩ ቀንና የገንዘብ መጠን የሌለው መሆኑን ገልጸው የተከራከሩ ሲሆን በቼክ ላይ የሚጻፉ አስፈላጊ መግለጫዎች ናቸዉ ተብለዉ በንግድ ሕግ አንቀጽ 827 ከፊደል ሀ እስከ ሠ ባሉት ንኡሳን አናቅጽ የተጠቀሱ መግለጫዎች(Contents)፡- ሀ) የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትእዛዝ፤ ለ) መክፈል የሚገባዉ ከፋይ ስም፤ ሐ) የሚከፈልበት ቦታ፤ መ) ቼኩ የወጣበት ቦታና ጊዜ እና ሠ) ቼኩን ያወጣዉ ሰዉ ፊርማ የሚሉ ናቸዉ፡፡በዚሁ ሕግ አንቀጽ 828 ስር ባለዉ የመግቢያ ዐረፍተ ነገር ላይ እንደተመለከተዉ ከእነዚህ መግለጫዎች አንዱ እንኳን የሌለበት ሰነድ እንደ ቼክ እንደማይቆጠር ተመልክቷል፡፡በዚህ ድንጋጌ ላይ “ከእነዚህ መግለጫዎች አንዱ እንኳን የሌለበት ሰነድ እንደ ቼክ አይቆጠርም” የሚለዉ አገላለጽ ላይ ላዩን ሲታይ ግልጽ ቢመስልም አገላለጹ የሚያገለግለዉ መግለጫዎቹ ያልተሟላ ቼክ በቼክ አዉጪዉ ተፈርሞ ለአምጪዉ በሚሰጥበት ጊዜ ነዉ ወይስ ቼኩ ለክፍያ ሲቀርብ ነዉ የሚለውን በመመልከት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 193270 ቼኩ በተሰጠ ጊዜ ከንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 አንጻር ቀንና የገንዘብ መጠኑ ባለመጻፉ የተሟላ ባለመሆኑ እንደ Blank Cheque የሚቆጠር ቢሆንም ቀንና የገንዘብ መጠን ተሞልቶ ለከፋዩ ባንክ በቀረበ ጊዜ ተሟልቶ ከቀረበ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 እና 828 ያስቀመጣቸዉን አንድን ሰነድ ቼክ የሚያሰኙ መገለጫዎችን የሚያሟላ ወይም እንደ ቼክ የሚቆጠር እና ሕጋዊ ዉጤት ያለው ነው በማለት አስገዳጅ ትርጉም የሠጠበት በመሆኑ እና አመልካች ለክፍያ ባንክ ያቀረቡት ቼክ በቂ ስንቅ የለውም መባሉ በቼኩ ላይ ያሉ መግለጫዎች ተሟልተው ለባንኩ መቅረቡን ስለሚያስገነዝብ ክስ የቀረበበት ቼኩ ሕጋዊ ውጤት ያለው ሠነድ ነው ብለናል፡፡

ተጠሪ በሁለተኛ ደረጃ የሚከራከሩት እና የሥር ፍርድ ቤት የተቀበለው ቼኩ ለዕቁብ ዓላማ ለዋስትና የተሰጠ ነው የሚል ነው፡፡ ቼክ ተላላፊ የገንዘብ ሠነድ በመሆኑና በዋስትናነት አይሰጥም በሚል በሕግ የተደነገገ ክልከላ ባለመኖሩ በመርህ ደረጃ ቼክ ለዋስትና ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም በሰበር መዝገብ ቁጥር 166392 ላይ በቀን 26/08/2012 ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ ላይ በመርህ ደረጃ አግባብነት ያለዉ የፍ/ብ/ህጉና የንግድ ህጉ ለቼክ የሰጡት ዋና ዓላማ ለመያዣነት እንዲያገለግል ነዉ ባይባልም እንደማንኛዉም ሊተላለፉ እንደሚችሉ ሰነዶች በመያዣነት ወይም በዋስትና ሊሰጥ እንደሚችልና ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግን በንግድ ህጉና በፍ/ብ/ህጉ ላይ በተቀመጡት ግልፅ ድንጋጌዎች መመራት ይኖርበታል (የን/ህ/ቁ 950 ና ፍ/ብ/ህ/ቁ. 2866)፡፡ በተለይ የመያዣ ዉል ስምምነት በሚደረግ ጊዜ ዉሉ መከተል ስላለበት ፎርም በተመለከተም በግልፅ የተደነገገ ስለመሆኑ ከን/ህጉ ቁ. 952 እና የፍ/ብ/ህጉ ቁ. 2828 መመልከት ይቻላል፡፡ የመያዣ ወይም የዋስትና ዉል ህጉ በፅሑፍ በሰነድ ካልተደረጉ በህግ ፊት ዋጋ የላቸዉም (ፈራሽ ናቸዉ) በማለት ከደነገጋቸዉ ጥቂት የዉል ዓይነቶች ዉስጥ አንዱ ስለመሆኑ ግልፅ ነዉ (የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1725(ሀ)፤ 1922(1-3)፣ 2828(1-2))፡፡ ሌላዉ ደግሞ የመያዣዉ ስምምነት ለምን ግዴታ እንደተደረገ፣ የግዴታዉ መጠን (ከፍተኛ የገንዘብ ወሰን) በጥንቃቄ ግልፅ መደረግ እንዳለበትና ስምምነቱ የተደረገበት ቀን በግልፅ ልቀመጥ እንደሚገባ ህጉ የግድ ይላል (የፍ/ብ/ህ/አንቀጽ 2828 (1-2)፣ 2864-2866ና የን/ህ/ቁ. 952)፡፡ እነዚህ የህጉ አስገዳጅ ድንጋጌዎች

ካልተሟሉ የመያዣ ስምምነት ዉል አለ ማለት አይቻልም። ስለሆነም ቼኩ የተሰጠዉ ለዋስትና ዓላማ እንደሆነ ተገልጾ በጽሁፍ የዋስትና ዉል ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር ቼክ ለዋስትና አላማ ተሰጥቷል በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት እንደሌለዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል።

ተጠሪ ቼኩን የሠጡት የዕቁብ ዕጣ ሲወጣላቸው ለዋስትና ዓላማ ከሆነ ይሕ ስለመሆኑ በጸሁፍ የተደረገ የመያዣ ውል (pledge) በማቅረብ ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል። የሥር ፍርድ ቤትም ቼክ ቁጥሩ ተገልጾ ለታወቀ ዕዳ መያዣ ስለመሆን አለመሆኑ በግራቀኙ ማስረጃ ሆነ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 መሰረት ተከራካሪዎች ካቀረቧቸው ማስረጃዎች በተጨማሪ ለክርክሩ አወሳሰን ጠቃሚ የሆነ የዕቁብ ዋስትና ውል ወይም መያዣ ውል ስለመኖር አለመኖሩ ጉዳዩን በማጣራት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተመለከተውን አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ ኃላፊነቱን ሳይወጣ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

## ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 338113 ጥር 18 ቀን 2013 ዓ/ም እና የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32991 መጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል።

2. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ቼኩን የሠጡት ለዕቁብ ዕጣ ሲወጣላቸው ለዋስተና ወይም ለመያዣ መሆን አለመሆኑን በማስረጃ በማጣራት የመሠለውን እንዲወስን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ጉዳዩን መልሠናል።

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ። የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል። ይጻፍ
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ተነስቷል። ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ




# ያልታተሙ የሰበር ውሳኔዎች በአንድ ተሰብስበው የተዘጋጁ ቅፅ 3

በዳንኤል ፍቃዱ ( ጠበቃና የህግ አማካሪ)